አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# "የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ"

በ

ኮማንደር መሐመድ

ILS LIBRARY

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

# “የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በዎባመር አካባቢ”

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያነት
የቀረበ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ኮማንደር መሐመድ

ጥቅምት 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# “የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ”

በ

ኮማንደር መሐመድ

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት

------------------------------ ------------------
አማካሪ ፊርማ

------------------------------ ------------------
የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

------------------------------ ------------------
የውጭ ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

የጥናቱን ርዕስ ከማስተካከልና ከማጽደቅ ጀምሮ የፊደል እርማት ሳይቀር ዓረፍተ ነገሮቼንም በማረም ጥናቱ ይህን ቅርጽ ይዞ እስኪወጣ ድረስ በእረፍት ሰዓት ጭምር እየሰሩ ለዚህ ያበቁኝን አማካሪዬን አቶ ዘሪሁን አስፋውን ከማንም በላይ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

የገንዘብ ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና የደቡብ አሪ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

በሁለት ዙር የመስክ ሥራዬ ጊዜ ያለ አንዳች ማቅማማት በቂና ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል ይህን ጥናት ሙሉ አካል ያደረጋችሁ በደቡብ አሪ ወረዳ የምባመር አካባቢ ነዋሪዎችና የምባ ባቢ አቶ ድክሳ አሰፋ፣ የደ/አ/ወ/አ/ጽ/ቤት ሰራተኞች እና ኃላፊዎች ከፍ ያለ ምስጋና ይገባችኋል፡፡ ተጨማሪ መረጃዎችንና ፎቶዎችን በመሰብሰብ የተባበርከኝ ታናሽ ወንድሜ ብዙአየሁ መሐመድ የዚህ ጥናት ልዩ ደጋፊ ነህና ኩራት ሊሰማህ ይገባል፡፡

መረጃ አቀባዮችን በመጠቆም እና የትምህርት ዘመኔን በሙሉ በሞራልና በገንዘብ ድጋፍ ያልተለያችሁኝ ቤተሰቦቼ አባቴ መሐመድ ብሩህቃል፣ እናቴ ዋያ ካይኪ እና ወንድሜ አስመላሽ መሐመድ ረጅም እድሜን ተመኘሁላችሁ፡፡

የተማሪነት ህይወቴን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው አብረሽኝ የተጋፈጥሽ፣ ያለማንም እገዛ ልጆቻችንን ያሳደግሽ፣ የሚስትነት ፍቅርና እንክብካቤ ያጐደልኩብሽ ውድ ባለቤቴ መሰለች አፍሪ፣ አብራችሁኝ የተጉላላችሁ ውድ የልጅነት ልጆቼ ይድነቃቻው ኮማንደር እና ቃል አለኝ ኮማንደር የዚህ ጥናት ልዩ ተመስጋኝ አድርጌ መረጥኳችሁ፡፡

መረጃዎችን ከመስጠት በተጨማሪ ላፕቶፕህን አርምበት ዘንድ የፈቀድክልኝ ጓደኛዬ ሙሉቀን ንጋቱ እና በኮምፒዩተር ጽሁፍ የተባበርሽኝ ወ/ሮ ታሪክ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## አጠቃሎ

በደቡብ ኦሞ ዞን በደቡብ አሪ ወረዳ የአሪ ብሔረሰብ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ ሀገረ-ሰባዊ እምነቶችን ይከተላል፡፡ የአሪ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ እምነቱ አድርጎ ከሚከተሏቸው በርካታ እምነቶች ውስጥ የበሪ እምነት እጅግ ይዘወተራል፡፡ “በሪ” ሴት አማልክት ስትሆን በወንድ አማልክትነት ከሚታመኑት “ሳቢ” እና “ጾይሲ” የበለጠ የዘወትር አምልኮ ይደረግላታል፡፡ በየክስተቱና በየአጋጣሚው የበሪ ስም ይነሳል፣ ለበሪ አምልኮ ይፈፀማል፡፡ ከ1976 ዓ.ም. ወዲህ በሌሎች ርዕሶች ስር የበሪን እምነት በጥቂቱ ጠቅሰው ካለፉ አንዳንድ ጥናቶች በስተቀር በእምነቱ ላይ አቢይ ትኩረት አድርጎ የተካሄደ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡

የአሪ ብሔረሰብ ለመኖሩና ላለመኖሩ፣ ለብልጽግናውና ለድህነቱ፣ ለጤንነቱና ለበሽታው መንስኤ አድርጐ የሚያምንበት ይህ የበሪ እምነት በውል አለመጠናቱ ለዚህ ጥናት ዋና አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡ ካለመጠናቱ በተጨማሪ ቢጠና ለብሔረሰቡና ለሌሎች (በተለይ ለፖለቲካ መሪዎች) ግለሰቦችና ድርጅቶች ያለውን ፖለቲካዊ፣ ስነ-ምግባራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ስነ-ልቡናዊ ፋይዳ ለይቶ የማሳየት ፍላጎትም ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአሪ ብሔረሰብ ዘንድ የሚፈፀመውን የበሪ እምነት ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ በመመርመር ምንነቱን እንዲሁም የእምነቱን ክዋኔዎች መቼትና አውድ፣ አከዋወን እና ደረጃ ማሳየት ነው፡፡ በእምነቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደሩ ጉዳዮችም ይገለጻሉ፡፡

ጥናቱ ገላጭና ተንታኝ ነው፡፡ ገለጻውና ትንተናው በብሔረሰቡ መካከል በአካል በመገኘት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መረጃዎቹ ከሁለት ዙር የመስከ ቆይታ ተሰብስበዋል፡፡ በመጀመሪያው የመስክ ቆይታ ጊዜ መረጃ አቀባዮችን መምረጥ፣ የክዋኔ መቼቶችን መለየት፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት ማድረግ ዋና ዋና ተግባራት ነበሩ፡፡ በሁለተኛው የመስክ ቆይታ ደግሞ ተጨማሪ መረጃ የማጠናቀር ስራ ተሰርቷል፡፡

በተገኙት መረጃዎችና በተደረገው ትንተና የአሪ ብሔረሰብ በጥብቅ የሚከተለው የበሪ እምነት ንብረት በከንቱ እንዳይባክን በሪን በማኖር የኢኮኖሚ አቅምን ሲያጠናክር፣ ወንጀልን በማውገዝና ወንጀለኛን በመገሰጽ ለፖለቲካዊና ማህበራዊ ሰላም፣ ለስነ-ልቡና መረጋጋት እና ለስነ-ምግባር ትምህርት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# SOUTH OMO




N

| W_NAME | area |
|---|---|
| Mago National Park | 136139.156888 |
| Selamago | 445006.659884 |
| South Ari | 152062.815052 |
| GELILA | 28123.351482 |
| Hamer | 569738.453709 |
| Bena Tsemay | 292275.863394 |
| Dasenech | 210231.346187 |
| Male | 143204.543278 |
| Gnangatom | 264949.408712 |

0 26,000 52,000 104,000 Meters

1 centimeter equals 13,914.118344 meters

Projected Coordinate System:
Adindan_UTM_Zone_37N

## ሙዳየ ቃላት

1. ዳም--------በለቅሶ ቦታ የአሪ ሴቶች ለማስለቀሻነት የሚጠቀሙበት የእንስራ ከበሮ፤ ማሰሮ አፉ በቆዳ ታስሮ ስሩ ተበስቶ የሚዘጋጅና አፉን በእጅ እየደበደቡ ለቅሶ የሚያደምቁበት መሳሪያ ነው፡፡
2. ሙዕሳ------የቡና ቅጠል ተፈልቶ የሚጠጣበት አነስተኛ የቅል ስንጣቂ
3. ማና---------ቃሉ ሲጠብቅ "ሴት" ማለት ሲሆን ሲላላ ደግሞ "የበታች ዘር" ለሚባሉት መጠሪያ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ሁለተኛ ትርጉሙ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡
4. ማታ---------በተመሳሳይ ንበት "ራስ" እና "ጎሳ" የሚሉትን ትርጉሞች ይይዛል፡፡ በዚህ ጥናትም ሁለተኛ ትርጉሙ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡
5. ሻላ--------------በአሪ ብሔረሰብ የበታች ዘር የሚባሉት በለቅሶአቸው ላይ የሚያሳዩት ፉከራ አዘል እንቅስቃሴ
6. ሾርቓ----------የውሃ፣የጠላ እና የወተት መጠጫ መካከለኛ የቅል ስንጣቂ
7. ቡንዳይ--------የቡና ቅጠል ማፍሊያ አነስተኛ እንስራ (ሸክላ)
8. በሪ/በረን-------የአሪ ሕዝብ የሚያመልካት ሴት አማልክት
9. ቶይዲ----------በእድሜ ታላቅ የሆነ ወይም ቀድሞ የተገኘ
10. አልቓ----------በለቅሶ ቤት የሚዘጋጅና የሚበላ ምግብ (ንፍሮ፣ እንሰት፣...)
11. ካለግር----------ተራ ትርጉሙ "በረት ውስጥ" ማለት ሲሆን በዚህ ጥናት ግን ከአካ ቀጥሎ በቤት ውስጥ የሚከናወን የወተት ቀመሳ ስርዓት ነው፡፡
12. ካሺ--------------የቤት እንስሳ ገዝቶ በአባት ማስመረቅ ወይም የአሪ ልጃገረድ ካገባች በኋላ ቤተሰቦቿ የመልስ ድግስ አዘጋጅተው የሚመርቁት የምርቃት ስርዓት
13. ወይሳ-------------ከቀጭን ቀርከሃ የሚዘጋጅ፣ ብዛቱ ስድስት የሆነ፣ ቁመቱ ከ10-15ሴ.ሜ. የሆነ፣በአፍ እየተነፋ ለጭፈራ ማድመቂያ የሚያገለግል ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ
14. ዓሜን/ኢንዲ------የዘር ሀረግ ግንድ መጠሪያ ስም
15. ዬሳ--------------በለቅሶ ጊዜ የአሪ ወንዶች ጋሻና ጦር ይዘው የሚያሳዩት ፉከራ አዘል እንቅስቃሴ
16. ይቻ-----------------ቀርከሃ ከሚመስሉ ብረቶች የሚዘጋጅና በቁርጭምጭምት የሚታሰር የጭፈራ ማድመቂያ መሳሪያ
17. ድሽታ---------------እህል ለመቅመስ የሚዘጋጅ ድግስ
18. ጎዳይ-----------------አንዲት አራስ ልጇ ጥርስ እስኪያበቅል ድረስ የምትቀይበት ጎጆ ቤት ወይም የጫጉላ ቤት ማለት ነው፡፡

## ማውጫ

ገጽ

## ምዕራፍ አንድ

### መግቢያ


1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................2

1.2. የጥናቱ ወሰን ....................2

1.3. የጥናቱ አላማ ....................2

1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፡- ....................3

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ....................3

1.6. የጥናቱ ዘዴ ....................3

1.7. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ....................3

1.8. የናሙና አመራረጥ ....................5

1.9. የመስክ ሥራ ....................5

1.10. በጥናቱ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች ....................7

1.11. የተወሰዱ መፍትሔዎች ....................8


## ምዕራፍ ሁለት

### ክለሳ ድርሳን


2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....................9

2.1.1. በሀገረ-ሰባዊ እምነትት ላይ የተደረጉ ጥናቶች ....................9

2.1.2. በአሪ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ....................11

2.2. የሀገረ-ሰባዊ እምነት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ....................13

2.3. ከበራ (Ritual) ....................14

2.3.1 የከበራ ዓይነቶች ........................................ 15
2.3.1.1 የሽግግር በዓላት ........................................ 15
2.3.1.2. ዓመታዊ እና የመታሰቢያ ከበራ ........................................ 16
2.3.1.3. የመንፃት ከበራ ........................................ 16
2.3.1.4. የመስዋዕት/የምስጋና ከበራ ........................................ 17
2.4 ክዋኔ ........................................ 17
2.5 አውድ ........................................ 18
2.5.1 ባህላዊ አውድ ........................................ 19
2.5.1.1 የትርጉም አውድ ........................................ 19
2.5.1.2 ተቋማዊ አውድ ........................................ 20
2.5.1.3 ተግባቦታዊ አውድ ........................................ 20
2.5.2 ማህበራዊ አውድ ........................................ 20
2.5.2.1 ማህበራዊ መሰረት ........................................ 20
2.5.2.2 ግለ-ሰባዊ አውድ ........................................ 21
2.5.2.3 ሁኔታዊ አውድ ........................................ 21

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዳራ

3.1. የደቡብ አሪ ወረዳ ........................................ 22
3.2. የአሪ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ........................................ 24
3.3. የአሪ ህዝብ ማህበራዊ መዋቅር ........................................ 26
3.4. ጋብቻ (ቴይሚ/ኤንሣ) ........................................ 27

3.5. የለቅሶ ስርዓት (ኤፊ) ........ 29
3.6. አመጋገብ (ኢስሚ) ........ 30
3.7. ባህላዊ ጭፈራ (ባይዳ) ........ 31

## ምዕራፍ አራት

## የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ክዋኔዎች ትንተና

4.1. ባቢ (ባላባት) ........ 34
4.2. ጎድሚዎች ........ 37
4.3. አንጀት የማንበብ ስርዓት ........ 40
4.4. የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ከበራ የሚፈጸምባቸው ዋና ዋና ቦታዎች ........ 42
4.5. የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ከበራ የሚፈጸምባቸው ጊዜያት ........ 43
4.5.1. እህል በሚዘራበት ጊዜ ........ 43
4.5.2. የሰብል ወረርሽኝ በተከሰተ ጊዜ ........ 45
4.5.3. በመኸር/ምርት መሰብሰብ ወቅት ........ 46
4.5.4. አዲስ እህል ሲገባ/ሲቀመስ ........ 46
4.5.5. የበሪ መገለጪያ ቀን ........ 48
4.5.6. በወሊድ ጊዜ ........ 52
4.5.7. ላም ስትወልድ ........ 54

## ምዕራፍ አምስት

## የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ለአሪ ብረሔረሰብ ያለው ፋይዳ

5.1. ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ........ 58
5.2. ፖለቲካዊ ፋይዳ ........ 58
5.3. ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ........ 60
5.4. ስነ-ምግባራዊ ፋይዳ ........ 61

ምዕራፍ ስድስት

ማጠቃለያ ........ 62
ዋቢ መጻሕፍት ........ 63

የፎቶ አባሪዎች

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት በደቡብ አሪ ወረዳ በ"ምባመር" አካባቢ የአሪ ብሔረሰብ በሚፈጽመው የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ "ምባመር" የአሪ ብሔረሰብ ከተከፈለበት ዘጠኝ ግዛቶች (ምዕራፍ ሶስት ይመልከቱ) አንዱ ሲሆን የአማርኛ ትርጉሙም "በአባታችን ይዞታ" እንደማለት ነው፡፡ "ምባ" ማለት "አባታችን" ማለት ሲሆን "-ሀመር" ማለት ደግሞ "ይዞታ/መሬት/ማሳ" ማለት ነው፡፡ የምባመር አሪ ከሌሎች አካባቢዎች ጋር የሚጋራቸው በርካታ ባህላዊ እሴቶች ቢኖሩትም የሚለይባቸው እሴቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል የበሪ እምነት በዘጠኙም ግዛቶች የሚታመን ሲሆን የእምነቱ ክዋኔዎች ግን በየአካባቢው ይለያያሉ፡፡ ይህ ጥናትም እነዚህንና የመሳሰሉትን ልዩነቶች መርምሮ በዝርዝር ለማቅረብ ከጊዜ እና ከገንዘብ እጥረት የተነሳ በአንዱ አካባቢ (ምባመር) ላይ ብቻ ያተኮረ መረጃና የመረጃ ትንተና አቅርቧል፡፡

ጥናቱ በስድስት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን ምዕራፍ አንድ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ ጠቀሜታ፣ የአጠናን ዘዴ፣ ወሰን፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመስክ ስራ፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችን እና የተወሰዱ መፍትሔዎችን አካቷል፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ከታተሙና ካልታተሙ ሰነዶችና መጻሕፍት የተገኙ ንድፈ ሀሳቦች እና ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን የያዘ ነው፡፡ ምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ መልክዓ ምድር፣ የስነ ህዝብ ዳራ፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ መዋቅር እና የኢኮኖሚ መሰረት ያሳያል፡፡

ምዕራፍ አራት የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ የሆነው የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ዋና ዋና ክዋኔዎች እና የክዋኔ መቼቶች የተካተቱበት ነው፡፡ አምስተኛው ምዕራፍ የበሪ እምነት ለብሔረሰቡ ያለውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊ እና ስነምግባራዊ ፋይዳ የተገለጸበት ነው፡፡ ምዕራፍ ስድስት በጥናቱ የተገኘውን ውጤት እና አስተያየት ይዟል፡፡ በመጨረሻም ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ ዋቢ መጻሕፍትና ጥናታዊ ጽሁፎች ተካተዋል፡፡ ከ መስክ የተሰበሰቡ ፎቶግራፎችም ተመርጠው በአባሪነት ቀርበዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ሀገረሰባዊ እምነት (folk belief) ለማጥናት ያነሳሱኝ ጉዳዮች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው በብሔረሰቡ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ላይ ሰፊ ጥናት አለመደረጉ ሲሆን ሁለተኛው እምነቱ ለብሔረሰቡ የሚሰጣቸውን ልዩ ልዩ ፋይዳዎች ለማሳየት ያለኝ ፍላጎት ነው፡፡ ከእነዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች በተጨማሪ በብሔረሰቡ ውስጥ ተወልጄ በማደጌ ስለ ሀገረ-ሰባዊ እምነቱ የቀደመ ግንዛቤ ስላለኝም ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ ወሰን

በደቡብ ኦሞ ዞን ከሚገኙት ስምንት ወረዳዎች መካከል ደቡብ አሪ ወረዳ የተመረጠ ሲሆን በወረዳው ከሚገኙት 48 ቀበሌዎች ውስጥ ሰባት ቀበሌዎች ብቻ ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ እነዚህ ቀበሌዎችም የአሪ ብሔረሰብ ከሚተዳደርባቸው ዘጠኝ ባላባታዊ ግዛቶች[1] ውስጥ በአንዱ (የምባ ባላባት[2]) ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበትም ወረዳው ካለው የቆዳ ስፋት መጠንና (በግምት የዞኑን 25%ይሸፍናል) መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ አመቺ አለመሆን (የትራንስፖርት አገልግሎት የለም-በበቅሎ ካልሆነ በስተቀር) እንዲሁም ከመረጃ አቀባዮች ጋር ካለኝ ትውውቅና ቅርበት አንፃር ነው፡፡

ጥናቱ ከላይ በተገለጸው ባላባታዊ ግዛት ውስጥ የአሪ ብሔረሰብ በሚፈጽመው “የበሪ እምነት” ላይ ተወስኖ በአዝመራ ጊዜ፣ በመኸር ጊዜ፣ በለቅሶ ጊዜ፣ ከቅድመ-ወሊድ እስከ ድህረ-ወሊድ ጊዜ እና በበሪ መገለጪያ ጊዜ የሚፈጸሙ የአምልኮ ክዋኔዎችን በዝርዝር ዳሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የስርዓቱን ማህበረ-ባህላዊ (socio-cultural values) ፋይዳዎች ተንትኗል፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአሪ ብሔረሰብ የሚፈጽመውን “የበሪ እምነት” በመመርመር ስርዓቱ ያለውን (የሚያበረክተውን) ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ ማሳየት ሲሆን ዝርዝር አላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

---

[1] “ባላባት” ማለት በቀደሙት የፖለቲካ ስርዓቶች ጊዜ የአንድ አካባቢ መሪ ማለት ሲሆን በአሁኑ ስርዓት ግን የሀገረ-ሰባዊ እምነቶች መሪ ማለት ነው፡፡ይህ ትርጉም በምባመር ባላባት ላይ የተመሰረተ ሲሆን አጠቃላይ የአሪን ብሔረሰብ ዘጠኝ ባላባቶች በአካባቢ ተከፋፍለው ይመራሉ፡፡ ባላባት በአሪኛ ባቢ ይባላል፡፡

[2] በአሁኑ ጊዜ የምባ አሪን የሚመራው ባላባት አቶ ድክሳ አስፍን ሲሆኑ የ75 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ ሁለት ሚስቶችና ስድስት ልጆች ያሏቸው፣ በስነምግባራቸው እጅግ የተወደዱ የማስትር ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ ምባ/ምባመር በአንድ ባላባት የሚመራ የአካባቢ ስም ነው፡፡

1. የበሪ እምነት መቼት፣ ክዋኔ እና አውድን መመርመር፤
2. የእምነቱን ማህበረ-ባህላዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች መለየት፤
3. በበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ጉዳዮችን ለይቶ ማሳየት፤

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች:-

- የበሪ እምነት መቼት፣ ክዋኔ እና አውድ ምንድን ናቸው?
- የበሪ እምነት ማህበራዊ ፋይዳዎች ምንድን ናቸው?
- በበሪ እምነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

1. ሀገረ-ሰባዊ እምነቱ በብሔረሰቡ ማህበራዊ ሕይወት ላይ ያሳደረውን አዎንታዊ ተጽእኖ ያሳያል።
2. ብሔረሰቡ በልማዳዊ ስርዓቱ ውስጥ የመሰረተውን የመቻቻል ባህል አጠናክሮ እንዲቀጥል ያበረታታል።
3. በዘርፉ (በሀገረ-ሰባዊ እምነት) እና በብሔረሰቡ ባህል ላይ ተጨማሪ ወይም አዲስ ጥናት ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች/አጥኚዎች መነሻ መረጃ ሆኖ ያገለግላል።

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የቀረበው በገላጫዊ (descriptive) ስልት ሲሆን ክዋኔ-ተኮር አቀራረብን (performance-centered approach) ተከትሎ የስርዓተ-አምልኮውን መቼት፣ አከዋወን፣ አውድ እና ተሳታፊዎች ያላቸውን ቦታ ይተነትናል።

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የፎክሎር ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ አጥኚው በቂ መረጃዎችን ለማግኘት የሚጠቀማቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ፈቃደ አዘዘ (1991፡90) ከነማብራሪያ ዘርዝረዋል። ከእነዚህም መካከል ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ምልከታ አጥኚው ጥናት ሊያካሂድበት በመረጠው ብሔረሰብ መካከል (ክዋኔ ላይ) ተገኝቶ የጥናቱ ትኩረት በሆነው የፎክሎር አይነት ላይ የሚያደርገው ጥልቅ አስተውሎት ነው፡፡ ምልከታ የሚያደርግበት ክዋኔ መቼቱ (ቦታውና ጊዜው) ተፈጥሮአዊ ወይም "አርቲፊሻል" ሊሆን ይችላል፡፡ ተፈጥሮአዊ መቼት ማለት ክዋኔው የሚፈፀምበት ትክክለኛ ቦታና ጊዜ ከመሆኑም በተጨማሪ የፎክሎሩ አይነት በትክክል የሚከሰትበትና የሚከወንበት አጋጣሚ ነው፡፡ አርተፊሻል መቼት ደግሞ ትክክለኛው መቼትና ክዋኔ በማይኖርበት ወይም አጥኚው በድጋሚ ለመመልከት በሚፈልግበት ጊዜ በማስመሰል የሚፈጥረው መቼት እንደሆነ Goldstein (1964፡80-81) ይገልጻሉ፡፡

ቃለ መጠይቅ አጥኚው ጥናት በሚያደርግበት የፎክሎር ዘርፍ ላይ ጥልቅ እውቀት ወይም ልምድ አላቸው ብሎ የመረጣቸውን እና የሚያምንባቸውን ሰዎች የተደራጀ ጥያቄ ወይም ያልተደራጀ ጥያቄ በማቅረብ በቃል መረጃ የሚያገኝበት ዘዴ ነው፡፡ የሚያገኛቸውን መረጃዎችም በማስታወሻ እና በድምፅ መቅረጫ ይይዛል፡፡ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ጊዜ የሚያጋጥም የመረጃ ክፍተትን ለመሸፈን እና የበለጠ ለማረጋገጥ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን አንድ ላይ በመሰብሰብ የቡድን ውይይት በማድረግ ክፍተቱ ይሞላል፡፡

ይህ ጥናት ሶስቱንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ በተጨማሪም ካልአይ የመረጃ ምንጮችንም ለማካተት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተለያዩ ቤተ-መጻሕፍት ስለ ሀገረ-ሰባዊ እምነት፣ ስለእምነት እና ተያያዥ ጉዳዮች የሚያትቱ መጻሕፍትና ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲሁም መጣጥፎች ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ በሀገረ-ሰባዊ እምነት እና በአሪ ብሔረሰብ ላይ የቀረቡ የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎችም ተዳሰዋል፡፡

ከመስክ ቆይታ መልስም የተቀረጹ መረጃዎችን ወደ ወረቀት የመገልበጥና የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ የተያዙ ማስታወሻዎችም በየይዘታቸው እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ መረጃዎች ወደ ወረቀት በሚዞሩበት ጊዜ የመረጃ አቀባዮች ዳራ፣ የክዋኔውን መቼትና አውድ በማስገባት ከመግለጫ ጋር ለማደራጀት ተሞክሯል፡፡ ከዚህም በመነሳት መረጃዎችን በመቼታቸው እና አውዳቸው በመከፋፈል ገለጻና ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

## 1.8. የናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋለው የናሙና አመራረጥ ዘዴ ታላሚ አመራረጥ (purposive sampling) ነው፡፡ ይህን ዘዴ በሚገባ ለመጠቀም የመስክ ጉዞ ከማድረጌ በፊት ጀምሮ ከቤተሰቦቼ፣ ከቀበሌ አስተዳደሮች እና ከዖባ ባላባት ጋር በስልክ በመገናኘት ሰባት ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙልኝ አድርጌያለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ እና ተያያዥ ነጥቦች ላይ ጥልቅ እውቀትና ልምድ ያላቸው ግለሰቦች፣ ሽማግሌዎች እና ጎድሚዎች[3] የታከሉበት አስራ አራት መረጃ አቀባዮችን መርጫለሁ፡፡ ከምርጫ በኋላም ለእያንዳንዱ መረጃ አቀባይ እንደሚመለከተው ጉዳይ ጥያቄዎችን አደራጅቻለሁ፡፡

## 1.9. የመስክ ሥራ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ አሪ ወረዳ ሁለት ዙር የመስክ ጉዞ አድርጌያለሁ፡፡ የመጀመሪያው ጉዞና ቆይታዬ ከጥር 01-30 ቀን 2004 ዓ.ም የዘለቀ ሲሆን በዚህም ቆይታ የመጀመሪያ ተግባሬ የነበረው ራሴንና ሥራዬን ከዞኑ አስተዳደር ጀምሮ እስከ ቀበሌዎች ድረስ ማስተዋወቅ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ከኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተፃፈልኝንና በደቡብ አሪ ወረዳ ላይ ስለ “የበሪ እምነት” ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚሆን ጥናት ለማድረግ መምጣቴን የሚገልጸውን ደብዳቤ ለዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት አቀረብኩ፡፡ በጊዜው የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተወካይ የነበሩት አቶ አለማየሁ ጭዶ ደብዳቤውን በአክብሮት ተቀብለውኝ ካነበቡ በኋላ በጥያቄዬ መሰረት ለደቡብ አሪ ወረዳ አስተዳደር እና መረጃ ሊሰጡኝ ከሚችሉ አካላት ጋር መገናኘት የሚያስችለኝን ደብዳቤ በአስቸኳይ ጻፉልኝ፡፡

የደቡብ አሪ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ቦጋለ መተኪያም የወረዳው ተወላጅ መሆኔን ስለሚያውቁ ምንም አይነት ጥያቄ ሳያቀርቡልኝ ወደ የቀበሌዎቹ ገብቼ መረጃ መሰብሰብ እንድችልና ለሚያጋጥሙኝ ችግሮች ትብብር እንዲደረግልኝ የሚገልጽ ደብዳቤ ጻፉልኝ፡፡ ይህን ደብዳቤ ይዤም ለዚህ ጥናት ወደተመረጠው ወደ ዖባ ባላባት አካባቢ ተጓዝኩ፡፡ ከዚያም ከአቶ

[3] በበሪ ስርዓተ-አምልኮ ውስጥ ከባላባት ባልተናነሰ ከፍተኛ ሚና ያላቸውና በተፈጥሮአቸው ከተፈጥሮ ጋር (ከዝናብና ጸሀይ፣ ከእንስሳት፣ ከጨረቃ፣ ከነፍሳት…) ልዩ ግንኙነት አላቸው ተብለው የሚታመኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ለባላባት እንደ አማካሪ ሆነው ከማገልገል በተጨማሪ በሕዝብ ላይ የሚመጡ የተፈጥሮ አደጋዎችን በአምልኮ ይከላከላሉ፡፡ በዖባ አሪ ሴቶችም ጎድሚ መሆን ይችላሉ፡፡

መሐመድ ቡርቃ[4] ጋር በመሆን የመረጃ አቀባዮቼን ዳራ መዘገብኩ። ለበለጠ ምርጫም ከምባ ባቢ ከአቶ ድክሳ አስፍን (አሰፋ) እና ከሻማመር ቀበሌ አስተዳዳሪ አቶ አሸብር ጋርሺ[5] ጋር ተመካክሬ ሰባት ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን እና ተጨማሪ አስራ አራት ሌሎች መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ ችያለሁ።

የመጀመሪያ ምልከታ ያደረኩት ክዋኔ ጥር 09 ቀን 2004 ዓ.ም ሲሆን ይህም በባቢው አቶ ድክሳ አስፍን ቤት የእህል ቀመሳ ክዋኔ ነው። የባቢው ቤት እኔ ካረፍኩበት ሰፈር በግምት ከ5-6 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። በዚሁ ዝግጅት ላይ በመገኘት የሚፈጽሙትን እምነታዊ ክዋኔዎች ለመመልከት፣ በድምፅ መቅረጫያ ለመቅዳትና በፎቶ ካሜራ ለመቅረጽ ችያለሁ። ለባቢና ለተወሰኑ ግለሰቦች ቃለ መጠይቅም አድርጌያለሁ። ከዚሁ ምልከታ ማግስትም ጥር 11 ቀን 2004 ዓ.ም. የጥምቀት በዓል ስለነበር በዚሁ በዓል ላይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች በዓላቸውን በሚያከብሩበት ጊዜ የአሪ ህዝብ የሃይማኖቱ ተከታይ ባይሆንም በዓሉ ላይ ከየቀበሌው በቡድን ተደራጅቶ ወደ በዓሉ መጥቶ በባህላዊ ሙዚቃው ይጨፍራል። ከዚህም በበሪ እምነት ጊዜ በአንዳንድ ክዋኔዎች ላይ የሚያቀርቡትን የብሔረሰቡን ባህላዊ ጭፈራ፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ እና አዘፋፈን ለመመልከትና ለመቅረጽ ችያለሁ።

ከእነዚህ ምልከታዎች በኋላ እስከ ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም. ድረስ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮች እና ለሌሎች መረጃ አቀባዮች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የቡድን ውይይት በማካሄድ ቆይቻለሁ። ከሁሉም ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ጋር ቃለ መጠይቅ ያደረግሁት በየቤታቸው በቀጠሮ ነው። ለሌሎች መረጃ አቀባዮች ቃለ መጠይቅ ያደረግሁት በአጋጣሚ እያገኘኋቸው ሲሆን የቡድን ውይይቱን ደግሞ ሰባት ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን በሻማመር ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ጥር 21 2004 ዓ.ም. በመሰብሰብ ነው።

ከጥር 22 እስከ 27 ቀን 2004 ዓ.ም. ድረስ ከጥናቱ ተተኳሪ አካባቢ (ምባመር) ወጥቼ ከወረዳው ዋና ከተማ ጋዘር ላይ በመሆን የወረዳውን አጠቃላይ ዳራ የሚገልጹ የጽሁፍ መረጃዎችን ከወረዳው የተለያዩ መስሪያ ቤቶች በመሰብሰብ እና ወደ ዞኑም በመሄድ ተጨማሪ መረጃዎችን በማጠናቀር ጥር 28 ቀን 2004ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ።

---

[4] አቶ መሐመድ ቡርቃ የ48 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ የ8 ልጆች አባት፣ ዘመናዊ ትምህርት የቀመሱ፣ በበሪ ስርዓት-አምልኮ ውስጥ አድገው የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን የተቀላቀሉና በአካባቢው ማህበረሰብ እጅግ የተከበሩ የቀሬትር ንውስ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው።

[5] አቶ አሸብር ጋርሺ የ34 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ የአራት ልጆች አባትና የሻማመር ቀበሌ ሊቀመንበር ናቸው።

ሁለተኛውን ዙር የመስክ ጉዞና ቆይታ ያደረኩት ከሚያዝያ 25 እስከ ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም. ነው፡፡ ይህን ጉዞ ያደረኩበት ዋና ምክንያት በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የአሪ ብሔረሰብ የሚያመልኳት "በሪ" ወደ ባቢው አካ ትመጣለች/ትገለጣለች ተብሎ የሚታመንበትና አምልኮ የሚደረግበት ቀን መሆኑን በመጀመሪያው የመስክ ቆይታዬ ጊዜ ስለአረጋገጥኩ ይህንኑ አምልኮ ለመመልከት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የዕለቱን ክዋኔ ለመመልከትና በፎቶ ለመቅረጽ ችያለሁ፡፡ በመጀመሪያው ዙር የመስክ ሥራ የታዩ የመረጃ ክፍተቶችም በድጋሚ ቃለ መጠይቅ እና በማስታወሻ እንዲሸፈኑ አድርጌያለሁ፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱም ዙር የመስክ ቆይታዬ በድምፅ መቅረጫ እና በፎቶ ካሜራ ታግዤ የምሰበስበውን መረጃ በሙሉ መረጃ አቀባዮቼ ያለ አንዳች ማንገራገር በፈቃደኝነት ሰጥተውኛል፡፡ በተለይም የምባ ባቢ የሆኑት አቶ ድክሳ አስፍን ማንኛውንም ክዋኔ በቀጥታ እንድመለከትና በፎቶም ሆነ በቪዲዮ ካሜራ መቅረጽ እንደምችል ከመፍቀዳቸውም በላይ ጥናቱ እዚህ ደረጃ እስኪደርስ በስልክ መረጃዎችን በማቀበል ተሳትፈዋል፡፡

## 1.10. በጥናቱ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች

ይህን ጥናት በማደርግበት ጊዜ የሚከተሉት ዋና ዋና ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡

1. የየእምነቱ ክዋኔዎች መቼት ተለይቶ አለመታወቅ (ከግንቦት ወር ላይ ክዋኔ በቀር ሁሉም ክዋኔዎች ተፈጥሮአዊ መቼታቸውን ማወቅ አይቻልም)፡፡
2. በጥናቱ አካባቢ የመኪና መንገዶች ባለመኖራቸው ከቀበሌ ቀበሌ ተንቀሳቅሼ መረጃዎችን ከቦታውና ከጊዜው ለመውሰድ አድካሚ ነበር፡፡
3. ከመስከረም ወር ጀምሮ እስከ የካቲት መጨረሻ የአሪ ህዝብ የኢኮኖሚው አጋር የሆነውን ቡና የሚለቅምበትና የሚነግድበት ጊዜ በመሆኑ በመጀመሪያው የመስክ ቆይታ ጊዜ መረጃ አቀባዮችን እንደልብ ማግኘት አልተቻለም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ከመረጃ አቀባዮች ቤት በተደጋጋሚ ለመመላለስ ተገድጃለሁ፡፡
4. የቪዲዮ ካሜራ ለፎክሎር አጥኚ ወሳኝ ማቴሪያል ቢሆንም ከአጥኚው የገንዘብ አቅም፣ ዩኒቨርስቲው ከሚፈቅደው አነስተኛ በጀት እና ከአካባቢው ነባራዊ እድገት አንፃር ለዚህ ጥናት የቪዲዮ ካሜራ መግዛት ወይም ከነባለ ሙያው መከራየት አልተቻለም፡፡

## 1.11. የተወሰዱ መፍትሔዎች

የማይታወቁትን የአምልኮ መቼቶች በቃለ መጠይቅ እና በአጋጣሚ በተገኙ ክዋኔዎች ላይ በመገኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። በተጨማሪም ከባላባቱ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ክዋኔዎቹ በሚፈፀሙበት ጊዜ በሰው እንዲያስጠሩኝ በማድረግ እና የሚታወቁትን መቼቶች (ለምሳሌ የግንቦት ወር ክዋኔን) ቀጠሮ በመያዝ የተሟላ መረጃ ተሰብስቧል። የቪዲዮ ካሜራ በማጣቴ መረጃዎችን በማስታወሻ፣ በድምፅ መቅረጫ እና በፎቶ ካሜራ ለማስቀረት ችያለሁ።

በወረዳው ገጠር አካባቢዎች ውስጥ ለውስጥ የሚያስገቡ የመኪና መንገዶች ባለመኖራቸው ውስጥ ለውስጥ ለመንቀሳቀስ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ ወረዳውን እና ዞኑን የገንዘብ ድጋፍ ጠይቄያለሁ። ይሁን እንጂ ከወረዳው ብቻ 1750 ብር አግኝቼ ከኪሴም ጨምሬበት ለበቅሎ ኪራይ እና ለመረጃ አቀባዮች አንዳንድ ወጪዎችን ከመሸፈን በተጨማሪ አድካሚ የእግር ጉዞም በማድረግ መረጃ በሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ ለመድረስ ችያለሁ። ወቅቱ በጋና የቡና ንግድ ወቅት በመሆኑ ለመረጃ ሰጪነት የተመረጡትን ሰዎች አስቀድሜ ቀጠሮ በማስያዝ እስከ ቤታቸው በመሄድ፤ ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች ውጭ ያሉትን ሰዎች ደግሞ በተገኙበት አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ከአማልክት (gods) ጋር ተያይዘው በሚፈጸሙ ሀገረ-ሰባዊ እምነቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ ጥናቶች፣ መጻሕፍት እና መጣጥፎች ተቃኝተዋል፡፡ በቅኝቱ ወቅትም እንደ በሪ ባሉ ሴት አማልክቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ባይገኙም በተለያዩ ወንድ አማልክቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ከእምነት ክዋኔዎች መመሳሰል አንጻር ተዳሰዋል፡፡ ጥናቱን ለመተንተን የሚያስችሉ ንድፈ ሀሳቦችና ቲዎሪዎችም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ተዳሰዋል፡፡

### 2.1.1. በሀገረ-ሰባዊ እምነት ላይ የተደረጉ ጥናቶች ቅኝት

ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ከሚመሳሰሉ ጥናቶች መካከል የመልስ በርሄ (1980) እና የግርማ ያደታ(1996) የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ናቸው፡፡ የመልስ በርሄ ስራ ለትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል በ1980 ዓ.ም የቀረበ ሲሆን የግርማ ያደታ ስራ ደግሞ ለ"ሶስዮሎጂ" ትምህርት ክፍል በእ.ኤ.አ.1996 የቀረበ ነው፡፡

የመልስ በርሄ ስራ በጉራጌ ብሔረሰብ ዘንድ የሚመለከውን "የቦዥ አምላክ" ወይም የጨረቃ አምላክ እምነት ክዋኔ የተነተነ ነው፡፡ "ቦዥ" ማለት የአምላኮች አምላክ፣ የእግዚ/ር የቅርብ መልዕክተኛ፣ ትክክለኛ የጉራጌ ህዝብ አባት፣...ማለት እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ለዚህ አምላክ የሚደረገው የእምነት ክዋኔ (አምልኮ) ደግሞ "ንፖር" እንደሚባል ይገልጻል፡፡

"የቦዥ አምላክ" እምነት በጉራጌ የተጀመረበትን ጊዜና ሁኔታ ሲገልጽም ጥንት የጉራጌ ህዝብ ከሲዳማ ብሔረሰብ ጋር በድንበር ላይ ሲዋጉ ሲዳማዎች በመሸነፋቸው ያመልኩት የነበረውን አምላክ እንደማረኩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የቦዥ አምላክ ከሲዳማዎች ጋር ተጣልቶ ወደ ጉራጌ ህዝብ (ሀገር) ገብቶ እንደነገሰ በማብራራት ጊዜውም ከ16ኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ ላይ እንደነበር ያሳያል፡፡ ስለ ቦዥ አምላክ አመጣጥ በዚህ ብቻም ሳያበቃ ቦዥ የመጣው (የተገኘው) "የመገራር" ከሚባል ወንዝ (ጉራጌዎችን ከሀዲያና ከምባታ አውራጃ የሚለይ) ከአንድ ወንድና (ሙጭረ) ከአንዲት ሴት (ዥምወት) ጋር እንደወጣ ይገልጻል፡፡

"የቦዥ አምላክ" በጉራጌ ህዝብ ዘንድ ህልውናውን ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ህዝቡ በየዓመቱ ጥር 22 ቀን የንፖር ስርዓተ ክዋኔ ይፈጽማል፡፡ የንፖር ጊዜ ሲደርስ ከሰባት ቀን በፊት ህዝቡ ከስራ፣ ከወንጀል እና ከቂም በቀል ራሱን አንጽቶ (ማንጻት) ይጠባበቃል፡፡ ለስርዓቱ አራት ቀን ብቻ ሲቀረው ደግሞ "ማጋ" የተባሉ የቦዥ አምላክ መንፈስ ያረፈባቸው ሰዎች ወይፈን ይዘው ሴቶቻቸውም የተነጠረ ቅቤ በመያዝ ስርዓቱ ከሚከናወንበት ቦታ አጠገብ በመሄድ ወይፈናቸውን አርደው እየጠበሱ ሲበሉ ቀኑ ሲደርስ ደግሞ ሁሉም የጉራጌ ህዝብ ያዘጋጀውን ስጦታ ይዞ ወደ ቦታው በመጓዝ ስርዓተ-አምልኮውን ይፈጽማል፡፡ ከዚያም ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ወንዶች ከጓሮአቸው በኩል በመሄድ በቤት ከተዘጋጀው ድግስ ከየአይነቱ በሾላ ቅጠል ውስጥ ይዘው በጓሮ አትክልት ላይ ይረጫሉ፤ ይበትናሉ፡፡ የተቀረውን (አስተርፈው) ወደ ቤት በመግባት ከሚስትና ሌሎች ቤተሰቦች ጋር ይበላሉ፡፡ በጓሮው ስርዓት ላይ ሴቶች አይሳተፉም፡፡

በአጠቃላይ የመልስ በርሄ ስራ እነዚህንና መሰል ክዋኔዎችን ከመተንተን ባሻገር ስነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳዎቻቸውን በማሳየት የስርዓቱ ጎጂ ጎኖችን (ሴቶችን ማግለሉ፣ የኢኮኖሚ ውድመቱ/ስጦታው፣ የግለሰቦች የበላይነቱ፣ ወዘተ.) የሚመለከታቸው አካላት እንዲያስተካክሉ ሀሳብ በመስጠት ተደምድሟል፡፡

የመልስ ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው ስለ ሀገረ-ሰባዊ እምነትም ሆነ ስለ ክዋኔ በንድፈ ሀሳብ አስደግፎ ባለማቅረቡ እና በአንድ ክዋኔ ላይ ብቻ በማተኮሩ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር በአጠቃላይ የአጠናን ዘዴው፣ አላማው እና የመረጃ አሰባሰቡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ገጽታ አለው፡፡

ሌላው ተዛማጅ ጥናት የግርማ ያደታ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት የኦሮሞ ህዝብ በተለይም የገዳ ማህበረሰብ "Waaqa" ለተሰኘው አምላክ የሚያከናውነውን ስርአተ-አምልኮ የተነተነ ነው፡፡ "Waaqa" በብሔረሰቡ እምነት እውነተኛ፤ የተከበረ፤ የቡዳ መንፈስ ያልሆነ፤ ሰው ሰራሽ ያልሆነ፤ ፈጣሪ አምላክ ተብሎ ይታመናል፡፡ በእምነቱም ውስጥ አያና (Ayaana)፤ ቃአሉ(Qaalluu)፤ ወዘተ. የተባሉ አገልጋዮች (spirits) ሲኖሩት እነዚህም ዋና ተግባራቸው ህዝቡን ከዋቃ ጋር የሚያገናኙ ድልድይ በመሆን ማገልገል ነው፡፡ ስለዚህም አንድ ሰው ችግር ቢገጥመው አስቀድሞ ምህረት የሚጠይቀውና የሚጸልየው "ዋቃ"ን ሳይሆን አያናን ወይም ቃአሉን ነው፡፡ እነሱ ደግሞ ስለዚሁ ሰው ወደ "ዋቃ" ያማልዳሉ:: "ዋቃ" በሰማይ የሚኖር የሁሉ ፈጣሪና ገዥ ተብሎ ይታመናል፡፡ እንደሚስቱ (ሴት አማልክት)ተደርጋ የምትታመነው ደግሞ "ላፋ" ትባላለች:: "ላፋ" በምድር ላይ የምትኖር የዋቃ ሚስት ተደርጋ ትታመናለች፡፡ በችግር ጊዜ ህዝቡ ሲፀልይም የሁለቱን ስም በየተራ እየጠራ ይፀልያል፡፡

ከዚህ ባሻገር በእምነቱ ውስጥ ከሚከናወኑት በርካታ ስርዓተ ክዋኔዎች ውስጥ አብዛኞቹ በቤተሰብ አባላት ዘንድ የሚከናወኑ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በወንዶች ብቻ አንዳንዶቹ ደግሞ በሴቶች ብቻ (ለምሳሌ Dhaabbata Maarama) የሚከናወኑ ስርዓቶች ናቸው። በሁሉም ዘንድ በጋራ የሚከናወነው ስርዓተ-አምልኮ ደግሞ "Jaarii" ሲባል ይህም "Jammoo" ለተሰኘ አማልክት የሚደረግ አምልኮ ነው። "Jammoo" በሁሉም ቦታ በፍጥነት የሚገኝ የ"Waaqa" የቅርብ መልእክተኛ ተብሎ ይታመናል።

ግርማ በጥናቱ የእነዚህን ስርዓተ ክዋኔዎች ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ባሻገር ይህ የኦሮሞ ህዝብ ባህላዊ እምነት (waaqa) ለግለሰቦችም ሆነ ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማሳየትና የስርዓቱ አገልጋይ የሆኑት ሰዎችም (አያና፣ ቃአሉ፣ ወዘተ) ለህዝቡ ብሎም ለሰው ልጅ ህይወት ዘብ የቆሙ መሆናቸውን በመግለጽ ጥናቱን ይቋጫል።

የግርማ ጥናት በቦታውና በባህሉ ልዩነት እና እንደ መልስ በርሄ ንድፈ ሀሳቦችን ካለመመልከቱ በስተቀር ዝርዝር ክዋኔዎችን በመተንተን፣ የእምነቱን ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳዎች በማሳየት ረገድ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው።

### 2.1.2. በአሪ ብሔረሰብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች

በተጠናል በአሪ ብሔረሰብ ላይ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት በአያሌው ምትኩ "የአሪ ሕብረተሰብ የስም አወጣጥ" በሚል ርዕስ በ1976 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበው ጥናት የመጀመሪያ ተጠቃሽ ነው። የአያሌው ጥናት ዋና አላማ በአሪ ሕብረ-ተሰብ የስም አወጣጥ ስርዓትን መመርመር ቢሆንም ሀገረ-ሰባዊ እምነታቸውንም ጠቅሷል። ጥናቱ ግን በቃለ መጠይቅ ላይ ብቻ የተመረኮዘ ነው። የአያሌው ጥናት በቦታው ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ጥናት ጋር በአጠናንም ሆነ በርዕስ አይገናኝም። ከአያሌው ጥናት ቀጥሎ ናምሲ አልቃ "አሪኛ ከአማርኛ የተዋሳቸው ቃላት" በሚል ርዕስ በ1980 ዓ.ም. ያቀረበው ጥናት ይገኛል። ይህ ጥናትም ስለ አሪኛ ቋንቋ ታሪክና የቃላት ተውሶ ከማተት በስተቀር ስለ ሀገረ-ሰባዊ እምነት በምንም ሁኔታ አልገለጸም። ጥናቱ አላማውም ሆነ የአጠናን ዘዴው አልተጠቀመም። ስለሆነም የናምሲ ጥናት አሪ ላይ የተሰራ ከመሆኑ በስተቀር በምንም አይነት ከእኔ ጥናት ጋር አይመሳሰልም።

ሌላው በአህመድ መሐመድ "የአሪ ብሔረሰብ የቢዩ ባላባታዊ ቤተሰብና የለቅሶ ስርዓቱ" በሚል ርዕስ በ1989 ዓ.ም. ያቀረበው ጥናት ነው። የአህመድ ስራ ከእኔ የሚለየው የእኔ ትኩረት በአይን በማትታየውና በእጅ በማትዳሰሰው በ "በሪ" ስም የሚደረገውን አምልኮ እና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳውን በጥልቀት መመልከት ላይ ሲሆን የአህመድ ግን ከባላባታዊ ቤተሰብና የለቅሶ ስርዓቱ በቀር ስለ በሪ እምነት ያነሳው ታሪክ የለም። የባላባት እምነቱም ጎጂ እንደሆነ ያምናል። በአጠናን ዘዴውም ሆነ ጥናቱን በንድፈ ሀሳቦች በማስደገፍ በኩል ከእኔ ጥናት በሰፊው ይለያል።

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ደግሞ በገብሬ ይንትሶ እ.ኤ.አ. በ1995 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማህበራዊ አንትሮፖሎጂ የቀረበው ጥናት ይጠቀሳል። የገብሬ ይንትሶ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው የአሪ ብሔረሰብ የሚተገብረውን የምርት ስራ ቢሆንም የብሔረሰቡን ባህላዊ እምነትም ዳሷል። በዚህም ብሔረሰቡ የተለያዩ እምነቶች እንዳሉትና ከነዚህም "ሳቢ" እና "በሪ" የተባሉት በጣም የታወቁ አማልክት መሆናቸውን በመጠቆም የሚደረግላቸውን አምልኮም በወፍ በረር ገልጾታል። ከነዚህ አማልክት በተጨማሪም በቤተሰብ ደረጃ የሚመለኩ የግል አማልክት (ባቢ ቶይድ /Ancester, ሳቢ ባብ /magician/፣ አካ/ Aka፣ ወዘተ. እንዳሉ ጠቁሟል።

በእኔ ጥናት እንደተገነዘብኩት ታዋቂና ገናና አማልክት "ሳቢ" እና "በሪ" ቢሆኑም "ሳቢ" የሚለውን ቃል በአሁኑ ጊዜ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች "እግዚአብሔር" ለማለት ይጠቀሙታል። እንደ ብሔረሰቡ እምነት "ሳቢ" ወንድ አማልክት ሲሆን "በሪ" ደግሞ ሴት አማልክት ነች። ነገር ግን የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ሲስፋፋ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን የተቀላቀሉት የብሔረሰቡ አባላት ድሮ በባህላዊ እምነቱ ለወንድ አማልክት ያገለግል የነበረውን መጠሪያ ቀጥታ በመውሰድ "እግዚብሔር" ለሚለው ቃል ትርጉም አድርገውታል። ከዚያም በፕሮቴስታንትና በባህላዊ እምነቱ ተከታዮች መካከል "ሳቢ" የሚለው ቃል "አምላክ" የሚለውን ቃል የሚገልጽ ሆኗል። ከሳቢ በተጨማሪ "ጾይሲ" የሚባል እጅግ የሚፈራ ወንድ አማልክትም አላቸው። የወንድ አማልክቶቹን በተመለከተ ራሱን የቻለ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል።

ተስፋዬ ኃይሉ "Childbirth and Seclusion among the Omotic Ari" በሚል ርዕስ በ12ኛው የኢትዮጵያ ጥናት ኮንፈረንስ ላይ እ.ኤ.አ.በ1994 ያቀረበው ጥናታዊ መጣጥፍ የአሪን ባህላዊ (ሀገረ-ሰባዊ) እምነት በጥልቀት ባይሆንም በስፋት የዳሰሰ ነው። በጥልቀት ባይሆንም ያልኩበት ምክንያት በብሔረሰቡ የሚከናወኑ የተለያዩ አምልኮዎችን በሙሉ ከመዘርዘር በስተቀር (ለማስተዋወቅ ያህል) አንዱንም በፎክሎር ንድፈ ሀሳብ (theory) አስደግፎ አልተነተነም። ካነሳቸው አምልኮዎች መካከል ለምሳሌ ያህል "The Spirit of Ancestors, the Godmis,

Bunka, the Influence of the Belief system on gender and social status, እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። እነዚህ እያንዳንዳቸው ሰፊ ጥናት የሚያስፈልጋቸው ቢሆኑም ተስፋዬ በዋዛ አልፏቸዋል።

የተስፋዬ ሥራ ከዚህ ጥናት የሚለየው በመላው የአሪ ብሔረሰብ የሚፈጸመው የበሪ እምነት ከልደት ጋር በእጅጉ የተያያዘ መሆኑን አላመለከተም። የእኔ ጥናት ደግሞ የወሊድ ጊዜ አምልኮን ጨምሮ የተለያዩ ክዋኔዎችን ከመመልከቱ በተጨማሪ የስርዓተ-አምልኮውን ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ ይዳስሳል።

## 2.2. የሀገረ-ሰባዊ እምነት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ከፎክሎር አራት ዋና ዋና ዘርፎች አንዱ ሀገረ-ሰባዊ ልማድ ነው። ሀገረሰባዊ ልማድ ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች በበለጠ ለመግለጽ አስቸጋሪ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ። ልማድ ማለት በተደጋጋሚነት የሚደረግ እና በተመሳሳይ መንገድ የሚፈጸም ድርጊትን ይገልጻል። በዚህም የተነሳ የፎክሎር ተመራማሪዎች ልማድን "የሚደጋገም ባህርይ" በማለት የሚገልፁት መሆኑን Smith *(2005: 16-17)* ያብራሉ፡-

> A custom is a repeated habitual action, a usual way of doing something. For folklorists, custom refers to patterned, repeated behaviourin which person's participation indicates involved membership. These practices may be situations that are stylized and /or "framed" by special words, gestures or actions that set them apart from every day behaviours, or they may be as simple as gestures used in every day communication with an intimate group of friends.

ተደጋጋሚነት የሚታይባቸው የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎች እምነት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው። ሰዎች ያመኑበትን ነገር በየጊዜው በተመሳሳይ ክዋኔዎች፣ በተመሳሳይ አልባሳት፣ ተመሳሳይ ቀለማትን በመቀባት፣ ለእምነቱ የሚያስፈልገውን የሰውነት እንቅስቃሰዎች (ዳንስ፣ ጭፈራ፣ ሽብሸባ፣ ስግደት፣ወዘተ.) በማድረግ ያመልካሉ (Pascal and Pierrer 2006፡37-39)። ሀገረ-ሰባዊ ልማድም ካሉት አራት ዘርፎች (ፌስቲቫልና ክብረ በዓል፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ባህላዊ መድኃኒት) ውስጥ ሀገረሰባዊ እምነት ይመደባል።

ሰዎች ላመኑበት ነገር ይታዘዛሉ፤ ይፈራሉ፤ ያከብራሉ፤ ይገዛሉም። ያመኑበት ነገርም (መንፈስ፣ ግዑዝ፣ ሰው) ለአማኞቹ እውነተኛነቱን ለማሳየት ልዩ ኃይል ይቀዳጃል። ሀገረሰባዊ

እምነት ስሙ እንደሚያመለክተው ከግለ ሰባዊነት ይልቅ ቡድናዊ እና ማህበረሰባዊ ይዘት አለው። ከዚህም የተነሳ ሰዎች ሃይማኖታዊ አምልኮውን በቡድን/በጋራ ይፈጽማሉ *(Smith 1950:15)*።

እምነት በአንድ ነገር ላይ አእምሮ የሚፈጥረው መተማመን ወይም እርግጠኝነት ነው። እምነት የሰዎች የማንነት፣ የእንዴትነትና የውጤታማነት መሰረት ነው። በየትኛውም የማህበረሰብ ክፍል አንድ የጋራ የሆነ የእምነት ፍልስፍና ይኖራል። በየትኛውም የእድሜ ክልል ያሉትም የዚያ ፍልስፍና አማኝ/ተከታይ ይሆናሉ። ይህም የሚታመኑበት ነገር "ያደርጋል" ያሉትን እንደሚያደርግ ተመሳሳይ አመለካከት፣ ተመሳሳይ እምነት ያድርባቸዋል።

ሰዎች ስለ ማንነታቸው፣ ስለ እንዴትነታቸው፣ ከየት ስለ መሆናቸው፣ እና ወደየት ስለ መሄዳቸው ለማወቅ በተጨነቁ ጊዜ ለጥያቄዎቻቸው መልስ የሚሰጣቸውን አንድ ልዩ አካል ይፈጥራሉ። ሁሉም ነገር ከዚሁ አካል እንደሆነና እንደሚሆንም ያምናሉ። እምነት ከሃይማኖታዊ ትርጉሙ በተጨማሪ በአንድ ነገር እርግጠኛ መሆንንም ይገልጻል። ፈቃደ አዘዘ (1991:14) የሀገረሰባዊ እምነት ምርምር የሚያተኩርባቸውን ጉዳዮች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

> የሀገረሰባዊ ሃይማኖት ምርምር፣ በልዩ ልዩ በዓላት ላይ፣ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ሃይማኖት (መስግድ፣ ቤተክርስቲያን፣ምኩራብ፣ወዘተ.) የሚያካሂዱትን ክንዋኔዎች፣ በልደት፣ በግዝረት፣ በክርስትና፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክንዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን (interactions) ያጤናል። የጥናቱ ትኩረት ግን ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እመመርመር ላይ ነው። ለምሳሌ፦ በሃይማኖት ስርዓቶች ላይ በሚደረገው ጥናት፣ ትኩረቱ በታወቁት የሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ ሰዎች በየራሳቸው (የሃይማኖቱ አማኝና ተከታይ መሆናቸው ሳይቋረጥ ማለት ነው) በሚከተሏቸው እምነቶችና በሚፈጽሟቸው እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው።

በአጠቃላይ "እምነት" ማለት በተወሰኑ ግለ-ሰቦች/ቡድኖች ዘንድ አንድን አካል (ሰው፣ግዑዝ፣ መንፈስ) ፈጣሪ፣ አድራጊ፣ ሁሉን ቻይ፣ አዳኝ፣ ወዘተ. አድርጐ በማመን የሚመነጭ ጠንካራ ስሜት ነው።

## 2.3. ከበራ (Ritual)

ከእምነት ጋር ተያይዞ የሚነሳውና የማይቀረው ጉዳይ ከበራ ነው። ማንኛውም እምነት የራሱ የከበራ ስርዓት (ritual) አለው። ከበራ አማኞቹ የሚያደርጉትን ስግደት፣ መስዋዕት፣ ዝማሬ/ውዳሴ፣ ስዕለት፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎች (ዳንስ፣ ጭፈራ፣ ሽብሸባ፣ ወዘተ) ይመለከታል፡ ፡ እነዚህን በማድረግም ለሚያምኑበት ነገር ያላቸውን ክብር/እምነት ይገልጻሉ። የሚደርስባቸውን አደጋም (ችግር) ያስወግዳሉ። ስለዚህም እነዚህን ከበራዎች ሆነ ብለው ይፈጽማሉ።

በከበራ አማካይነት አማልክት/እግዚአብሔር (gods/God) ከአማኞቹ ጋር ይገናኛል፤ መለኮቱንም ይገልጥላቸዋል። በዚህም አማኙ ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል፤ ይጠቀምበታል። Hamer በሲዳማ ብሔረሰብ የሚመለከውን አማልክት (Magano) በተመለከተ ባደረጉት ጥናት "የሲዳማ ብሔረሰብ ከአምላካቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያደርጉ ነበር። ነገር ግን የኋላ ኋላ ከሰዎቹ ጋር በመጣላቱ ርቆ መኖርን መረጠና ወደ ሰማይ አረገ። ከዚያም በመረጣቸውና በወደዳቸው ሰዎች (Shatana) አማካይነት ብቻ ከአማኞቹ ጋር ይገናኛል።" በማለት ቸሩሊን ጠቅሰው ገልፀዋል (Hamer 1966፡392)። አማኞቹ ከአምላካቸው ጋር መገናኘት የሚችሉት በአምልኮ (ለ"ማገኑ" ስዕለት በመግባት፣ መስዋዕት በማቅረብ፣ ወዘተ.) ነው። አምልኮ/ከበራ የእምነት ክዋኔ ነው። ስለዚህም ማንኛውም አማኝ እምነቱን በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል።

## 2.3.1. የከበራ ዓይነቶች

ሰዎች እምነታዊ በዓላትን የሚያከብሩባቸው ምክንያቶች እንደ የማህበረሰቡ የአኗኗር ስርዓትና እሴት የተለያዩ ናቸው። በዚህም የተነሳ በውስጣቸው የሚያካትቷቸው ሥነ-ሥርዓቶችም ከባህል ባህል ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያያሉ። በአንዳንድ ባህሎች በአንዱ ስር የተመደቡት ሥርዓቶች ከሌላው ጋር ተቀይጠው ሊከወኑ ይችላሉ። Catherin Bell (1997፡93-94) ክብረ በዓላትን በስድስት የመደቡ ሲሆን ከነዚህም አራቱ ብቻ በዚህ ጥናት ተዳሰዋል። ምክንያቱም በጥናቱ ከሚተነተኑ ከበራዎች ውስጥ በቀጥታ የሚመለከቱት አራቱ ብቻ ሲሆኑ እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

### 2.3.1.1. የሽግግር ከበራ (Rites of passage)

ይህ የከበራ አይነት ሰዎች ከአንድ ደረጃ ወደ ቀጣይ ደረጃ በሚሸጋገሩበት ጊዜ የሚፈጽሙት ከበራ/አምልኮ ነው። በዚህ አይነት ከበራ ውስጥ የሚጠቀሱትም በልደት ጊዜ፣ በሞት ጊዜ፣ በግዝረት ጊዜ እና እነዚህን በመሳሰሉ የሕይወት ዑደቶች ጊዜ የሚፈጸሙ ከበራዎች ናቸው።

> Rites of passage are ceremonies that accompany and dramatize such major events as birth, coming-of-age initiations for boys and girls, marriage, and death. Sometimes called "life-crisis" or "life-cycle" rites, they culturally mark a person's transition from one stage of social life to another. (Bell 1997:94).

በዚህ አይነት ክበራ ውስጥ የተካተቱት ክበራዎች እንደየባህሉ በግል፣ በቤተሰብ እና በአጠቃላይ ማህበረሰብ ሊከበሩ ይችላሉ። ለምሳሌ የሞት ጊዜ ክበራ በግል አይፈጸምም። የግርዛት ግን በግል/በቤተሰብ ሊፈጸም ይችላል። በአሪ ብሔረሰብ በወሊድ ጊዜ እና በባቢ ለውጥ ጊዜ የሚፈጽሟቸው ክበራዎችም በዚሁ የክበራ አይነት ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ።

### 2.3.1.2. ዓመታዊ እና የመታሰቢያ ክበራ (Calendrical and Commumorial rites)

እነዚህ ክበራዎች የወቅቶችን መፈራረቅ ጠብቀው የሚከበሩ ናቸው። በዚህ ክበራ ውስጥ የዘመን መለወጫ፣ ዓመታዊ በዓላት፣ የአየር ንብረት ሲለወጥ፣ ወዘተ. የሚከበሩ ክበራዎች ይካተታሉ። *Bell (1997: 239). ይህን አምልኮ* "Calendrical rites give socially meaningful definitions to the passage of time, creating an ever-renewing cycle of days, months, and years. ...," በማለት ይገልጻሉ።

እነዚህ ክበራዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚከበሩ ስለሆኑ ከተቆረጠላቸው ቀን ወይም ወር ላይ የማያልፉ ናቸው። ጊዜያቸውን የሚወስኑትም በዓሉን የሚያምኑና የሚያከብሩት የማህበረሰቡ አባላት ናቸው። በአሪ ብሔረሰብም በአዝመራ ጊዜ፣ በመኸር ጊዜ እና በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የሚፈጸሙት የአምልኮ ክዋኔዎች ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

### 2.3.1.3. የመንፃት አምልኮ (Rites of affliction)

የዚህ አይነት ክብረ በዓል ሰዎች በበሽታ በተለከፉ ጊዜ እና በእምነታቸው የተከለከሉ ድርጊቶችን በፈጸሙ ጊዜ ከበሽታቸው ለመዳንና ከአምላካቸው ምህረት ለማግኘት ሲሉ የሚፈጽሙት አምልኮ ነው። በዚህም የተለያዩ መስዋዕቶችን በማቅረብ፣ ጸሎት በማድረግና በመስገድ ይለማመናሉ።

> Purification is a major theme with in rites of affliction, although it can be understood in a variety of ways. It can involve freeing a person from demonic possession, disease, sin, or the karmic consequences of past lives. (Bell 1997:118).

በዚህ የክብረ በዓል አይነት ውስጥ ከወሊድ ጋር ተያይዞ የሚከሰት የመንጻት ስርዓትም ይካተታል። ለምሳሌ በቻይና አንዲት ወላድ እናት ከመውለዷ በፊት ጀምሮ ለብቻዋ የምትኖርበት ጎጆ ይዘጋጃል። ይህም በምትወልድበት ጊዜ የሚፈሳት ደም፣ ፈሳሽ እና እንግዴ ልጅ ቤተሰብን

ያረክሳል ተብሎ ስለሚታመን ነው። የአሪ ብሔረሰብም አንጀት እያነበበ የግልና የቤተሰብ ሕይወትን ከተፈጥሮ አደጋዎችና ከኃጢአት ለማዳን የማንጻት (ጭልሺ) አምልኮ ይፈጽማል።

### 2.3.1.4 የመስዋዕት/ምስጋና ክበራ (Rites of exchange and communion)

ይህ የአምልኮ ዓይነት አንድ ነገር በስኬት ሲፈጸም መስዋዕት የማቅረቢያና የማመስገኛ ስነ-ስርዓትን የያዘ ነው። ከላይ የተገለጸው የማንፃት አምልኮም ውጤቱ በዚህ አምልኮ ውስጥ የሚካተትባቸው አጋጣሚዎች አሉ። በመስዋዕትነት የሚቀርቡት ነገሮች ደም፣ ፀሎት አሊያም የተለያዩ ቁሳዊ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

> Among the best-known examples of religious rituals are those in which people make offerings to a god or gods with the practical and straightforward expectation of receiving something in return–whether it be as concrete as a good harvest and a long life or as abstract as grace and redemption.
>
> ... Such rites call attention to an order in these relationships that all depend upon for their well-being.Offerings to ancestors, gifts from the spirits, or sacrifices in which the object and the god become one all create a profound sense of cosmic interrelatedness and of human responsibility for more than one's own immediate needs. (Bell 1997□109).

እነዚህ መስዋዕቶች ከአምላክ ጋር ያለን ግንኙነት ለማጠናከር የሚዘጋጁ ናቸው። የእምነቱ ተከታዮች ከሚወለዱ የመጀመሪያ እንስሳት ወይም ከሚሰበሰብ ምርት የመጀመሪያውን በመስጠት አምልኮውን ይፈጽማሉ። ይህ የአምልኮ ክዋኔ በዚህ ጥናት ውስጥ ለበሪ የሚሰጡ የተለያዩ ስጦታዎችንም ያካትታል።

## 2.4. ክዋኔ

ክዋኔ ውበታዊ ተግባር ነው፤ የፎክሎር አፈጻጸም ነው፤ በፎክሎር ውስጥ ያለ ውበታዊ ክስተትም ነው። ክዋኔ ከዋኙን፣ የአከዋወን ስርዓትን፣ ታዳሚን እና መቼትን በአንድ ላይ የክዋኔ አቀራረብን እድገት ማሳደግ በሚችሉበት ሁኔታ አጣምሮ ይይዛል (Bauman 1976:4-5)። አምልኮ ያለ ተግባር እንደማይሆን Rappaport (*1999:25)* እንደሚከተለው ያፀናሉ።

---If there is no performance, there is no ritual; performance itself is an aspect of that which is performed. The medium is part of the message; more precisely, it is a metamessage about whatever is encoded in the ritual.

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ ያለ ክዋኔ የትኛውንም የፎክሎር ጥናት በማካሄድ የፎክሎር ሀብቱን መሰረታዊ ይዘት ማግኘትና መረዳት ያስቸግራል፡፡ በተለይም በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠበትን "እምነት" ለማጥናት የአማኞቹን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መመርመር ግድ ይሆናል፡፡

ክዋኔ እንደየባህሉ አይነትና ይዘት የተለያየ አቀራረብ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ክዋኔ የሚቀርብበትና የሚተረጎምበት ሁኔታ የተለያየ ይሁን እንጂ ዋናው ጉዳይ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውናም ሊኖረው እንደማይችል የመስኩ ምሁራን ይጠቁማሉ (Finnegan 1977, Rappaport 1999)፡፡ በክዋኔ-ተኮር አቀራረብ አንድን ክዋኔ ለማጥናት/ለመረዳት የተለያዩ ነጥቦችን ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህም ከዋኙ፣ አድማጩ/ተደራሲው፣ ለክዋኔ የሚቀርበው ጉዳይ፣ መቼቱ፣ መልዕክቱ፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተሉ፣ ደንቡ እና የአድማጩ ምላሽ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

## 2.5 አውድ

አውድ በአንድ ሁነት (event) ውስጥ የሚገኝ አጠቃላይ ድባብን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም አውድ የክዋኔን ቦታ፣ ጊዜ፣ እና የተለያዩ እምነታዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው፡፡ ማርታ እና ማርቲን (2005:137) አውድን "Context refers to anything and everything that surrounds a text and performance" በማለት ይገልጹታል፡፡

ከፎክሎር ምሁራን አንዱ የሆኑት ሪቻርድ ቦውማን አንድ የፎክሎር ክዋኔ ቢያንስ ሁለት አውዶች ይኖሩታል ይላሉ፡፡ እነዚህም ባህላዊና ማህበራዊ አውድ በመባል ይመደባሉ፡፡ ባህላዊ አውድ የአንድ ቡድን ብቻ የሆነ የግንኙነት/የመግባቢያ ደንብ ሲሆን ማህበራዊ አውድ ደግሞ ከአንድ ቡድን አልፎ ብዙዎችን ሊያሳትፍ የሚችል አውድ በመሆኑ ይህን አውድ ለመረዳት የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ መሰረት፣ ፖለቲካዊ መዋቅሮች እና ማህበራዊ ባህሪያትን መረዳት ይገባል ይላሉ፡፡ እንደ ክዋኔ ተኮር አቀራረብ የትኛውንም ፎክሎር መረዳትና መተርጎም የሚቻለው በዚያው በማህበረሰቡ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ውስጥ ሆኖ መሆን እንዳለበት ይመክራል፡፡

ከመስክ ስራ ያገኘነውን መረጃም በእነዚህ ሁለት የአውድ አይነቶች መድበን መተንተን እንዳለብን ምሁራኑ ይመክራሉ (Bauman 1983፡363-7, Ben Amos 1992፡209)፡፡

### 2.5.1 ባህላዊ አውድ

ይህ የአውድ አይነት ለፎክሎር ቅንጣቱ በየባህሉ የሚሰጠውን ትርጉም እና ትዕምርታዊ ግንኙነቶችን ይመለከታል፡፡ በውስጡም ሶስት ንዑሳን አውዶችን ያቅፋል፡፡

#### 2.5.1.1 የትርጉም አውድ

ይህ አውድ የፎክሎርን ባህላዊ አውድ ለመረዳት ወሳኝ ነው፡፡ አንድ የፎክሎር አይነት ከይዘት፣ ከትርጉም እና ከምንነት አንጻር ያለው አንድምታ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል፡፡ የአንድን ፎክሎር ባህላዊ ትርጉም ለማወቅ በራሱ በባህሉ ውስጥ ባሉ የአተረጓጎም እይታዎች ላይ መመርኮዝ ያስፈልጋል፡፡ የባህሉ ባለቤቶች በፎክሎራቸው ውስጥ የሕይወት መስመራቸው በምን መልኩ እንደተወከለ፣ እንዴት እንደተላለፈ እና ምን ምን እምነቶችና እሴቶች እንደተዛመዱበት ይመረምራል፡፡ በፎክሎር አይነቱ ውስጥ መንስኤና ውጤት፣ ተነሳሽነትና ምርጫ፣ የአከዋወን ስልቶች፣ ትዕምርታዊና ዘይቤያዊ አገላለጾች እንዴት እንደተገለጹበት ያጤናል፡፡ ለዚህም ልምዱ ያላቸው ፎክሎረኞች ባህላዊ ትርጉምን ከባህሉ ባለቤቶች በቀጥታ ይወስዳሉ (Bauman 1983፡363)፡፡

በአሪ ብሔረሰብ ዘንድ የሚፈጸመው የበሪ ስርዓተ-አምልኮም የተለያዩ ባህላዊ ትርጉም ያላቸው ክዋኔዎች አሉት፡፡ ለምሳሌ አንዲት አራስ ሴት ከባሏ እግር ስር ስትሾልክ በወሊድ ጊዜ ከነበራት ደምና ፈሳሽ "ነጻች" ማለት እንደሆነ ብሔረሰቡ ይተረጉማል፡፡ በበግ አንጀት ንባብ ጊዜም እያንዳንዱ የአንጀት ውስጥ ደም እንቅስቃሴ ባህላዊ ትርጉም አላቸው፡፡

#### 2.5.1.2 ተቋማዊ አውድ

ይህ አውድ አንድ የፎክሎር ቅንጣት በተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ያለውን አውድ ይመለከታል፡፡ "ተቋማት" የሚለው ቃል ፖለቲካን፣ ሃይማኖትን፣ ኢኮኖሚን፣ ቡድንን፣ ጎረቤትን እና ለተለያዩ ጉዳዮች በአንድ ላይ የሚሰበሰቡ ሰዎችን ይገልጻል፡፡ እነዚህን ተቋማት አንድ

የፎክሎር ቅንጣት በምን እንዴት ያገናኛቸዋል? በየትኛው ባህል ውስጥ ይገኛል? እንዴትስ ያገለግላል? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ፎክሎሩ በሚገኝበት ተቋም እና በተቋሙ ውስጥ በሚሰጠው ጥቅም ላይ ማተኮር ያስፈልጋል (Bauman 1983፡364)።

የምባ አሪ የሚከተለው የበሪ ስርዓተ-አምልኮ ወንጀልን በመቀነስ፣ ስነ-ምግባርን በማስተማር እና ኢኮኖሚን በመጠበቅና በማሳደግ ረገድ ለፖለቲካዊ አሰራር፣ ለሃይማኖታዊ አስተምህሮ እና ለማህበራዊ ግንኙነቶች የጋራ አገልግሎት ይሰጣል።

### 2.5.1.3 ተግባቦታዊ አውድ

ይህ ባህላዊ አውድ አንዱ የፎክሎር ቅንጣት ከሌላው ቅንጣት ጋር ያለውን ዝምድና ይመለከታል። ለምሳሌ የበሪ ስርዓተ-አምልኮ ከስነ ቃል፣ ከቁሳዊ ባህል፣ ከትውን ጥበባት እና ከመሳሰሉት ጋር በምን እንደሚጣመር በመመርመር የሚገኝ አውድ ነው። በበሪ እምነት ጊዜ የተለያዩ ጸሎቶች፣ ልመናዎች፣ ቁሳዊ መስዋዕቶች፣ ወዘተ. የሚቀርቡ ሲሆን እምነቱ ከእነዚህ ቃላዊ እና ቁሳዊ ፎክሎር ጋር ያለውን ግንኙነት የምናይበት ነው።

## 2.5.2 ማህበራዊ አውድ

### 2.5.2.1 ማህበራዊ መሰረት

ይህ አውድ ከፎክሎሩ ባለቤቶች ማንነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን አውድ ያጤናል። የፎክሎሩን አውድ ለማጥናት ማህበረሰቡን ወይም ቡድኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ስለ ቡድን የተለያዩ ፎክሎርስቶች የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶቹ ቡድን (ፎክ) የሚባሉት “ገበሬዎች ናቸው” ሲሉ በሌላው ወገን ደግሞ “አንድን ነገር የጋራ አድርገው የሚጠቀሙ ማናቸውም ቡድኖች ናቸው” በማለት ይገልጻሉ። ነገር ግን የፎክሎር ትምህርት እየተስፋፋ በመምጣቱ ቡድንን በጎሳ፣ በዘር፣ በስራ እና በእድሜ ለይቶ ከመከፋፈል በላይ በግለሰብ እና በቤተሰብ ደረጃም ቡድን ሊኖር እንደሚችል እየታመነ መጥቷል። ስለዚህም የፎክሎሩን አውድ ለመረዳት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማንነት ማወቅ ግድ ይሆናል።

### 2.5.2.2 ግለሰባዊ አውድ

ፎክሎር በቡድን እንደሚገለጸው ሁሉ በግለሰብም ይገለጻል፡፡ ፎክሎሩ በግለ-ሰብ ሕይወት ውስጥ የሚይዘው ቦታ፣ ለግለ-ሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ ግለ-ሰቡ ለፎክሎሩ የሚሰጠው ትርጉም እና ከሌሎች ግለ-ሰቦች/ቡድኖች ጋር የተዋቀረበት ሁኔታ በዚህ አውድ ይጠናል (Bauman 1983፡ 365)፡፡ በአሪ ብሔረሰብም የበሪ እምነት ከቡድናዊነት ባለፈ በግለ-ሰብ ሕይወት በሰፊው ትርጉም ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ አንድ ዛፍ ለአንዱ በሪን የሚያመልክበት እጅግ የተከበረ የአምልኮ አድባር ሲሆን ለሌላው ግን ለማገዶ፣ ለጥላ፣ ለተለያዩ የቤት ቁሳቁስ መስሪያ የሚውል የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

### 2.5.2.3 ሁኔታዊ አውድ

ይህ አውድ የፎክሎር ቅንጣቱን ወቅታዊ ትርጉም ለማወቅ የሚያግዝና በአሁኑ ጊዜ ፎክሎርስቶች በስፋት የሚጠቀሙበት አውድ ነው፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ የሚጠናው የፎክሎር ቅንጣት አከዋወኑና አወቃቀሩ ወቅታዊ/ሁኔታዊ ነው፡፡ ይህ አውድ የፎክሎሩን ተጨባጭ መቼት፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና፣ ባህላዊ የክዋኔ ህጎችን፣ የተግባቦትንና የአተረጓጎም ደንቦችን፣ የተግባራትን ቅደም ተከተል እና የሁኔታውን ፍሰት ለመረዳት ያስችላል፡፡

በአንድ የፎክሎር ቅንጣት ውስጥ የተደራጀ፣ ፍሰታዊ እና የተለመደ አከዋወን ወይም አውድ ሊኖር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ ለውጥ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሚከሰቱትም ለክዋኔ ከሚመረጠው ቅንጣት (item)፣ ለመከወን ከምንጠቀመው ስልት፣ ከተፈጠረው አጋጣሚያዊ ጉዳይ እና ከሁኔታው ጊዜያዊ መዋቅር አንጻር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ጥቅል ባህላዊ ትርጉም በተጨማሪ ሌላ የአተረጓጎም አቅጣጫን አጥኚው እንዲመራመር ያስችለዋል፡፡ አጥኚው ሁኔታዊ አውድን ለማግኘት ራሱንም ሆነ ቡድኑን መጠየቅ ያለበት እየተከናወነ ያለው የፎክሎር ቅንጣት አሁን ባለው ሁኔታ ውስጥ ምን ማለት ነው? በዚህ በአስቸኳይ ዓላማ ውስጥ ምን ይፈይዳል? ለማህበረሰቡ/ለቡድኑ ተግባቦት እንዴት ያገለግላል? የሚሉትን ጉዳዮች ነው (Bauman 1983፡ 365-6)፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ አካባቢ የሆነው የደቡብ አሪ ወረዳ አጠቃላይ ዳራ፣ የአሪ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የአሪ ህዝብ ማህበራዊ መዋቅር፣ የለቅሶ ስርዓት፣ ጋብቻ፣ አመጋገብ እና ባህላዊ ጭፈራ ተገልጸዋል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የተገለጹበት ምክንያትም ጥናቱ የተካሄደበትን ብሔረሰብ ከማሳወቅ በተጨማሪ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተያያዥ የሆኑ እሴቶችን አስቀድሞ ለማስገንዘብ ስለሚረዱ ነው፡፡

## 3.1. የደቡብ አሪ ወረዳ

የደቡብ አሪ ወረዳ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በደቡብ ኦሞ ዞን ከሚገኙ ስምንት ወረዳዎች አንዱ ሲሆን አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱም 1,492.60 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ከወረዳ ው ፋይናንስና ኢኮኖ ሚ ልማት ጽ /ቤት የ ልማት መረጃ ማሰባሰ ብና ማሰራጨት የሥራ ሂደት በተገኘው መረጃና ካርታ መሰረት ወረዳውን በስተሰሜን ሰሜን አሪ ወረዳ፤ በስተደቡብ በና ፀማይ ወረዳ፤ በስተምእራብ ሣላማጎ ወረዳ እና በስተምስራቅ ማሌ ወረዳ ያዋስኑታል፡፡ ወረዳው በደቡባዊ ክፍል $4^0$ $26^{l}$ ሰሜናዊ ላቲትዩድ እና $35^047^{l}$ እስከ $36^040^{l}$ ሎንግትዩድ ኬንትሮስ መስመር ዞን ውስጥ ሲገኝ ከፍታውም ከባህር ወለል በላይ ከ 1,200-3,418 ሜትር ይደርሳል *(ከደ/አ/ዞ/ግ/መ/ስብል ጥበቃ የስራ ሂደት ዓመታዊ ሪፖርት፣ 2003 ዓ.ም.)፡፡*

ወረዳው በአጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ ካሉት ስምንት ወረዳዎች ስድስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በህዝብ ቁጥር እድገት አንደኛ ደረጃን ይዟል፡፡ በ1999 ዓ.ም. የተካሄደውን ሀገር አቀፍ የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሠረት በማድረግ በ2002 ዓ.ም. የወረዳው አጠቃላይ ህዝብ ብዛት 209,047 ሲሆን ይህም ከዞኑ ጠቅላላ የህዝብ ብዛት አንጻር 67.72% እንደሆነ የወረዳው ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ዕድገትና ትራንስፖርሜሽን ዕቅድ የሥራ ሂደት መረጃ ያመለክታል፡፡ የሥራ ሂደቱ አስተባባሪ አቶ እንዳሻው ከማይ በሰጡኝ መረጃ የ1999 ዓ.ም የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤትን መሠረት በማድረግ በየዓመቱ 2.9% ዕድገት ሲሰላ በዘንድሮው 2004 ዓ.ም. በከተማ 12,348 እና በገጠር 208,999 በድምሩ 221,347 ህዝቦች እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ በፆታ ሲለዩም

ወንድ 108,253 እና ሴት 113,094 ሲሆን ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙትም ሴቶችና አምራች ወጣቶች ናቸው።

የደቡብ አሪ ወረዳ ዋና ከተማ "ጋዘር" ሲሆን ከክልሉ ዋና ከተማ ከሀዋሳ በ 542 ኪ.ሜ.፤ ከዞኑ ዋና ከተማ ጂንካ በ17 ኪ.ሜ.፣ ከወረዳው ቅርብ ቀበሌ (አይዳ ቀበሌ) በ 1 ኪ.ሜ. እና ከወረዳው ሩቅ ቀበሌ (ሸንጋማ አርኪ) በ 58 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። ሦስቱንም የአየር ንብረት (ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላ) የያዘ ሲሆን ቆላማው 10%፣ ወይና ደጋው 70% እና ደጋው 20% ይሸፍናል። በወረዳው የዝናብ መጠን ዝቅተኛ 800 ሚ.ሜ.፤ ከፍተኛ እስከ 1600 ሚ.ሜ. እንዲሁም በአማካይ 1200 ሚ.ሜ. ሆኖ ተመዝግቧል *(ከደ/አ/ወ እቅድና ግምገማ የስራ ሂደት ዓመታዊ እቅድ፣ 2004 ዓ.ም.)።*

ወረዳው ተራራማ ቦታዎች ቢበዙበትም ለሰብል፣ ለእርሻ፣ ለደንና ቁጥቋጦ እንዲሁም ለግጦሽ የሚሆን አመቺ የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት አለው። ከመሬቱ ለምነት የተነሳም አብዛኛው የወረዳው ነዋሪ የሚተዳደረው በግብርና ሥራ ነው። በወረዳው ከሚመረቱ የግብርና ውጤቶች ውስጥ ከእህል በቆሎ፣ማሽላ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ቦሎቄ/አደንጓሬ፣ ምስር፣ ሱፍ፣ ከስራስር ስኳር ድንች፣ ድቡልቡል ድንች፣ ሀረግ ቦዬ፣ ጎደሬ፤ እንሰት፣ ቀይ ስር፣ ካሮት፣ እንጨት ቦዬ... ወዘተ. ከፍራፍሬ ሁሉም የፍራፍሬ አይነቶች ይገኙበታል። ከእንስሳትም የቀንድ ከብቶችን ጨምሮ ከግመል በስተቀር ሁሉም የጋማ ከብቶች ይረቡበታል። መሬቱ እጅግ ለም ከመሆኑና ግብርና ዋነኛ ተግባራቸው ከመሆኑ የተነሳ ከተፈጥሮ ደኖች በስተቀር የደን ልማት አይዘወተርም *(ከደ/አ/ዞ/ግ/መ/ሰብል ጥበቃ የስራ ሂደት ዓመታዊ ሪፖርት፣ 2003 ዓ.ም.)።*

በቱሪዝም መስህብነትም የተመዘገቡት የወንዞች ዋሻዎች ናቸው። በዚህም መሠረት በወረዳው አራት የወንዝ ዋሻዎች ሲኖሩ እነዚህም ሻቻ (አይዳመር)፣ ቦንቢ (ቶልታ)፣ ዞብናንት (ዞምባ) እና ማኪ (ቶልታ አከባቢ) ዋሻ ተብለው ይጠራሉ። ከነዚህ ዋሻዎች በተጨማሪ የተለያዩ ፏፏቴዎችና ሣላማኪ ፍልውሃም ከወረዳው የቱሪስት መስህቦች ይመደባሉ*(የደ/አ/ወ/ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት የልማት መረጃ ማሰባሰብና ማሰራጨት የስራ ሂደት)።*

ወረዳው አጠቃላይ 48 ቀበሌዎችና 3 ታዳጊ ማዘጋጃ ቤቶች ሲኖሩት ከነዚህም አብዛኞቹ ቀበሌዎች ከግብርና ሥራ በተጨማሪ በቀርከሃና በቡና ይታወቃሉ። የቀርከሃ ስራ በዘመናዊ ባይሆንም በባህላዊው አሠራር ለበርካታ አገልግሎቶች (ለቤት ሥራ፣ ለበር መዝጊያ፣ ለወንፊት፣ ለቃሬዛ፣ ለሳጠራ፣ ለአጥር፣ ለሙዚቃ መሳሪያነት፣ ለመመገቢያነት፣ ወዘተ) ይውላል። የወረዳው

የኢኮኖሚ ምንጭ የሆኑት ቡና፣ ኮረሪማ እና ሰሊጥ ይመረታሉ። ከግብርና በተጨማሪ የከብት እርባታ፣ የሸክላ ሥራ እና ንግድ እንደየቅደም ተከተላቸው የብሔረሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት ናቸው። የግብርና ሥራው የሚከናወነው ያለ አንዳች ዘመናዊ መሳሪያ ሲሆን ህዝቡ ከሚገለገልባቸው ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎች በይራ፣ ጎሻ፣ ዋሲ፣ እና የበሬ ዕቃዎች ዋነኞቹ ናቸው።

## 3.2. የአሪ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙን የአሪ ህዝብ ምንጩ ከሱዳን እንደሆነ ነው። በተለያዩ ጊዜያት በብሔረሰቡ ማንነትና ቋንቋ ላይ ያተኮሩ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የአሪ ህዝብ ከሱዳን የፈለሰ መሆኑን እና ቋንቋውም ከማዕከላዊ ሱዳን ጋር እንደሚመሳሰል ለማረጋገጥ ሲዳዱ ይስተዋላል። "በተለያዩ ጊዜያት ሱዳኖች ወደ ኢትዮጵያ ፈልሰዋል።...ቅመ ኒሎዎች ከኦሞአዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በመዳቀል አሪን፣ ባስከቶን፣ ድሜን እና ጊሜራ ማጂ ነገዶችን መሠረቱ። ..." (Levin 1974፡31)።

ከላይ እንደተገለጸው የሱዳን ህዝብ በፍልሰት ወደ ኢትዮጵያ በመግባት እንደየ አመጣጡና አሰፋፈሩ የተለያዩ ነገዶችን ሲመሰርት አንደኛው "አሪ" ተብሎ መሰየሙንና ቋንቋውም ከኦሞቲክ ቋንቋዎች ጋር መዳቀሉን እንረዳለን። ይህ ብቻም ሳይሆን የእነዚህ ነገዶች ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረት ሥራሥርን በማልማት ላይ የተመሠረተ እንደሆነም ተጠቁሟል።

ቋንቋውን በተ መለከተም በምስራቅ ኦሞ አዊ ቋንቋዎች ላ ይ ጥናት ያደረጉት ምሁ ር (Bender 2000) ከማዕከላዊ ሱዳን ቋንቋ ጋር የሚመሳሰልና አብዛኛዎቹን ቃላትም ከዚያው አካባቢ የተዋሳቸው መሆኑን ጽፈዋል። ገብሬ ይንትሶ ለሁለተኛ ዲግሪው ማሟያ ባቀረበው ጽሑፍ ላይ ስለ አሪ ህዝብ አመጣጥ ሲገልጽ ከላይ የቀረቡትን ምሁራን (Fleming 1973፡263 Levin (1974፡30-31) ሃሳብ በሚቃረን መልኩ የአሪ ህዝብ ከማዕከላዊ አፍሪካ (ከሱዳን) ወጥቶ ከኦሞቲክ ጋር እንዳልተቀላቀለ ጠቁሟል። የገብሬ መረጃ አቀባዮችም የአሪ ህዝብ ከሱዳን ወይም ከማዕከላዊ አፍሪካ ሳይሆን ከዚያው ከኦሞቲክ ህዝቦች (በና፣ ሀመር፣ ጎፋ፣...) መካከል ፈልሶ በመምጣት እንደተደራጀ ገልፀዋል (Gebre 1995፡ 12-13)።

እነዚህ ምሁራን የቋንቋውን መመሳሰልና የቃላት ተውሶን እንዲሁም የህዝቡን የኢኮኖሚ መሠረት መመሳሰል ዋነኛ ማስረጃ አድርገው ያቀረቡት መረጃ መላ ምታዊ እንደሆነ ቃለ

መጠይቅ ያደረግሁላቸው የብሔረሰቡ አዛውንት አቶ ግንጀሎ ሀቅዳኪ[6] የሰጡኝ አስተያየት ያመለክታል፡፡

> በእርግጥ እግዜር ሰውን ሲፈጥር አንድ ወንድ አንዲት ሴት ብቻ አድርጎ ነበር፡፡ ስለሆነም በአለም ያለነው ሁላችንም ከአንድ ዘር ነው የተገኘነው፡፡ ይህን እውነታ ለማሳመን ካልሆነ በስተቀር የአሪ ህዝብ ምንጩ እዚሁ አሪ ምድር ላይ ነው፡፡ ከየትም አልመጣም፡፡ ቋንቋውም ቢሆን በትዕቢት የተሞሉ ቅመ-አያቶቻችን (ባቢሎናዊያን) እግዜርን ለመድረስ ረጅም ቤት መስራት በጀመሩ ጊዜ እግዜር ቋንቋቸውን ደበላለቀ፡፡ በዚህም የተነሳ የሁሉም ቋንቋ የተለያየ ሆነ ፡፡ የአሪ ህዝብ ቋንቋም ከዚህ ታሪክ ውጭ አይደለም፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2004 ዓ.ም.)

ከዚህ የምንገነዘበው የአሪ ህዝብ ከሱዳንም ሆነ ከየት የፈለሰ ሳይሆን በሀገሩ ተወላጅ መሆኑን እና ቋንቋውም እንደማንኛውም ቋንቋ ራሱን የቻለ እንደሆነ ነው፡፡ ስለሆነም በቋንቋው ከሱዳን እና ከምስራቅ ኦሞአዊ ቋንቋዎች ጋር መመሳሰሉ ከጉርብትናና ከቃላት መዋዋስ የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ የአሪ ህዝብ ቋንቋ "አራፍ" (አሪኛ) ሲሆን የሚጠቀመው ፊደልም የሳባኛ ፊደላትን ነው፡፡

የአሪ ህዝብ አመጣጥን በተመለከተ የተፃፉ ፅሑፎች እና የብሔረሰቡ አባላት ያላቸው አስተያየት አይገናኙም፡፡ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ጊዜ (ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም.) ይህን ጥያቄ ባቀረብኩላቸው ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ከየትም እንዳልመጡና ከዚሁ ከአገራቸው እንደተፈጠሩ መልስ ሰጥተውኛል፡፡ በእርግጥ ፍልሰት በአካባቢያቸው እንዳለና ፍልሰቱ ደግሞ በግለ ሰብ ደረጃ እንጂ በነገድና በዘር እንዳልሆነም መስክረዋል፡፡

የአሪ ህዝብ በአሰፋፈሩ በአንድ አካባቢ ብቻ የተገደበ ሳይሆን በደቡብ ኦሞ እና በሰሜን ኦሞ ዞን ወረዳዎችና አውራጃዎች የተበታተነ ነው፡፡ ሆኖም ግን የአሪ ህዝብ በብዛት የሰፈረበትና ሌሎች 15 ብሔረሰቦች የሚገኙበት ደቡብ ኦሞ ዞን በድሮው "ባኮ ጋዘር ወረዳ" በአዲሱ ደግሞ "ደቡብ አሪ ወረዳ እና ሰሜን አሪ ወረዳ" ውስጥ ነው፡፡ የደቡብ አሪ ወረዳ ሙሉ በሙሉ የአሪ ህዝብ የሰፈረበት ቢሆንም በከተሞች አካባቢ የአማራ፣ የባስኬቶ፣ የወላይታ፣ የጋሞ፣ የጎፋ፣ የማሌ፣ ወዘተ. ብሔረሰቦችም አብረው ይኖራሉ፡፡

---

[6] ከ 110 ዓመት እድሜ በላይ እድሜ እንዳላቸው የሚናገሩ፣ የስድስት ልጆች አባት፣ ከምባመር አካባቢ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን በቀዳሚነት የተቀሳቀሱ፣ የቆሬትር ንዑስ ቀበሌ ነዋሪ አዛውንት ናቸው፡፡ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን ከመቀሳቀሳቸው በፊት የበሪ ስርዓተ-አምልኮን አክርረው ይፈጽሙ የነበሩና ዛሬ ሳይ ታሪካቸውን በዝርዝር መናገር የሚችሉ ጠንካራ ታሪክ አዋቂም ናቸው፡፡ ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች አንዱ ናቸው፡፡

## 3.3. የአሪ ህዝብ ማህበራዊ መዋቅር

የአሪ ህዝብ እስከ ዘውዳዊው አገዛዝ ስርዓት መጨረሻ ድረስ የፖለቲካም የሃይማኖትም ገዥና መሪ ተብለው በሚታመኑ ግለሰቦች ሥር ይተዳደር ነበር፡፡ እነዚህም ግለሰቦች "ባቢ" (ባላባት) ተብለው የሚጠሩ ሲሆን በአጠቃላይ የአሪን ህዝብ ዘጠኝ የሚደርሱ ባላባቶች ተከፋፍለው ያስተዳድራሉ፡፡ የእያንዳንዱ ባላባት ስም የሚጠራው ከግለሰባዊ ስሙ በተጨማሪ በሚገዛበት አካባቢም ስም ነው፡፡ ዘጠኙ የባላባት ግዛቶች ቤያ (ቢዮ)፣ምባ (ምባመር)፣ ሲዳ (ሲዶ)፣ ሻንግማ/ላይዳ (ሸንጋማ)፣ ባካ (ባኮ)፣ ጋይል (ገሊላ)፣ ባርግድ፣ ሴይኪ እና ኩሬ በመባል ይጠራሉ፡ ፡ እነዚህ ስሞች ለባላባቶች መለያ መጠሪያ ብቻ ሳይሆኑ በየግዛቱ ለሚገኙ ሕብረተሰቦች በሙሉ መለያ መጠሪያ ናቸው፡፡ ስለሆነም ባላባቱ ሲዳ ባብ (የሲዳ ባላባት)፣ ምባ ባብ (የምባ ባላባት)፣ ወዘተ እንደሚባለው ሁሉ ህዝቡም ሲዳ ኤድ (የሲዳ ሰው)፣ ምባ ኤድ (የምባ ሰው)፣ ... እየተባለ ይጠራል (Gebre 1995)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው እነዚህ ባላባቶች የየአካባቢያቸውን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች በበላይነት ሲመሩ ኖረዋል፡፡ ያልተፃፉ ቢሆኑም ህጎችና ደንቦችን ያወጣሉ፤ ያስፈፅማሉ፡፡ የስልጣን ተዋረድም አላቸው፡፡ ዋናው መሪ ባቢ (ባላባት) ሲሆን ጎድሚ እና ጋና (Ganna) እንደየቅደም ተከተላቸው የሀገረ-ሰባዊ እምነት ደንብ ፈጻሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ጠለቅ ባለ መረጃ በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ከአስተዳደራዊው መዋቅር በተጨማሪ የአሪ ህዝብ በሁለት ዘሮችና በተለያዩ ማታዎች ተከፋፍሎ የማህበራዊ ደረጃ ልዩነትም ፈጥሮ ይኖራል፡፡ ይህ ልዩነትም የሚመሠረተው "ዘር" በሚባለው መስፈርት ሲሆን በበላይነትና በበታችነት የተፈረጁ ዘሮች አሉ፡፡ በጥቅሉ የበላይ የሆኑት "ቻንሣ" የሚባሉ ሲሆን የበታች የሆኑት ደግሞ "ማና" (Mana) ተብለው ይጠራሉ፡፡ በሁለቱ ግንድ ዘሮች ውስጥም የተለያዩ ማታዎች በመኖራቸው የበታችነትና የበላይነቱ ደረጃ አለ፡ ፡ ይህ ልዩነትም በጋብቻ ጊዜ በመስፈርትነት ያገለግላል፡፡ አንዱ ማታ ከተመሳሳይ ማታ ጋር መጋባት አይችልም፡፡ "ማና" ተብለው የተፈረጁት ሁለገብ ቢሆኑም በዋናነት በሸክላ ስራ፣ በእንጨት ስራ፣ በብረት ስራ(ቀጥቃጭ) የሚተዳደሩ ሲሆን "ቻንሣ" የተባሉት ደግሞ በእርሻ፣ በከብት እርባታ፣ በንግድ፣ ወዘተ. የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ከላይ የተገለጸውን ሥልጣን የሚያገኙትም ከዚሁ የዘር ግንድ ውስጥ ነው፡፡ *(ቃለ መጠይቅ፣ አቶ መሐመድ ቡርቻ፣ 8/05/2004)*

## 3.4. ጋብቻ (ቴይሚ/ኤንሣ)

በአሪ ብሔረሰብ ጋብቻ በተጋቢዎች ስምምነትና ፍቅር ብቻ የሚከናወን ቢሆንም ባህሉ ያስቀመጠው ግዴታ (ደንብ) አለ፡፡ ይህም ተጋቢዎች ከአንድ "ማታ" መሆን የለባቸውም፡፡ ለምሳሌ "ዓመን" ከ "ዓመን" ወይም "ሸኪ" ከ "ሸኪ" ማግባት አይፈቀድም፡፡ በነገራችን ላይ ቓንሣ ከቓንሣ ማናም ከማና ጋር መጋባት የሚፈቀድ ሲሆን እነዚህ የዘር ግንዶች ግን እርስ በርሳቸው (ቓንሣ ከማና/ማና ከቓንሣ) እንዲጋቡ ክልክል ነው፡፡ ከአንድ ማታ ሆነው ቢጋቡ ዘር አይበረክትም፤ ትዳር አይፀናም፤ በሀገር ላይ እርግማን ያመጣል፤... ተብሎ ስለሚታመን ሲሆን ቓንሣ ከ ማና ቢጋቡ ደግሞ ቓንሣውን እከክ ይበላዋል፤ በትዳር ውስጥ በዘር የመናናቅ ግጭትም ይፈጠራል፤ የቓንሣው ቤተሰብም ክብሩ ይቀንሳል፤... ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ባህሉ በሚፈቅደው መንገድ ጋብቻቸውን የሚፈፅሙ ወገኖች ከጋብቻ በፊት አቅማቸው የቻለውን ያህል ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ ወንዱ ከ15 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ከአባቱ ቤት ውስጥ ማደር እንደነውር ስለሚቆጠር ትንሽ ጎጆ ሰርቶ ብቻውን ወይም ከጓደኞቹ ጋር ማደር ይጀምራል፡፡ በጎጆዋ ዙሪያ እንሰት ይተክላል፡፡ የጓሮ አትክልቶችን ያለማል፤ ከአባቱ መሬት ወስዶ እህል ይዘራል፤ ወዘተ. ሴቷም በአማካይ ከ14 ዓመት እድሜዋ ጀምሮ በምታገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ጥቃቅን የቤት ዕቃዎችን (ሲኒ፣ቡንዳይ፣ሙዕሳ፣...) እና ጌጣጌጦችን እንዲሁም የማታ ልብስ (ብርድልብስ/ጋቢ/ፎጣ) በመግዛት ትዘጋጃለች፡፡

ተጋቢዎች በሚገባ ከተጠናኑና በአገኛኝ ሰው አማካይነት የመግባባት ሂደት (ሦራ) ከጨረሱ በኋላ የጋብቻ ቀን ይቆርጣሉ፡፡ ከጋብቻ ቀን በፊት ልጂቱ ያላትን ንብረት ሁሉ ቀስ በቀስ በስውር ወደ ልጁ ቤት ትልካለች፡፡ በጋብቻው ቀንም የተቀራትን ዕቃዎችና ልብሶች እንዲሁም ኣቲ (ጉሎ) በቅል ይዛ ከጓደኞቿ ጋር ወደ ቀጠሮ ቦታ ትጓዛለች፡፡ ወንዱም ጓደኞቹን ይዞ በተጠንቀቅ ወደ ቀጠሮው ቦታ ይሄዳል፡፡ ከቦታው ሲደርሱም ልጂቱን አጅበው በሰዋራ መንገድ ወደ ልጁ ቤት ይወስዱአታል፡፡

ምሽት ሲሆንም ከቤት ውጭ ከእንሰት ቅጠል በተዘጋጀ ጎዳይ (ጎጆ) ውስጥ ሙሽሮች ጫጉላ ይገባሉ፡፡ በዚህ ጊዜም ሴት ጓደኞቻቸው የልጂቱን ልብስ በማውለቅ ይዛ የመጣችውን ኣቲ (ጉሎ) ጨፍልቀው ሰውነቷን በሙሉ ይቀባሉ፡፡ ኣቲ ከምጣድ ማሰሻነት በተጨማሪ የአሪ ልጃገረድ በጫጉላ ጊዜ ሰውነቷን በመቀባትና በመምለጭለጭ ለወንዱ አስቸጋሪ ለመሆን ትጠቀምበታለች፡፡ ያም ቢሆን ወንዱ ክብሩን ለማስጠበቅ ታግሎ በማሸነፍ ክብረ ንፅህናዋን ማግኘት ግዴታው ነው፡፡

እዚህ ላይ ለወንዱ አንድ ኃላፊነት ቢኖር ከቤተሰቦቹ ጋር በፍቅር የኖረ መሆን አለበት፡፡ በቤተሰቦቹ (አባትና እናት/ታላቅ ወንድም) ዘንድ ቅራኔ ካለበት የጫጉላ ትግሉ አይሳካለትም፡፡ ይህ ሲሆንም በማግስቱ ሌ ሊት ላይ ቤተ ሰቦቹ ተ ጠርተው ይቅርታ እንዲያደርጉለት ና ይቅ ርታ ማድረጋቸውንም በሾርቓ ውኃ ጠጥተው ግማሹን ለልጁ በመስጠት እንዲሁም በእንስት ገለባ (ዳልሚ) ሆዳቸውን ጠርገው እንዲጥሉ ይደረጋል፡፡ ቅራኔ ያደረበት ቤተሰብ ይህን ካደረገ በኋላ ያለምንም ትግል በቀላሉ እንዲገናኛት ያስችለዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ለሦስት ቀን በዚሁ በቅጠል ጎጆ ውስጥ ከቆዩ በኋላ ወደ ልጁ ቤት ይገባሉ፡፡ የልጁ ቤተሰቦችና ጎረቤቶች ምግብ ከየቤታቸው እያዘጋጁ በማምጣት ያበሉአቸዋል፡፡ ጓደኞቻቸውም ለሳምንት ያህል ያጫውቷቸዋል፡፡ ከሦስተኛው ቀን ማግስት ጀምሮ ሽማግሌዎችን በመላክ የእርቅ ሽምግልና ይከናወናል፡፡ በሽምግልናውም የተጋቢዎች የዘር ሐረግ ልዩነት፣ የልጁ ሰብዕና፣ የሥራ ተነሳሽነት፣ ወዘተ. ትኩረት ይሰጥባቸዋል፡፡ የሽምግልና ሂደቱ ሲጠናቀቅም የበግና የብር ዻክማ[7] (ኮይታ) ይፈፀምና የካሺ/ወጭሚ (የመልስ ሰርግ) ዝግጅት ይጀመራል፡፡

የዻክማ ስርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከወራት /ከአመት በኋላ የልጂቱ አባትና እናት ጎላ (ቦርዴ) በብዙ ጋኖች ጠምቀው ለልጁና ለቤተሰቦቹ የእርሻ መሳሪያዎችን በየአይነቱ ገዛዝተው/አዘጋጅተው እና ለልጂቱም የቤት ዕቃዎችን በሙሉ አሟልተው "ካሺ/ወጭሚ" ይጠራሉ፡፡ በዚህም የሁለቱም ቤተሰቦች ዘመዶችና የአካባቢው ሰዎች በሙሉ ተሰብስበው ቀንም ሌሊትም እየጨፈሩ፣ ቦርዴ እየጠጡ፣ በግ ታርዶ በእንስት (ስሩ ተቀቅሎ) እየበሉ ሁለት ቀን ከቆዩ በኋላ የተበረከተላቸውን ስጦታዎች ይዘው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ በድግሱ ጊዜም የልጂቱ አባትና እናት ልጃቸው እንድትወልድና በትዳርዋ እንድትባረክ ይባርኩዋታል፡፡ ይህ የካሺ ስርዓት እስኪፈፀም ድረስ ግን ሙሽራውና ሙሽሪት ከሙሽሪት ቤተሰቦች ጋር ፊት ለፊት እንዲገናኙና ሰላምታ እንዲለዋወጡ አይፈቀድላቸውም፡፡ እንደ ድፍረትና ንቀት ስለሚቆጠር ከቤተሰቦቿ እየሸሹ ይኖራሉ፡፡*(ቃለ መጠይቅ፡ ወ/ሮ ጋበትከን ካሚኝ[8]፣ጥር 19/2004)*

---

[7] የቃሉ ትርጉም በጋብቻ ወቅት ለሙሽሪት አባት/እናት የሚከፈል ጥሎሽ ወይም ኮይታ ማለት ሲሆን በቃሉ መጀመሪያ ላይ ያለው ሆሄ እንደ ኦሮምኛው "dh" ድምጽ ይነበብ፡፡

[8] የ 90 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ የሰባት ልጆች እናት፣ የቶቖር ንዑስ ቀበሌ ነዋሪና የዝናብ ጎድሚ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ቁልፍ መረጃ አቀባይ ናቸው፡፡

## 3.5. የለቅሶ ስርዓት (ኤፊ)

በአሪ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓትና ክብደት እንደየግለሰብ፣ እንደየሟች ሰብዕና እና እንደየባህሉ ከቦታ ቦታ የተለያየ ነው፡፡ የቀብር ስነ-ስርዓቱም እንዲሁ፡፡ የአሪ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የለቅሶ እና የቀብር ስርዓት አለው፡፡ ስርዓቱ በዕድሜ፣ በፆታ፣ እና በማህበራዊ ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በብሔረሰቡ የተለመደውንና የማይቀረውን የለቅሶ ስርዓት ቀጥለን እንመልከት፡፡

በአሪ ብሔረሰብ አንድ ሰው ቢሞት የሚፈፀመውን የለቅሶ ስርዓት ስንመለከት ሟቹ እንደሞተ በሙቅ ውሃ ታጥቦ ወዲያውኑ ከተከፈነ በኋላ ጭንቅላቱን ወደ በር በማዞር ያስተኙታል፡፡ ከዚያም ከቤት ውጭ ከፍ ብሎ የሬሳ ማስቀመጫ ቆጥ (አራት ባላዎች ላይ ርብራብ) በመስራት ሬሳውን አውጥተው ያስተኙበታል፡፡ አነስተኛ የቤት ክዳንም (ጣሪያ) ይደረግበታል፡፡ ባላባት ካልሆነ በስተቀር ሟቹ ከሞተበት ሰዓት ጀምሮ ቤተሰቦቹ ያለቅሳሉ፡፡ ሬሳው ውጭ ወጥቶ ከተቀመጠ በኋላ ሟች ከቤተሰቦቹ ጋር የነበረውን ግንኙነት (በጠብ ወይም በፍቅር) ለማጣራት አንጀት የማንበብ ስርዓት ይፈፀማል፡፡

ሟቹ ቤተሰቦቹን ያሳዘነ ወይም ቤተሰቦቹ ያሳዘኑት እንደሆነ የበግ አንጀቱ ይመሰክራል፡፡ ይህ ከታወቀም ሌላ በግ በማረድ የይቅርታ መጠየቂያ ወይም ቅሬታ በመካከላቸው ከሌለ በሕይወት ሳለ ከቤተሰቦቹ ጋር የነበረው ግንኙነት እንዲቋረጥ መለማመኛ አንጀት እንደገና ይነበባል፡፡ አንጀት የማንበቡ ስርዓት የሚቀጥለው የተፈለገውን መልስ እስኪሰጥ ድረስ ስለሆነ ከዋናው የቤተሰብ ተጠሪ ጀምሮ አቅም ያለው ቤተዘመድ በሙሉ በግ በማቅረብ ይተባበራል፡፡

መርዶ የተነገረው ቤተ-ዘመድና የአካባቢው ሰዎች ሁሉ ከየአቅጣጫው እያለቀሱ (ሴቶች ው፣ ው!ው፡ው! ብለው እየጮሁ) እና የከፈን ልብስ (ጋቢ) ቤተ-ዘመዶቹ እየያዙ ይመጣሉ፡፡ ወደ ለቅሶ ቦታ ሲኬድ ወንዶች ጦርና ጋሻ ይይዛሉ፡፡ ከለቅሶው ቦታ ሲደርሱም ከሟች ቤተሰቦች ፊትና እግር ሥር በመንበርከክ /በመደፋት  አንዳንዶቹም ጦር በመስበቅና ሴቶቹም ደረት በመድቃት፣ ፊት በመቧጨር፣ በመውደቅ፣ ወዘተ. ሀዘናቸውን ከገለጹ በኋላ ወደ ዋናው የለቅሶ ስርዓት ይዞራሉ፡፡ ዋናው ለቅሶ የሚከናወነው የእንስት ቅጠልና አገዳን ክብ በመዘርጋት ዙሪያውን ሴቶች በእንብርክክ ይከቡታል፡፡ ወንዶች ደግሞ ከሴቶች ጀርባ ይቆማሉ፡፡ ከሴቶች መካከል አንዷ መካከለኛ ክብደት ያለው እንስራ (ዳሓ) አፉን በቆዳ ወይም በእንሰት ቅርፊት በማሰር ቂጡን በመብሳት ትይዛለች፡፡ ይህ እንሰራም በአሪኛ "ዳም" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን አገልግሎቱም እንደከበሮ እየተደበደበ የለቅሶው ማድመቂያ ነው፡፡

ሴቶችም ወንዶችም ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ሴቶቹ የእንስቱን ቅጠልና አገዳ እንዲሁም ዳም እየደበደቡ ዜማ ያሰማሉ፡፡ ወንዶቹ ተራ በተራ መሃል ላይ እየገቡ ጦር እየሰበቁ ጋሻ በተረከዝ ይገጫሉ፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ፉከራ መሰል እንቅስቃሴ እያሳዩ ሲሆን ድርጊቱም "የሳ" ተብሎ ይጠራል፡፡ የሳው ለሰዓታት ከተከናወነ በኋላ አስከሬኑ ከቆጡ ወርዶ ወደ ቀብር ቦታ ይኬዳል፡፡ ከቀብሩ መልስም ንፍሮና እንሰት ይበላል፡፡ ከለቅሶ ቦታ የሚበላ ምግብ "አልቻ" ይባላል፡፡ ሟች በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ለለቅሶ የተዘጋጀው ዳስ ይነቀላል፤ የቤቱ ግቢ ይጸዳል፤ ቤተሰቦችና ቤተ-ዘመዶች (ሴቶች) ፀጉራቸውን ይላጫሉ፤ የተቀበሩትን አመድ፣ ጥላሸትና ኖራ ይታጠባሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉላቸው የአካባቢው ሴቶች እንጂ ራሳቸው አይደሉም፡፡ እንደየሟቹ ሰብእናና የዝምድና አይነት ሀዘናቸውን በዓመት የሚጨርሱም አሉ፡፡

## 3.6. አመጋገብ፣ መኝታ እና የቤት አሰራር

የአሪ ህዝብ ኑሮ የተመሠረተው በግብርና ሥራ ላይ መሆኑን ቀደም ሲል ጠቁሜያለሁ፡፡ በዚህም የተነሳ የህዝቡ ዋነኛ ምግቦች ስራስር፣ የእንስት ውጤቶች (ዋሺ)፣ አስኒ(ሀረግ ቦዬ)፣ ሀቻ አስን (ካዛባ)፣ ዛቲ (አደንጓሬ)፣ ሞሳ (ከእንስትና ከጎመን የሚሠራ) ወዘተ. ናቸው፡፡ እነዚህን ምግቦች እንስራ ውስጥ በመቀቀልና በመስራት በእንስት ቅጠል ላይ አቅርበው እናትና ልጆች በአንድ ላይ ሲመገቡ አባት (ባል) ብቻውን በሌማት (በወጪት) ቀርቦለት በር ላይ ጥግ ይዞ ይበላል፡፡ ይህ የአባት(የባል) የመመገቢያ ዕቃ በንፅህናና በጥንቃቄ ይያዛል፡፡ ቡናና ውኃም የሚጠጣባቸው ዕቃዎች (ሾርቃዎች) እንዲሁ ለብቻው አሉት፡፡ በነዚህ ዕቃዎች ላይ የሚስት የጡት ወተት ቢደርስና እንሽላሊት ቢገባባቸው/ቢነካቸው ረክሰዋልና ከቤት አውጥተው ይጥሉአቸዋል፡፡ ልጆችም እንዲመገቡባቸው አይመከርም፡፡ ከረከሱበት ጊዜ ጀምሮ "ዷቢ ሬይ(ርኩስ)" ይባላሉ፡፡ *(ቃለ መጠይቅ፡ አቶ ለጋስ ሀቻዲኪ[9]፣ ጥር 12/2004 )*

የመመገቢያ ዕቃዎቻቸውም ከእንጨትና ከቅል የተሠሩ ናቸው፡፡ ለመቀመጫነት በአብዛኛው ከዋንዛ (አሻ) እና ከብሳና (ባታ) ዛፎች የተሰሩ በርጩማዎችን ከመጠቀም በተጨማሪ መደብንና ቆዳንም ይጠቀማሉ፡፡ መኝታቸውም በመደብ፣ በቆዳ፣ በእንስት ቅጠል፣ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ችሎታው ወይም አቅሙ ያለው ዘንባባን ሰሌን ሠርቶ/አሰርቶ ይተኛበታል፡፡ የአሪ ብሔረሰብ ቤቱን የሚሰራው ደግሞ ከእንጨትና ከሣር ሲሆን የቤቱ አሠራርም መጀመሪያ ቦታ ተደልድሎ፣ እንጨትና ሽምበቆ፣ ሣር(ሚሳ) እና ላጊ (የጣሪያ ማሰሪያ የእንጨት ልጣጭ)ወዘተ.

[9] የ 95 ዓመት አድሜ ያሳቸው፣ የአምስት ልጆች አባት፣ እድሜያቸውን በበሪ አምልኮ ውስጥ ያሳለፉና ታሪክን በቀልድ እያዋዙ የሚናገሩ አዛውንት ናቸው፡፡

ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ጎላ (ቦርዶ) ተጠምቆ በደቦ ይሰራል። የቤቱ መሠረትም በመሃል ላይ በሚተከል ምሰሶ ላይ ሲሆን ግድግዳው ክብ ወይም አራት ማዕዘን ሆኖ ይቆማል። ጣሪያውም በሸምበቆና በመሪ ማገሮች ተሞልቶ በላጊው እና በሰኪ እንጨት በደረጃ በደረጃ ተደርጎ ይታሰራል፡ ፡ በመጨረሻም በሣር ይከደንና ግድግዳውም በጥሩ ሁኔታ በጭቃ ይለጠፋል። የበር መዝጊያውም ከሳንቃ ወይም ከቀርከሃ ይገጠምለታል።

## 3.7. ባህላዊ ጭፈራ (ባይዳ)

የአሪ ብሔረሰብ ሌላ መለያው ባህላዊ ጭፈራው ነው። ባህላዊ ጭፈራውን የሚያከናውነው በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲሆን ከእነዚህም ኤንሣ (ሰርግ)፣ ወጭሚ (የመልስ ሠርግ)፣ በቡና ለቀማ፣ በእምነት ሥርዓቶች፣ በሺዕሺ (በሙት ዓመት) ወዘተ. ይጠቀሳሉ። በእነዚህ አጋጣሚዎች ላይ ለጭፈራው የሚያግዛቸውን ወይሳ እና ይቻ (ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች) ይዘው በመገኘት ሲያሻቸው በቃላት አልባ ዜማ (የዬ!የዬ!...) ሲፈልጉም በዚሁ ዜማ ውስጥ የተወሰኑ ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ክብ ሰርተው እጅ ለእጅ አሊያም ወገብ ለወገብ ተያይዘው እየዞሩ ያዜማሉ። በአብዛኛው በቀላሉ ከሚያዜሙትም መካከል የሚከተለው ይጠቀሳል።

<u>አሪኛ</u>

| <u>አቀንቃኝ</u> | <u>ተቀባይ</u> |
|---|---|
| ኧ ኢበሎ ሀረ ካልመ፤ | ኧ! ኧ! |
| ኧ ኢበሎ ሀረ ሽግረ ፤ | «» |
| ኧ ኢበሎ ካልሚ ዶቕ? | «» |
| ኧ ኢበሎ ሽግር ዶቕ? | «» |

<u>አማርኛ</u>

| | |
|---|---|
| ኧ ወዳጄ የምን ጉዳይ፤ | ኧ! ኧ! |
| ኧ ወዳጄ የምን ችግር፤ | «» |
| ኧ ወዳጄ ጉዳይ አለ? | «» |
| ኧ ወዳጄ ችግር አለ? | «» |

በሌላ በኩል ደግሞ ወንዶች ወይሳ እየነፉ መሃል ላይ ሲጨፍሩ ሴቶች ክብ እንደሰሩ ዜማቸውን እያቀነቀኑ ዙሪያቸውን ይዞራሉ። ይህን ሲሰለቹም ሴቱም ወንዱም ለየብቻው ወይም አንድ ላይ ክብ ሰርተው በመቆም ሲያዜሙ መሃል ላይ አንዳንድ ሰው እየገባ ጨፍሮ ሲያበቃ ወገቡን ወደፊት ሰበር አድርጎ ለሚፈልገው ሰው ምልክት ያደርጋል። ከዚያም ይወጣል፤ ምልክት የተደረገለት ሰው ተራውን ይዞ የመጨፈር ግዴታ አለበት። እንዲህ እያደረጉ በተለያየ አይነት ጭፈራቸውንና ጨዋታቸውን ያካሂዳሉ።





የምባ አሪ በወይሳና ያለ ወይሳ ሲጨፍር

# ምዕራፍ አራት

## የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ክዋኔዎች ትንተና

የአሪ ብሔረሰብ ከሚያምንባቸው በርካታ ሀገረ-ሰባዊ እምነቶች ውስጥ እጅግ የሚዘወተረው የበሪ እምነት ነው፡፡ “በሪ” የአሪ ህዝብ ፈጣሪና ሁሉን አድራጊ አድርጎ የሚያምንባትና የሚያመልካት ሴት አማልክት ነች፡፡ በሪ ከየት እንደመጣች፣ በትክክል የት እንደምትኖር እና ብሔረሰቡም ከመቼ ጀምሮ እምነቱን እንደጀመረ የሚያስረዳ መረጃ አላገኘሁም፡፡ በሪን እያንዳንዱ ግለ-ሰብ የራሱ ብቻ አስመስሎ ቢያመልካትም በሪ የሁሉም ነች፡፡ እምነቱም የጋራ መሆኑን የምንረዳው በጋራ ጉዳይ ጊዜ አንድ ላይ ተሰብስበው ከበራ(ritual) በመፈጸማቸው ነው፡፡

በበሪ እምነት የማስተባበር ድርሻ ያላቸው የተለያዩ ግለ-ሰቦች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ዋናዎቹ “ባቢ” እና “ጎድሚ” የሚባሉት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ግለ-ሰቦች የተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ኖሮአቸው በሪን የሚያማልዱ፤ ህዝቡን የሚያስተባብሩ እና የሚያስመልኩ ናቸው፡፡ የእምነቱን ክዋኔዎች ከመተንተኔ በፊት የእነዚህን ግለ-ሰቦች ማንነት፣ ከእምነቱ ጋር ያላቸውን ትስስር እና የሥራ ድርሻቸውን እመለከታለሁ፡፡

### 4.1. ባቢ (ባላባት)


“ባቢ” ማለት “አባት” ማለት ሲሆን በምባ አሪ ባቢ በበሪ እምነት ውስጥ የእምነቱ መሪ ተደርጎ ይታመናል፡፡ ይህን መሪነት የሚያገኘውም በብሔረሰቡ ዘንድ ንጹህ/ቅዱስ ከሚባሉት ማታዎች ውስጥ ይበልጥ ከተከበረው ማታ (ጋዳ) በመመረጥ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በነበሩት የፖለቲካ ሥርዓቶች (ከደርግ አገዛዝ በፊት) ባቢ የእምነት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካም መሪ ሆኖ ይሰራ ነበር፡፡ ከጥንት ጀምሮ በዘጠኝ ባቢ የተከፈለው የአሪ ህዝብ ኢኮኖሚውን፣ ሃይማኖቱን፣ ማህበራዊ ኑሮውን የሚመራው በባቢ ትዕዛዝ ብቻ ነበር፡፡ ለመንግስት ግብር ይሰበሰብ የነበረውም በዚሁ ግለ-ሰብ አማካይነት ነበር፡፡ አቶ መሐመድ ቡርቃ ባቢዎች የነበራቸውን ሚና እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡፡

> ባቢ እንደዛሬው በአንድ ነገር ብቻ የሚታመን አልነበረም፡፡ የመንግስት አዋጅ የምንሰማው ከእሱ ነው፡፡ ግብር የምንከፍለው ለእሱ ነው፡፡ ሌላው ይቅርና የገዛ ንብረታችንን የሚቆጣጠረው እሱ ነ ው፡፡ በኂላ ደግሞ አማራ ዎች ሲ መጡ ግብር ማስከፈሉንና ንብረታችንን መቆጣጠሩን እነሱ ተረከቡ፡፡ ባቢ ወደ ሃይማኖታዊ ሥራው አዘነበለ፡፡ ይህ ሁሉ የምነግርህ በአባቶቻችን ጊዜ የሆነውን ነው፡፡ በእኛ ጊዜ ደግሞ ከኃይለ ስላሴ ስልጣን

መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ “መሬት ላራሹ” የሚል ህግ ሲወጣ ግብራችንን በቀጥታ ለመንግስት መክፈል ጀመርን። ባቢም ለበሪ ከሚቀርብ ስጦታና መስዋዕት በቀር ከኛ ምንም አያገኝም (ቃለ መጠይቅ፡ 08/05/2004 ዓ.ም.)።

ይሁን እንጂ ባቢ በድሮውም ሆነ በአዲሱ ስርዓት ሃይማኖታዊ መለኮት ስላለበት በክፉ አይታማም። ከዚህ ይልቅ ህዝቡን ከበሽታ፣ ከድርቅና ረሃብ፣ ከአደጋ የሚከላከል የበሪ ልዩ መልዕክተኛ /ህዝቡንና በሪን አስታራቂ ሆኖ ይታመናል።

ባቢ የሚሆነው ሰው አዲስ ሕይወት የሚጀምርበት ስለሆነ ይህን ስርዓትም “የሽግግር አምልኮ” ካልነው ጋር ማመሳሰል ይቻላል። ባቢ ሲሾም የራሱ አምልኮታዊ ክዋኔዎች አሉት። ንጹህ እና የበላይ ከተባለው ዘር የሚመረጥ ሲሆን ስለመጀመሪያው ባቢ አሿሿም ከስርዓቱ ጥንታዊነት የተነሳ ማወቅ ባለመቻሉ በሟች ባቢ ቦታ የሚሾመውን የሹመት ስርዓት እንመልከት፡ ፡ ነባሩ ባቢ በእድሜው መግፋት ወይም በበሽታ ሲሞት በቦታው ከቤተሰቡ ታላቅ ወንድ ልጃቸው ይሾማል። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ነገር ቢኖር ነባሩ ባቢ ስልጣኑን መልቀቅ የሚችለው ሲሞት ብቻ ነው። ህዝቡ ይሹመው እንጂ አይሽረውም። ምንም ቢያጠፋ ወይም የህዝቡን ፍላጎት በትክክል ማሟላት ባይችል እንኳን (በዝሙት፣ በስካር፣ በጉልበት…) ከስልጣኑ አውርዶ በቦታው የሚሾም አካል የለም። *(ቃለ መጠይቅ፡ ባላባት ድክሳ አሰፋ፣ ጥር 9/2004)*



የምባ ባቢ አቶ ድክሳ አስፍን (አሰፋ)

ነባሩ ባቢ በእድሜ መግፋት ይሁን በበሽታ ሲሞት ከደከመበት ጊዜ ጀምሮ ህዝቡ ተተኪውን ከቤተሰቦቹ ማፈላለግና መምረጥ ይጀምራል፡፡ ቦታውን/ስልጣኑን የሚወርስ እድሜውም የደረሰ ወንድ ልጅ ካለው ያለምንም መስፈርት ስልጣኑን ይረከባል፡፡ ስልጣን ለመውረስ እድሜው ያልደረሰ ከሆነ ደግሞ ከልጆች ውጭ ከሆኑት ቤተሰቦቹ (ተከታይ ወንድሞቹ፣ አጎቶቹ፣ አማቾቹ) ይመረጣል፡፡ ባቢ ሲሞት ወዲያውኑ ጎድሚዎች ይከፍኑታል፡፡ መሞቱንም ከጎሚዎችና ከሚች የቅርብ ቤተሰቦች በቀር ማንም እንዲሰማ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም "ባቢ (የበሪ መልዕክተኛ) አይሞትም!" ተብሎ ስለሚታመንና ህዝቡ አባት የሌለው ሆኖ እንዳይሰማው ለማድረግ ነው፡፡ ሚቹን እንደከፈኑ ተተኪውን ጠርተው በማስቀመጥ በግ እያረዱ ጎድሚዎች አንጀት ያነባሉ፡፡ የሚቹንና የተተኪውን እግር አንድ ላይ በልብስ ያስራሉ፡፡

አንጀት የማንበቡ ስርዓት የሚከናወነው ሚቹ ባቢ ስልጣኑን ለሚረከበው ልጁ (ዘመዱ) ስልጣን ማስረከቡንና ምንም አይነት ቅሬታ የሌለው መሆኑን እንዲመሰክር ነው፡፡ ሚቹ ተተኪውን መቀበሉን የሚገልጸው ምልክት በአንጀት ውስጥ እስኪታይ ድረስ አንዱ አንጀት ሲበላሽ ሌላ በግ ይታረዳል፤ አሁንም ሲበላሽ ሌላ ይታረዳል፡፡ እንዲህ እያደረጉ የሚፈልጉትን ምልክት ካዩ በኋላ እግራቸው የታሰረበት ልብስ ተፈትቶ በተተኪው ላይ ይለበሳል፡፡ ሚቹንም አውጥተው ከበሪ ጫካ ውስጥ በስውር ያስቀምጣሉ፡፡ መቃብሩም በዚያው አከባቢ ይዘጋጃል፡፡

የሚች አስከሬን ከወጣ በኋላ ተተኪውን በገሃድ የመሾም ስርዓት ይከናወናል፡፡ በዚህም አንድ "እንጋሽ" የተባለ ሰው ትልቅ ድንጋይ ላይ ወጥቶ ጦር እየሰበቀ የሚች ባላባቱን ዝና እያወደሰ የተተኪውን ስም ጠርቶ በአባቱ ጀግንነት የሚቀጥል መሆኑን እየፎከረለት ይሸልላል (ሽለላው "ዳርግ" ይባላል)፡፡ ከዚያም ተተኪው ይሸልላል፡፡ እንደሚቹ ወይም ከዚያ በበለጠ ህዝቡን በሠላም ሊያስተዳድር እንደሚችል እየፎከረ ከገለጸ በኋላ የለቅሶ መርዶ ይሰራጫል፡፡ ድምፅ አውጥቶ ማልቀስም ይፈቀዳል፡፡

ዋናው ለቅሶ በተቆረጠለት ቀን መርዶ የደረሳቸው ወገን፣ ዘመድ፣ ጎረቤት ከተሰበሰበ በኋላ ይሆናል፡፡ ይህም ባቢው ከሞተበት ከ3ኛው እስከ 4ኛው ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን መርዶ የደረሰው ወገን ዘመድ ጋቢ በመግዛት፣ እንስትና (ሥሩ) እህል አስይዞ ለቅሶ ይመጣል፡፡ የሌላ አካባቢ ባቢ ከሆነ ደግሞ ወደ ሚች ባቢ ለቅሶ ሲሄድ ወጣቶችን (ጉልበተኞችን) ከሴትም ከወንድም መርጦ ጦርና ጋሻ አስይዞ ይሄዳል፡፡ ከለቅሶው ቤት አካባቢ (ጎረቤት) ሲደርስም ያስከተላቸው ወጣቶች ከፊት ለፊት እየቀደሙ በዛፍ፣ በእንስት፣ በቡና አትክልት፣ ወዘተ. እየወጡ፣ እየሰበሩ፣ ሴቶችም በእሪታ እየረበሹ ወደ ለቅሶ ቤቱ ይደርሱና ተመልሰው ወደኋላ

ይሄዳሉ። አሁንም ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ። የተሰበሰበው ህዝብም የባላባቱን ስም (በአካባቢው ስም) እየጠሩ መምጣቱን በማረጋገጥ ቦታ ይለቃሉ። የየትኛውም አካባቢ ባቢ ሲመጣ ሁሉም ክብር ይሰጠዋል። ለቀስተኛው ባላባትም ረጅም አርጩሜ ይዞ እየሰበቀ ከአዲሱ ባቢ ፊት ይደርሳል። በእሱ ፊት ከፎከረና ዝናውን ካሳየ በኋላ የያዘውን አርጩሜ ሰማይ ላይ ይወረውረዋል። በዚህ ጊዜም ተከታዮቹ (አጃቢዎቹ) እና ለቀስተኛው ህዝብ በሙሉ እልልታና ጩኸት ያሰማል። ምክንያቱም አዲሱ ባቢ (ተተኪው) "ልምድ ያለው አንጋፋ አማካሪ /ደጋፊ አለው" በሚል እምነት ነው። *(በቡድን ውይይት ወ/ሮ ጋበትከን ካሚን፣ጥር 21 ቀን 2004)*

ለቀስተኛው ባቢ ይህን አድርጎ ቦታ ከያዘ በኋላ አዲሱ ባቢም በተራው ተነስቶ በጀግንነት ክልሉን (አካባቢውን) ማስተዳደር እንደሚችል እና ለቀስተኛው ባቢ ባሳየው የ"አለሁልህ" ሞራል መደሰቱን ጦር በመስበቅና ጋሻ በመግጨት ያሳያል። ህዝቡም እንደገና እልልታና ጩኸት ያሰማል። ከዚህ በኋላ ክብ ቆመው ሴቶች ደግሞ ተንበርክከው የእንስት ግንድ አንጥፈው እየደበደቡና ሙሾ እያወረዱ ማስለቀስ ይጀምራሉ። ህዝቡ ይህን ሲያደርግ ጎድሚዎች የደበቁትን ሚች ባላባት በስውር ቀብረው ካጠናቀቁ በኋላ ጥይት በመተኮስ የለቅሶውን ፍጻሜ ያበስራሉ።


ጎድሚዎች ሚቹን ከመቅበራቸው በፊት ጀምሮ አንጀት ለማንበብ የታረዱትን በጎች በዚያው በአካ ውስጥ እየበሉ የሚቹንም መቃብር በጋቢ ጋርደው ይጠብቃሉ። በግ የሚቀርበው ተተኪው ባቢ ገንዘብ እየሰጠ ከገበያ/ከጎረቤት እየተገዛ ሲሆን ብዛቱም የተፈለገው የአንጀት ምልክት እስኪታይ ይወሰናል። ባቢው ከተቀበረ ከሦስተኛው ቀን ጀምሮ ተተኪው ባቢ የማንጻት(ጭልሺ)፤ የመለማመን እና አጠቃላይ የባቢ ስርዓቱን ማከናወን ይጀምራል። በሪም "ታከናውንለታለች" ተብሎ ይታመናል። በየአካባቢው የሚሾመው ባላባት ከተለያየ ማታ ቢሆንም የበላይ ከሚባሉት ውስጥ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው አካባቢ (ምባመር) ያለው ባላባት "ጋዳ" ከሚባለው ማታ የተሾመ ነው። *(በቡድን ውይይት አቶ ድክሳ አስፍን፣ ጥር 21/2004)።*

## 4.2. ጎድሚዎች

ጎድሚዎች እንደ ባላባቱ ንጹህ ከሚባለው ዘር ቢሆኑም ከተለያዩ ማታዎች የተውጣጡ ግለሰቦች ናቸው። ጎድሚዎች በተፈጥሮ ከተፈጥሮ ጋር ልዩ ግንኙነት እንዳላቸው ተደርገው ይታመናሉ። በሪ ያላትን ሃሳብ (መልዕክት) የሚገልጡ ልዩ መንፈሳዊ ኃይል ያለባቸው ሆነው ስለሚቆጠሩ ይከበራሉ። እነሱን ማስቀየም ማለት የበሪን መንፈስ ማሳዘን ማለት እንደሆነ ይታመናል። እነዚህ ጎድሚዎች "አንደንዴ እንደ ጠንቋይም ሆነው ይሰራሉ" ሲሉ የሻማመር

ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ አፍሪ ቓዳ[10] መደበኛ ባልሆነ ውይይት ጊዜ ይናገራሉ፡፡ ተስፋዬ ኃይሉም በመጣጥፋቸው ይህን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ ገልጸውታል፡፡

> The Godmis are magicians in which the force is contained in them which can be used by their specialty of reading the intestine of a sheep for beneficient purposes such as health, the fertility of crops, wealth, progency and success or for harmful purposes which include illiness, death, crop failure or disaster (Tesfaye Hailu 1994: 1020).



ወ/ሮ ጋበትከን ካሚን (የዝናብ ጎድሚ)

ጎድሚዎች በሁሉም ነገር ላይ ስልጣን የላቸውም፡፡ ሲሞቱም ስልጣናቸውን ወንድ ልጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ሴት ልጆቻቸውም ይወርሳሉ፡፡ በሁሉም ነገር ላይ ስልጣን እንዳለው የሚታመነው ባላባት ብቻ ሲሆን ጎድሚዎች እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ተናጠል ስልጣን አላቸው፡፡ በዚህም መሠረት የዝናብ ጎድሚ፣ የእህል ጎድሚ፣ የከብት ጎድሚ፣ ... እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ የዝናብ ጎድሚ ከዝናብና ፀሐይ ጉዳይ ውጭ ሌላ ነገር ላይ ምንም አይነት ተአምር መስራት አይችልም፡፡

---

10 አቶ አፍሪ ቓዳ የ 50 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ የስድስት ልጆች አባት፣ በበሪ አምልኮ ሰፊ ልምድና እውቀት ያላቸው የሻማመር ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡

ስጦታም አይቀርብለትም። የግል ተሰጥኦና ችሎታ አላቸው *(ቃለ መጠይቅ፣ ባላባት ድክሳ አሰፋ፣ 09/05/2004ዓ.ም)።*

ጎድሚዎች ከሰው በላይ ከበሪ በታች የሆኑ የሰውና የበሪ አገልጋዮች ናቸው። ህዝቡንና በሪን የሚያገናኙ ድልድዮችም ሆነው ይታመናሉ። ይህ ሲባል ግን እያንዳንዱ ግለ-ሰብ በግሉ የሚያደርገው አምልኮ እንደተጠበቀ መሆኑ ሳይዘነጋ ነው።

ጎድሚዎች ካላቸው በርካታ ተግባራት አንዱ በንብረት ላይ "በሪ ማኖር" ነው። በሪ ማኖር ማለት ንብረት ሳልተወሰነ ጊዜ እንዳይነካ በበሪ ስም መከልከል (መገዘት) ማለት ነው። አንድ ግለሰብ ንብረቱ በልጆች፣ በሚስቱ ወይም በሌቦች ያለ አግባብ እየባከነ ቢያስቸግረው ከጎድሚዎች አንዱን ጠርቶ በሪ ያኖራል። ጎድሚውም ደረቅ የእንሰት ቅጠልን እና ከንብረቱ ናሙና ወስዶ ከእንጨት ጫፍ ላይ አስሮ በንብረቱ መሃል ላይ ያቆማል። ይህ ስርዓት በአብዛኛው የሚከናወነው በአትክልቶች ላይ (ሽንኮራ፣ ኮረሪማ፣ ቡና፣ እንሰት፣ ፍራፍሬዎች፣...) ስለሆነ ያለ እንጨትም በአትክልቱ ቅጠል ላይ በማሰር በሪን ለምኖ፣ ሌባን ረግሞ ይሄዳል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ባለቤቱም ጭምር ከዚያ ንብረት ውስጥ ወስዶ መጠቀም አይችልም። የሚታረም ከሆነ እያረመ፣ እያፀዳ እና እያጠረበት ይጠብቀዋል። ከዚህ ውጭ ባለቤቱም ሆነ ሌላ ሰው በድፍረት ወስዶ/ሰርቆ ቢሄድ ይቀሰፋል ተብሎ ይታመናል።

ባለቤቱ በንብረቱ ላይ በሪን ካኖራት ጊዜ ጀምሮ ለቤተሰቦቹ በሙሉ ይነግራቸዋል፤ ያስጠነቅቃቸዋልም። ይህን ሰምቶ ሊሰርቅ የሚገባ ቤተሰብ ካለ ካለማወቅ ሳይሆን ከድፍረት የተነሳ ስለሆነ ከተጠቀመበት ጊዜ ጀምሮ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከአናቱ እስከ እግር ጥፍሩ እከክ ይወርሰዋል። እከኩም በምንም አይነት መድሃኒት የሚድን አይደለም። የበሪ ቁጣ ነው ተብሎ ይታመናል። ባለቤቱ ይህን እያወቀ ዝም ይላል። ሌባውም ለረጅም ጊዜ ከተሰቃየ በኋላ ጎድሚው ተጠርቶ ይቅርታ እንዲያደርግለት ይደረጋል። በሽተኛው የሰው መሳለቂያ በመሆን በስነ-ልቦናም እንዲጎዳ ይደረጋል። በሪን ያኖረው ጎድሚ መጥቶ ሌባውን ይዞ በሪን እየለመነ ይቅርታ ካስደረገለት ብቻ ይድናል። ይህን ለማድረግም ለጎድሚው ከሳንቲም በተጨማሪ ጥሩ ምግብ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። *(ቃለ መጠይቅ፣ አሸናፊ ጎፍታ[11]፣ጥር 13/2004)*

---

[11] የ 88 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ ሁለት ሚስትና ስምንት ልጆች ያሏቸው፣ የጎድሚ ዘር እና በንብረት ላይ በሪ የሚያኖሩ የተከበሩ አዛውንት ናቸው።

ጎድሚዎች ያልቀመሱትን እህል ማንም አይቀምስም፤ ያለ እነሱ የህዝቡ ንብረትም አይባረክም ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በማንኛውም ነገር ላይ ቅድምና የሚሰጣቸው የተከበሩ ግለ-ሰቦች ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን ጎድሚዎች በሀብት ከሌሎች ሰዎች የበለጡ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ እንደማንኛውም ሰው የሆነ የኢኮኖሚ አቅም አላቸው፡፡ ነገር ግን በተግባራቸው፣ በዘራቸው እና በልዩ ልምዳቸው በህዝቡ ዘንድ የተከበሩና የተፈሩ ናቸው፡፡ ለባላባቱም እንደ ልዩ አማካሪዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡

ባቢም ሆነ ጎድሚ ዋና ተግባራቸው የህዝቡን ደህንነት ማስጠበቅ ነው፡፡ ከበሪ ጋር በመንፈስ፣ በህልም እና በምልክቶች እየተገናኙ እና መስዋዕት እያቀረቡ ህዝቡ የሚፈልገውን ነገር ማሳካት ከበሪ የተሰጣቸው ፀጋ ከህዝቡም የተቀበሉት ኃላፊነት ሆኖ ይታመናል፡፡ በህዝብና በሀገር ላይ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን ይከላከላሉ፡፡ *(ቃለመጠይቅ፣ አቶ ግንጀሎ ሀቅዳኪ፣ 12/05/2004)፡፡*

## 4.3. አንጀት የማንበብ ስርዓት

ከጥቂት ጉዳዮች (ለምሳሌ፡- በጋብቻ እና በልደት ጊዜ) በስተቀር አንጀት የማንበብ ስርዓት የማይፈፀምበት ጉዳይ በአሪ ብሔረሰብ የለም ማለት ይቻላል፡፡ በእያንዳንዱ አጋጣሚ አንጀት ይነበባል፡፡ ይህን ስርዓትም በዋናነት “የማንጻት አምልኮ” ውስጥ አካቶ መመርመር ይቻላል፡፡ ለግለ-ሰብም ሆነ ለማህበራዊ ጉዳይ አንጀት የማንበብ ስርዓት ይፈፀማል፡፡ የበሪ አላማ መገለጫ ዋና መንገድም የበግ አንጀት ንባብ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለአንጀት ማንበብ አንጀት በማንበብ ሰፊ ልምድ ያላቸው አቶ ማሞ ናሻ[12] የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> አንጀት በማንበብ ረጅም ልምድ አለኝ፡፡ ለብዙ ሰዎች አንጀት አንብቤላቸዋለሁ፡፡ ሰዎች አንድ ችግር (በሽታ፣ ሞት፣ ውልደት፣...) ሲከሰትባቸውና ጥሩ አጋጣሚዎችም ሲፈጠሩላቸው ወደ እኔ ይመጣሉ ወይም ይጠሩኛል፡፡ እኔም አንጀቱን አነብላቸዋለሁ፡፡ በሪም ስለሰዎቹ ያላትን አላማ በአንጀቱ በኩል ትገልጥልኛለች፡፡ አንጀቱ ውስጥ ያሉት የደም ጠብታዎች ለእኔ ትርጉም ባለው ሁኔታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው ለባለጉዳዩ መልክት አላቸው፡፡ እኔም እንቅስቃሴውን በእጄ ላይ አሳያቸዋለሁ፡፡ ለምሳሌ ምልክቱ ከትከሻዬ ተነስቶ ክንዴን አልፎ ከእጄ ሰዓት ማሰሪያ ቦታ ሲደርስ ወደ ጎን ከወጣ ባለጉዳዩ ወይም ከቤቱ አንድ ሰው ይሞታል፡፡ ነገር ግን ከትከሻዬ ጀምሮ ወርዶ እስከ እጄ ጣት ጫፍ ድረስ ከወጣ ባለ ጉዳዩ ሌላ ቦታ ለቅሶ ይሄዳል፤ ከሩቅ ቤተዘመዶቹ ይሞታሉ ማለት ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ 20/05/2004 ዓ.ም.)

[12] የ95 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ አንጀት የማንበብ ልምድ ያላቸው፣ የጋዘር ንዑስ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች አንዱ ናቸው፡፡

በታረደ የበግ አንጀት ውስጥ በሪ የምትናገረውን ነገር ወይም በባለ ጉዳዩ ላይ የሚፈፀመውን መልካምና ክፉ አጋጣሚ ባለሙያው (ጎድሚው) በእጆቹ እና በዓረፍተ ነገሮች ይገልጻቸዋል፡፡ ከአገላለጾቹም የተወሰኑትን በምሳሌነት እንመልከት፡፡

<u>አሪኛ</u>

ኮፊዛንክ ሀዶ ኮክ ሀቾ
ኮክ ኦስ ውታችሶ ባካ ተይ፡፡

****

ከፊዛንክ ሀዶ ኮክ ሀቾ
ዱሪክ ቦሥስ፡፡


<u>አማርኛ</u>

ከላይ መጥቶ በዚህ ወረደ
ወደዚያ ወጥቶ ምድጃ ይዞ ሄደ፡፡

****

ከላይ መጥቶ በዚህ ወረደ
ከጫፍ አደረሰ /ወጣ፡፡

"ምድጃ ይዞ ሄደ፡፡" ማለት በቤተሰብ መካከል መፈራረስን/መለያየትን የሚያመለክት ሲሆን ይህም ምልክት ከታየበት ጊዜ ጀምሮ ቤተሰቡ ለበሪ በግ እያረደ የመንጻት አምልኮ ይፈጽማል፤ ጠንቋይ ቤትም (ሳቢባ ኤር) በመሄድ ምን ማድረግ እንዳለበት ይጠይቃል፡፡ ቤተሰቡ ይህን እያደረገም በሪ አንዴ ቆርጣ ከሆነች ምድጃ ይዛ ትወጣለች ወይም በቤተሰቡ ላይ እንዲደርስ ያሰበችውን ችግር ማስቀረቷን በአንጀት/በጠንቋይ ትገልጻለች፡፡ "መልካም ሆነ" ወይም "በሪ ታረቀችው" የሚባለው ምልክት ደግሞ ከላይ መጥቶ ወደዚያ ሳይወጣ /ከጫፍ ሳይደርስ ሲቀር ነው፡፡ የደም ጠብታዎች ዞረው ዞረው በእጃችን ሰዓት ማሰሪያ ላይ ሲቆሙ (በአንጀቱ ውስጥ) የመጣው ችግር ቆሟል፤ይቅር ተብሏልም ማለት ነው *(ማሞ ጉሳብ፣ 14/05/2004 ዓ.ም.)*፡፡



አቶ ድክሳ አስፍን አድባር ስር አንጀት ሲያነቡ

## 4.4. የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ከበራ የሚፈጸምባቸው ዋና ዋና ቦታዎች

የአሪ ብሔረሰብ ለበሪ ለተለያየ ምክንያት በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከበራ/አምልኮ ይፈጽማል፡፡ ለከበራው በምክንያትነት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል ለአዝመራና ለመኸር የሚያስፈልገው የአየር ጠባይ እንዲኖር፣ የሰውን፣ የከብቶችን እና የሰብሎችን ወረርሽኝ ለመከላከል፣ በሟች እና በህይወት ባሉ ቤተሰቦች መካከል የሚፈጠር ግንኙነትን ለማስተካከል፣ በወሊድ ጊዜ የቤተሰብን ንጽህናና የበሪን ክብር ለማስጠበቅ፣ ምርትን በበሪ አስባርኮ ለመጠቀም፣ ወዘተ. ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህና መሰል ጉዳዮች ከበራ የሚደረግላቸው በሦስት ዋና ዋና የከበራ ቦታዎች ላይ ነው፡፡ እነዚህም አካ፣ አብዳር (አድባር) እና ማል ናቸው፡፡

“አካ” የሚለው ቃል በአሪኛ ሦስት ትርጉሞች ያሉት ሲሆን አንደኛ “አያቴ” ሁለተኛ፣ “ዋና የማምለኪያ ሥፍራ” እና ሦስተኛ “የበሪ መኖሪያ” የሚሉትን ጽንሰ ሀሳቦች የሚገልጽ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቤተ-ዘመድ (lineage) የራሱ አካ አለው፡፡ ማንኛውንም መስዋእት ለበሪ ሲያቀርብ በመጀመሪያ ደረጃ ለአካ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በአካ ጫካ ውስጥ በሚቀርብ መስዋዕትና በሚደረግ አምልኮ ውስጥ ሴቶች አይሳተፉም፡፡ ምክንያቱም ሴቶችና ልጆች በበሪ እምነት ቀጥተኛ አምልኮ ለማድረግ ስለማይፈቀድላቸው ካልሆነ በቀር ሌላ ምክንያት ከመረጃ አቀባዮቼ አላገኘሁም፡ ፡ ከባላባት፣ ከቤተሰብ አስተዳዳሪ (ባቢ. ቶይድ) እና ከጎድሚዎች በቀር ማንም ሊገባበትም

(ሲደርስበት) አይችልም፡፡ እጅግ በጣም የተከበረ ቦታ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በዚህ ጥናት እንኳ የሥፍራውን የአምልኮ ክዋኔ በካሜራ መቅረጽ አልተቻለም፡፡

"አብዳር/አድባር" ደግሞ ግለሰቦች በማንኛውም ጊዜ ለበሪ ፀሎት የሚያደርሱበት፣ በትርፍ ጊዜያቸው የሚያርፉበት እና ዕለታዊ መስዋእታቸውን (ሣንቲም፣ ክር፣ ጨሌ፣ ወዘተ.) የሚጥሉበት ዛፍ ነው፡፡ ይህም ሴቶችን በቀጥታ የማያሳትፍ ቢሆንም ለአድባር የቀረበን (የታረደን) በግ መብላት ይችላሉ፡፡ ዓመታዊ የሆኑ (በዓመት አንዴ የሚከናወኑ) የእምነቱ ክዋኔዎች ሲመጡ በሦስቱም ቦታዎች በግ ይሰዋል፡፡ መጀመሪያ ለአካ፣ ቀጥሎ ለአብዳር፣ በመጨረሻም "ማል" ላይ ይታረዳል፡፡

"ማል" የሚለው ቃልም ሁለት መሠረታዊ ትርጉሞች አሉት፡፡ ትርጉሞቹም በቃሉ መጥበቅ እና መላላት የሚከሰቱ ሳይሆን ላልቶ ሲነበብ ብቻ በድምጽ አወጣጥና በአውድ ልዩነት የሚመጡ ናቸው፡፡ አንደኛው ትርጉም በአሪኛ "ማል" ሲባል ቶሎ ወደ አእምሮ የሚመጣው "ደጅ" የሚለው ትርጉም ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በዚህ ጥናት ውስጥ የተወከለውን ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጸው "የቅድመ-አያት፣ የአያት ወይም የአባት መኖሪያ ቤት የነበረበት ቦታ" ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በቦታው የሚገኘው ግለሰብ/ቤተሰብ በቦታው ላይ ቀድመው ለኖሩበት ሰዎች መስዋዕት ያቀርባል፡፡ አላፊዎቹ በምትሃት እንዳይመጡበትና እንዳይቀስፉት መስዋእት እያቀረበ ይከላከላቸዋል፡፡ *(ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ማሞ ጉሳብ፣[13] ጥር 14/2004 ዓ.ም.)*

## 4.5. የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ከበራ የሚፈጸምባቸው ጊዜያት

በአሪ ሀገረሰባዊ እምነት ዘንድ ከበሪ እምነት ጋር በተያያዘ በርካታ ከበራዎች ይፈጸማሉ፡፡ ብሔረሰቡ በሪን እንደህይወቱ ምንጭ አድርጎ በማመኑ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴው የእምነቱን መርህ ይከተላል፡፡ በቤተሰብ፣ በቡድን እና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ውስጥ ባለው እለታዊ ኑሮው የበሪን አማልክትነት ያስባል፡፡ ምክንያቱም በሪን መዘንጋት የሚያስከትለው መዘዝ ብዙ ነው ተብሎ ይታመናልና፡፡

### 4.5.1. እህል በሚዘራበት ጊዜ

ብሔረሰቡ ለበሪ ከሚያከናውናቸው ዓመታዊ የአምልኮ ክዋኔዎች መካከል በአዝመራ/በዘር ወቅት የሚያከናውነው አምልኮ አንዱ ነው፡፡ በአዝመራ ጊዜ አስፈላጊው የአየር ጠባይ እንዲኖር ሲል አስቀድሞ ለበሪ መስዋእትና ፀሎት በባቢ አማካይነት ያደርሳል፡፡ ለዚህም የሚሆነው

---

[13] የ85 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ ባህላዊ የጊዜ አቆጣጠርን ጠንቅቀው የሚችሉና ስለበሪ አምልኮ ሰፊ እውቀት ያላቸው፣ የስድስት ልጆች አባት፣ የሻማመር ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ቁልፍ መረጃ ሰጪ ናቸው፡፡

መስዋእት በግና ገንዘብ ሲሆን ህዝቡ ተመካክሮ በማዋጣት ያቀርባል። ባቢውም እነዚህን ስጦታዎች ተቀብሎ ከዝናብ ጎድሚዎች ጋር በመመካከር ለበሪ ፀሎት የሚያደርሱበትን ቀን ይቆርጣል። በዚህ ዕለትም የሚሆነውን የፀሎት ስርአት የምባ ባቢ አቶ ድክሳ አስፍን እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> በዘር ወቅት ዝናብ እንዲመጣ ሲፈለግ ህዝቡ በቤቱ ተመካክሮ "እስኪ ከባቢ ጋር ሆነን በሪን እንጠይቃት፤ ድርቅ ሊከሰትብን ነው፤ የአዝመራ ወቅትም እያለፈ ነውና።" ብሎ ገንዘብ አዋጥቶ ለእኔና ለዝናብ ጎድሚ አራት ጥቁርና ነጭ በግ ያቀርባሉ። ወደ እኔ ሲያመጣ ሁለቱን (ነጭና ጥቁር) አስቀርቼ ሁለቱን ለጎድሚው እልካለሁ። ከዚያም ጎድሚው በራሱ ቤት አጠገብ ካለው አካ ውስጥ አርዶ አንጀት አንብቦ ጉበት ከቀመሰ በኂላ በእርጥብ ቦታ ገልፊ ያስቀምጣል። ይህን ሁሉ ካደረገ በኂላ ወደ እኔ ይመጣል። አብረን ደግሞ እኔ ባዘጋጀሁት (ቀድሞ አባቴ ባዘጋጀው) አካ ውስጥ ተመሳሳይ ስራ እንሰራለን። ዝናብንም እየጠራን በሪን እንለምናለን። ነጩን በግ ብቻ አርደን አንጀቱን እናነባለን፤ ጉበቱን ጫካው ውስጥ እንበላለን። ጥቁሩ በግ ግን ላልተወሰነ ጊዜ ከጫካው አካባቢ እንዲዞር እናደርጋለን። ዝናቡም በሁለት ቀን ልዩነት ውስጥ መምጣት ይጀምራል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 09/2004)

በዘር ወቅት ዝናብ እንዲመጣ የሚከናወነው ተግባር በዋናነት የሚተረጎመው ለመስዋዕት በሚቀርቡት ነጭና ጥቁር በግ እና በእርጥብ ቦታ በሚኖረው ሾጣጣ ድንጋይ (ገልፊ) ነው። በዚህ የጸሎት ጊዜ ነጩ በግ ፀሐይን ወክሎ የሚቀርብ ሲሆን ትርጉሙም አንድም፤ ፀሐዩ እንዲጠፋ (ለጊዜው) ሲባል ታርዶ በአካ ውስጥ ይበላል። በዚህም በሪ ፀሐይን ወስዳ ትደብቃታለች ተብሎ ይታመናል። አንድም ደግሞ ፀሐዩ እንዲጠፋ አንፈልግም፤ ነገር ግን ከዝናብ ጋር አብሮ ይሁንልን በማለት ከጥቁር በጉ ጋር ያቀርባሉ። ጥቁር በግ መቅረቡም ዝናብን ወክሎ ሲሆን ዝናቡ እስኪመጣ ድረስ ከአካ አካባቢ አይጠፋምና መለማመኛ ነው። ሾጣጣ ድንጋዩ ደግሞ ጫፉ ወደ ሰማይ ሆኖ የዝናብና የጸሐይ መለመኛ ሆኖ ይታመናል።

በአካ ውስጥ ይህን ስርዓት ከፈፀሙ በኂላ ወደ ቤት ይገባሉ። ቡና ተፈልቶ፣ በቆሎ ተቆልቶ፤ ጎድሚው፣ የባቢው ቤተሰቦች እና ጎረቤቶች ተሰብስበው ባቢ ከቡናውም ከቆሎውም ወስዶ ከረጨና ከበተነ በኂላ ይበላሉ። ለበሪ የታረደው ነጭ በግም ተጠብሶ ይበላል። የተሰበሰቡት ሰዎች ሲበሉና ሲጠጡ ባቢው ግን ከቤቱ መሃል ላይ ቆሞ ህዝቡን እየባረከ በሪን እየተለማመነ ይቆያል። በልተውና ጠጥተው ሲጨርሱም ሁሉም ቀጠማ እየያዘ አምጥቶ ለባላባቱ ይሰጣል። ባቢውም እየባረካቸው ቀጠማውን ከቤት እስከ ውጭ (ደጅ) ይበትናል። በመጨረሻም ሁሉም በዚሁ ቀጠማ ላይ እየረገጠ ወጥቶ ይሄዳል፤ የልመናውም ፍጻሜ ይሆናል። ከዚህ በኂላ ሁሉም ዝናብን ይጠባበቃል፤ ዝናቡም ቀስ በቀስ መምጣት ይጀምራል። ይህ ሲሆንም ባቢው ጥቁሩን በግ አርዶ ከቤተሰቦቹ ጋር ይበላል።

ከተዘጋጀው ምግብ ባላባቱ የማይቀምሰውና ቆሞ የሚጠብቃቸው ለምን እንደሆነ ባላባቱ "እኔ የምቆመውና የማልበላው ለህዝቡ ደህንነት መቆሜን ለማሳየት እና የፀሎቴ መልስ ሳይፈጸም ለበሪ ከቀረበው መስዋእት አልበላም ለማለት ነው፡፡ ፀሎቴ ሥራውን ሳይሰራ ቁጭ ብዬ መብላት ህልናዬን እንደ መጣል ስለምቆጥርም ጭምር ነው፡፡" ብለው ገልጸዋል (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ድክሳ አስፍን፣ 09/05/2004 ዓ.ም.)፡፡

## 4.5.2 የሰብል ወረርሽኝ በተከሰተ ጊዜ

የበሪ አምልኮ ከሚፈጸሚባቸው አጋጣሚዎች አንዱ የሰብል ወረርሽኝ መከሰት ነው፡፡ በአሪ ብሔረሰብ የበሪ ስርዓተ-አምልኮ የሰዎችን ጤንነት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ከማገልገሉም በተጨማሪ ሰብልን ከተለያዩ የተባይ ወረርሽኝ ለመከላከል እንደሚያግዝ ይታመናል፡፡ በደቡብ አሪ ወረዳ ውስጥ በተከታታይ ባይሆንም አልፎ አልፎ የተባይ ወረርሽኝ ይከሰታል፡፡ ወረርሽኝ በተከሰተ ጊዜም የግብርና ባለሙያዎችና የተለያዩ አካላት የሚወስዱት ዘመናዊ የተባይ መከላከያ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው የምባ አሪ ማህበረሰብ ከዘመናዊው መከላከያ (ኬሚካል) መፈጠር በፊት ጀምሮ በበሪ አምልኮ እንደሚከላከል የምባ ባቢ አቶ ድክሳ አስፍን ገልጸዋል፡፡

ብሄረሰቡ በአዝመራ ወቅት አስፈላጊው የአየር ንብረት እንዲኖር አምልኮውን ይጽማል፡፡ ከአዝመራ በኋላም ከቡቃያ እስከ ምርት (ፍሬ) ድረስ ባሉት ጊዜያት ውስጥ እንዳጋጣሚ ሆኖ የተባይ ወረርሽኝ ቢከሰት ለዚህም አምልኮ ይፈጸማል፡፡ በቅርቡም (2003 ዓ.ም) "ኤላ" የተሰኘ የሰብል ተባይ ወረርሽኝ ተከስቶ የተከናወነውን ከበራ የምባ ባላባት አቶ ድክሳ አስፍን እንዲህ አውስተዋል፡-

> የአባቴን ቦታ በተተካሁ በሶስተኛው ዓመት ላይ "ኤላ" የሚባለው ኃይለኛ የሰብል ወረርሽኝ ተከስቷል፡፡ በስርዓቱ መሰረት ወረርሽኙን ለመከላከል የበግ መስዋዕት የሚቀርበው ከህዝቡ በተዋጣ ገንዘብ ተገዝቶ ቢሆንም በወቅቱ ህዝቡ ችላ በማለቱ እኔ በራሴ ገንዘብ በግ በማቅረብ በቅርበት ካሉኝ ጎድሚዎች ጋር አምልኮውን ፈጽመናል፡፡ አምልኮው እንደማንኛውም ጊዜ አካ ውስጥ አንጀት በማንበብና ጉበት በመቅመስ ይካሄዳል፡፡ ከዚያም ወደ "ማል" በመሄድ ከተባዩ የተወሰኑትን በመልቀም ምጣድ ላይ ቆልተን ፍም ውስጥ ጨምረናል፡፡ አንዱን ደግሞ በሕይወት ይዘን በቂጡም እንጨት ሰክተን "በሪ ከሀገራችን እንዲህ ታባክንህ! ወደ መጣህበትም ትመልስህ!" ብለን ረግመን አየር ላይ ወርውረናል፡፡ ከማግስቱም ጀምሮ ተባዩ ከሰብል ላይ ቀስ በቀስ እየረገፈ ጠፍቷል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ 09/05/2004 ዓ.ም)

ከላይ አቶ ድክሳ አስፍን እንደገለጹት የተባይ ወረርሽኝ በተከሰተ ጊዜ ባቢው ከእህል ጎድሚዎች ጋር በመሆን ከህዝብ ወይም ከባቢውና ጎድሚዎች የቀረበን የመስዋዕት በግ አርደው

አንጀት ካነበቡ በኋላ አካ ውስጥ ጉበት ይቀምሳሉ። ከዚያም የባቢው ጎረቤቶችና ሴቶች ከተባዩ ለቅመው ሲያቀርቡ የባቢው ሚስት እሳት በማንደድና በመቁላት ትረዳቸዋለች። ባቢውም የተቆላውን ተባይ በገል ወይም በቅል ስንጣቂ ውስጥ ይዞ ከላይ የተገለጸውን እርግማንም ረግሞ ፍም ውስጥ ይጨምራል። በአንዱም እንጨት ሰክቶበት አየር ላይ ይወረውረዋል። ይህን አምልኮ ከፈጸሙበት ማግስት ጀምሮም ወረርሽኙ እየተመናመነ እንደሚጠፋ ይታመናል።

### 4.5.3 በመኸር (በምርት መሰብሰብ) ወቅት

ፀሐይ እንዲሆንና ዝናብ እንዲቀንስ/እንዲጠፋ ሲፈለግም ህዝቡ በመመካከር እንደ አዝመራው ጊዜ በግ በማቅረብ እንዲለመንለት ያደርጋል። ስርአቱም በአዝመራ ወቅት ከሚፈጸመው ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ ጥቁር በግ ግን አይቀርብም። ለባቢውም ለጎድሚውም ነጭ በግ ይቀርባል። ጎድሚውም ገልፊውን ከእርጥብ ቦታ አንስቶ ደረቅ ቦታ ያስቀምጣል። በዚህም “ፀሐይ ይሆናል፤ ለመኸር አመቺ ጊዜ ይመጣል፤ ሁሉም ሰው ሰብሉንና እህሉን በሠላም ሰብስቦ ያስገባል።” ተብሎ ይታመናል።

### 4.5.4 አዲስ እህል ሲገባ/ሲቀመስ

እህል ከተሰበሰበ በኋላ ደግሞ እህሉን ለመጠቀምም የራሱ ከበራዊ ክዋኔ አለው። ይህም “የምስጋና ከበራ” ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር በቀጥታ ሊያያዝ ይችላል። እህል ለመቅመስ ወይም ገበያ ለማውጣት ለበሪ የምስጋና ከበራ መፈጸም ግዴታ ነው። እያንዳንዱ የቤተሰብ መሪ (ባቢ ቶይድ) ከሰበሰበው ምርት የቤተሰቡን ሀረግ ቆጥሮ ብኩራት ወስዶ ለእህል ጎድሚ ይሰጣል። ጎድሚውም ባርኮ ለበሪ አስቀርቶ ናሙናውን ለባለቤቱ መልሶ ይሰጠዋል። ባለቤቱም ወደ ቤቱ ተመልሶ ቦርዴ እና እንጀራ አዘጋጅቶ ከጎተራ ስር ከቤተሰቦቹ ጋር የእህል ቀመሳ (ዶም) ያከናውናል። በዚህ ብቻም አያበቃም፤ ጎድሚውን፣ ወገን ዘመዶቹን በሙሉ ጠርቶ “ድሽታ” (የእህል ቀመሳ ድግስ) ያዘጋጃል። ከመረጃ አቀባዮቼ የቆሬትር ንዑስ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ለጋስ ሀቾዳኪ የሚከተለውን መረጃ ሰጥተውኛል።

> እህል ሲደርስ ተሰብስቦ ጎተራ ውስጥ ይጨመራል። ለጎድሚም የመጀመሪያው ይሰጣል። ከዚያም ለቤተሰብ ብቻ የሚሆን እንጀራና ጠላ ተዘጋጅቶ ከጎተራ ስር በቤቱ ባለቤት ኃላፊነት/መሪነት ይቀመሳል። ይህም “ድሽታ” እስኪዘጋጅ ድረስ ልጆች ቀለብ እንዳይቸገሩ ሲባል እንጂ ዋናው ቀመሳ ጎረቤት፣ ወገን ዘመድ ተሰብስበው ድሽታ ከጠጡ በኋላ ነው። ድሽታ ማለት እንግዲህ እንጀራ ተጋግሮ፣ ጠላ ተጠምቆ፣ ወይሳ እየነፉ ሲጨፍሩ ውለው አድረው የሚሄዱበት የእህል ቀመሳ ድግስ ነው። (ቃለ መጠይቅ፡ ጥር 12/2004)

ይህ በቤተሰብ ደረጃ የሚከናወነው አምልኮታዊ ስርዓት በወጉ ካልተከናወነ እህሉ ማሳ ላይ ሳለ ጀምሮ መብላትም ሆነ መሸጥ አይቻልም፡፡ ሴቶች ለአምሮት ወይም ለልጆች ብለው ቅንጣት ያህል ወስደው ቢጠቀሙ እንኳ የቀመሱት የቤተሰብ አባላት በሙሉ ይታመማሉ፡፡ እስከሞትም ይደርሳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ እንዳይፈጠር ደግሞ እህል ሲዘራ "የእሸት" ተብሎ ለብቻው ይዘራል፡፡ ወቅቱ ሲደርስም የቤተሰብ ኃላፊው ከእህል ጎድሚው ጋር በሪን አመስግነው ይቀምሳሉ፡ ፡ ከዚያም ከአባት እስከ ልጅ በየእድሜያቸው ቅደም ተከተል ይቀምሳሉ፡፡ አንዳንድ ዓመታዊ ስራስሮች (ቦዬ) በሚቀመሱበት ጊዜ ግን ጎድሚዎች በእያንዳንዱ ቤተሰብ እየተጠሩ ይቀምሳሉ፡፡ ይህን ስርዓት አባት በህይወት ከሌለ የአባት ወንድም ወይም በቤተሰብ ውስጥ ያለ ታላቅ ወንድ ልጅ ያከናውናል፡፡

በቤተሰብ ደረጃ በዚህ ሁኔታ የሚከናወነው ስርዓት ባቢ ቤት ሲሆን ለየት ያለ ዝግጅት ይጠይቃል፡፡ ባቢው ብዙ ረዳቶች/አጋሮች ስላሉት ምን ጊዜም ሰፊ እርሻ ያሳርሳል፡፡ ሰፊ ምርትም ይሰበስባል፡፡ ለእርሻም ሆነ ለምርት ስብሰባው ህዝቡ ተሰብስቦ በደቦ ያከናውናል፡፡ "ከባቢ ቤት እህል ከጠፋ እኛ ቤት ድርቅና ረሃብ ይሆናል፡፡" በሚል እምነት ለባቢ እህል ይጨነቃል፡፡ ይህ ሰፊ ምርት ከተሰበሰበ በኂላ ባቢው ታላቅ ድሽታ ያዘጋጅና የፈለገ ሰው ሁሉ መጥቶ እንዲጠጣ እንዲበላ በአጠቃላይ እንዲደሰት ይጋብዛል፡፡

ሩቅ ያሉትም ጭምር በቡድን በቡድን በመሆን (ከየቀበሌያቸው) ወይሳና ይቻ (የሙዚቃ መሳሪያዎች) ይዘው ይመጣሉ፡፡ የባቢው ጎረቤቶችም የዳስ ጥላ አዘጋጅተው የጠላ መጠጫ ሾርቓ (የቅል ስንጣቂ) ሰብስበው፣ የሚመጡትን እንግዶች እየተቀበሉ ያስተናግዳሉ፡፡ ከሚበላው እየተበላ ከሚጠጣውም እየተጠጣ በየቡድናቸው መጨፈር ይጀምራሉ፡፡ እየተበላ እየተጠጣና እየተጨፈረ ይታደርና በማግስቱም እስከ ረፋድ ድረስ ሲጫወቱ ቆይተው በመጨረሻ ላይ ባቢው አንድ ማሰሮ ጠላ ውስጥ ግራዋ ጨምሮ ይሰጣቸዋል፡፡ ህዝቡም ይህን ግራዋ ያለበትን ጠላ እየመረራቸው ጠጥተው ከባቢው የሚወጣውን ጸሎት ተቀብለው ይሄዳሉ፡፡ ጸሎቱም እንዲህ የሚል ነው፡፡ *(ምልከታ፣ጥር 09/2004)*

### አሪኛ

| ባቢው | ህዝቡ |
|---|---|
| እስኒ ዎን እምስንዳ በሪ | |
| ኤሮንታንክ ዳቺ ካይስክ | ዎን ካይስክ |
| ምሽም ዎን ታትክ | ዎን ታትክ |
| እስኒ ዎን ጻቕምስተንክ ከካ | |
| ምሺ ዎ ላልስተንክ ከካ | |
| ቦንክ ቦንክ ዎም አንጅክ | ዎም አንጅክ |

### አማርኛ

| | |
|---|---|
| እህል የሰጠሽን በሪ | |
| ከቤታችን ረሃብን አጥፊልን | አጥፊልን |
| ጥጋብን አምጪልን | አምጪልን |
| እህል እስኪመረን | |
| ጠግበን እስኪንበትን | |
| በየዓመቱ ባሪክን | አዎን ባሪክን |

ባቢው ጠላ ውስጥ ግራዋ የሚጨምረው ህዝቡ ጠላን እስኪመረው ድረስ ጠጥቶ የሚጠግብበት ሀብት እንዲኖረው መመኘቱንና በሪም እንዲህ ህዝቡን እንድትባርክ መለመኑን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡

## 4.5.5. የበሪ መገለጫ ቀን

የአሪ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ የሚያመልካት በሪ በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች ለግለ-ሰቦች እና ለእምነቱ መሪዎች በምትሃት፣ በህልም እና በምልክት ትገለጣለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ከነዚህም መገለጫዎች በተሻለ መንገድ ደግሞ ለአንዳንድ አማኞቿ የተወሰነ አካሏን በግልጽ እንደምታሳይ እና በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ በንፋስ እንደምትገለጥ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የአሪ ብሔረሰብ ከሚፈጽሟቸው ዓመታዊ ከበራዎች አንዱ ይህ ከበራ/አምልኮ ነው፡፡

የአሪ ህዝብ የጊዜ አቆጣጠር በሰዓት፣ በቀን እና በሳምንት የተለካ አይደለም፡፡ ነገር ግን አስራ ሁለት ወራት አሉት፡፡ ወራቶቹም የሚቆጠሩት በጨረቃ መታየትና መጥለቅ እንዲሁም በተፈጥሮ ክስተቶች መፈራረቅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የግንቦት ወር "ታብዛ" ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ ወር ላይ በሪ ትገለጣለች ተብሎ ስለሚታመን የወሩ ጨረቃ በታየበት ማግስት ከባቢው ቤት አምልኮ ይፈጸማል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ብሔረሰቡ የአማርኛውን አቆጣጠር እየለመደ በመምጣቱ ጨረቃን ሳይጠብቅ ግንቦት አንድ ላይ የዓመቱን ከበራ ይፈጽማል፡፡

በዚህ ጥናት ለመመልከት እንደቻልኩት በዘንድሮው ግንቦት አንድ 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ጀምሮ የስርዓቱ መሪዎች የተባሉት ጐድሚዎች፣ የባቢው ቤተሰቦች እና ጐረቤቶች ከባቢው ግቢ ተሰብስበዋል፡፡ ሴቶች ቡናና በቆሎ በመቁላት፣ ቀጠማ በመጎዝጎዝ እና ስኒ በመደርደር ስራ ከስርዓቱ እየተሳተፉ ነው፡፡ ባቢውና ጎድሚዎች ከአካ ውስጥ ሆነው ባቢውና ጎድሚዎች ባዋጡት ገንዘብ የተገዛን የመስዋዕት በግ አርደው አንጀት ማንበብ ጀመሩ፡፡ አንጀቱንም አንብበው መልካም ምልክት መታየቱን በፊታቸው ፈገግታ ከገለጹ በኋላ እሳት አቀጣጥለው የበጉን ጉበት ጠብሰው በሉ፡፡ ቀጥለውም ወደ አድባር ዛፍ ስር በመሄድ ሌላ በግ አርደው አንጀቱንም አንብበው በደሙ ዛፉን ቀብተዋል፡፡ ከተፈላው ቡናና ከቦርዴ አንዳንድ ስኒ ወስደው ከዛፉ ስር ረጭተዋል፡፡ ከዚያም ባቢው ቆመው የሚከተለውን ፀሎት ሲፀልዩ ጎድሚዎቹ የጸሎቱን የመጨረሻ ሀረግ እየደገሙ ተቀበሏቸው፡፡

<u>አሪኛ</u>

| <u>ባቢው</u> | <u>ጎድሚዎች</u> |
|---|---|
| በሪ ሀድንቲ ሀንተክ፣ | |
| ፍጨግሮንታንክ ሀኘሮሚ ካየን፣ | ሀኘሮሚ ካየን |
| ደኤም፣ ቃምዕረም፣ ዳቐም ካይስክ፣ | ምን ካይስክ |
| ቆልማዎንተም፣ ፍጨዎንተም፣ | |
| ይንሲዎንተም አንጅክ፣ | ምን አንጅክ |
| ቦንንከን ላቕሚ ዎም ዣዕሽክ፡፡ | ላቕሚ ዎም ዣእሽክ፡፡ |

## አማርኛ

በሪ በመምጣትሽ

| | |
|---|---|
| ከሀገራችን በሽታ ይጥፋልን፣ | ይጥፋልን |
| ሞት፣ድህነት፣ረሃብ ይወገድልን፣ | አዎ ይወገድልን |
| ከብቶቻችንን፣ ሀገራችንን | |
| ልጆቻችንን ባሪክልን፣ | አዎ ባሪክልን |
| ለከርሞ በሰላም አድርሽን። | በሰላም አድርሽን |

ይህን ፀሎት ከጨረሱ በኂላ ከተጠበሰው ጉበት ወስደው ከአድባሩ ስር በተኑ። ከዚያም ሴቶች ወዳዘጋጁት የቡና ስርዓት በመሄድ ባቢው ከበቆሎ ቆሎ እየበተኑ ከላይ የፀለዩትን ፀሎት ደግመው ሲጸልዩ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ቃሉን በመድገም ተቀበለ። ከቡናውም አንድ ስኒ ተቀድቶ ከአድባሩ ስር ከረጩ በኂላ እንዲጠጡና እንዲበሉ ፈቀደላቸው። ቡናውን ሲጠጡና ቆሎውን ሲበሉ እንደየክብራቸውና እድሜያቸው ደረጃ ቅደም ተከተል ነው። በመጨረሻም ባቢው “በሪ በሰላም መጥታ ቂም ሳትይዝብን በሰላም ትመለስ! የከርሞ ሰዎች ታድርገን! ሰላምና ፍቅር ለሀገራችን ይሁን!...” ሲሉ ህዝቡም ቃሉን በመድገም ተቀበሉትና ተበታተኑ። ከዚያም ግማሹ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከሴቶች የተመረጡ፣ ጎድሚዎች እና የአካባቢው ሽማግሌዎች እዚያው ቀሩ። የቀሩበትም ምክንያት አንጀት ለማንበብ እና እንደመስዋዕትም የታረደውን በግ እነዚህ ሰዎች እንደሚበሉ ባቢው አቶ ድክሳ አስፍን ነገሩኝ።



አቶ ድክሳ አስፍን(የምባ ባቢ) አድባር ስር ቡናና ቦርዴ ሲረጩ

በዚህ ዕለት ከባቢው ቤት በሚደረገው ክዋኔ ላይ ያልተገኙት ጉደሚዎች (ከባላባቱ ራቅ ብለው ያሉ) “በየቤታቸው በራሳቸው አካ ውስጥ በግ አርደው አንጀት አንብበው ስርዓቱን ይፈጽማሉ፤ ነገ እዚህ መጥተው በአንጀት የታያቸውን ምልክት (ክፉ ወይም መልካም) ይነግሩኛል፡፡” ሲሉ ባቢው ገልጸውልኛል፡፡

በአጠቃላይ በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የሚፈፀመው ከበራ በዋናነት በባቢው መሪነት(ከዋኝነት) ሲሆን ጉድሚዎች፣ ጎረቤቶች፣ ሴቶችና የአካባቢው ሽማግሌዎች ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ እስከ ወሩ መጨረሻ ባሉት ቀናት በአንዱ በሪ በንፋስ መጥታ ከባቢው አካ ውስጥ ትገባለች ተብሎ ይታመናል፡፡ በዋናነት ግን ከወሩ በመጀመሪያው ቀን ትገለጣለች ብለው ስለሚያምኑ ቀኑን ሙሉ ከላይ የተገለጹትን ክዋኔዎች እየፈጸሙ ይውላሉ፡፡ የበሪ መምጫ ምልክት በአካባቢው ኃይለኛ ንፋስ መከሰት ነው፡፡ ይህ ንፋስ ሲከሰት መምጣቷን ያረጋግጣሉ፡፡ በዚሁ ቀን ካልተገለጠችም አምልኮውን ጨርሰው ይለያያሉ፡፡ ይህን መረጃ ያገኘሁት የዕለቱን ምልከታ ከማጠናቀቁ በፊት ባቢውን እና የባቢው አንጋሽ (አማካሪ) የሆኑትን አቶ ሞላ በሪዶይዳብን ባደረኳቸው ቃለ መጠይቅ ነው፡፡

### 4.5.6. በወሊድ ጊዜ

የአሪ ብሔረሰብ ከሚያከብራቸው የሽግግር ከበራዎች ውስጥ አንዱ ይህ አጋጣሚ ነው። በምባ አሪ ብሔረሰብ አንዲት እናት ካረገዘችበት ዘጠነኛ ወሯ ጀምሮ ከቤተሰብ ተለይታ በልዩ ጎጆ (ጎዳይ) ውስጥ ትኖራለች። እርጉዝ እናት ከ8ኛ ወሯ ጀምሮ ከማንኛውም ማህበራዊ ስብሰባዎች ትከለከላለች። ከዘጠነኛ ወሯ ጀምሮ ደግሞ ከባሏም ከልጆቿም ተለይታ በዚሁ ጐጆ ውስጥ ትቆያለች። ጎዳይ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ወልዳ ከቤተሰቦቿ እስክትቀላቀል ድረስ ምግብ፤ ውሃ እና ሌሎች አገልግሎቶችንም የምታቀርብላት ሴት ልጅ (ለጋብቻ ያልደረሰች) ብቻ አብራት ትኖራለች። ይህችም ልጅ የጎረቤት ወይም የዘመድ ልጅ እንጂ የወላዷ ልጅ መሆን የለባትም።

የእርግዝና ወራቷን ጨርሳ ስትወልድ "ጋሳ ማን" ከሚባለው ማታ አንዲት ሴት ተጠርታ የህፃኑን እትብት ቆርጣ ከወራጅ ወንዝ በተቀዳ ውሃ አጥባ ለእናት ትሰጣለች። ይህን ሁሉ ካደረገች በኋላ ወደ ጓሮ ወጥታ ከእንሰት መካከል መርጣ በቅጠሉ ላይ እጇን ትጠርጋለች። የወላዷ ባልም እንሰቱን ቆፍሮ ይሰጣታል። ይህም ላደረገችው መልካም ትብብር የሚሰጥ ክፍያ ነው ማለት ነው። ከ"ጋሳ ማን" የሚመረጥበት ምክንያትም ይህ ማታ ዝቅተኛ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ስለሆነ የወላዷን ቆሻሻ እነሱ እንዲጠርጉ በማሰብ ነው። ወላዷ ከመውለዷ አንድ/ሁለት ወር በፊት በበሪ የተያዘች ስለሆነች በአንዳንድ ማህበራዊ ስብሰባዎች (ገበያ፤ ለቅሶ፤ ሠርግ፤ የከበራ ቦታዎች…) ላይ ስትገኝ ምናልባት ተገፍትራ/ተደናቅፋ ብትወድቅ "በሀገራችን ላይ እርግማን ይሆናል።" ተብሎ ስለሚታመን ከጐጆዋ ርቃ እንድትሄድ አይፈቀድም። ከቤተሰብ ተለይታ የምትኖርበት ምክንያት ደግሞ ወሯ እያለቀ ስለሆነ ምናልባት ቤት ውስጥ ከወለደች ቤቱ፣ ቤተሰቧቿ እና "ማል" ይረክሳሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ከወ/ሮ ሾሺ ጉስታብ[14] ያገኘሁትን መረጃ እንመልከት፡-

> አንዲት ሴት ልትወልድ ወሯ በደረሰ ጊዜ በተዘጋጀላት ጎዳይ ውስጥ ትገባለች። በገበያ፣ በስብሰባ፣ በማንኛውም ጉዳይ ብዙ ሰዎች በሚገኙበት ቦታ ላይ እንድትገኝ አይፈቀድም። ሰው ገፍትሮኣት ከወደቀች "በበሪ የተያዘች ተገፍትራ ወደቀች" ሲባል በሀገር ላይ እርግማን ይሆናል፤ ልጅ አይበረክትም። ይህች ሴት ከማህበራዊ ኑሮ ብቻም ሳይሆን ከቤተሰብ መካከልም ትለያለች። ቤት ውስጥ ከወለደች የበሪ ማምለኪያ የሆነው ማል ይረክሳል። ስለዚህ በጎጆዋ (ጎዳይ) ውስጥ በተመደበችላት ልጅ አማካይነት እየተቀለበች ልጇ ጥርስ እስኪያበቅል ድረስ ትቆያለች። ህፃኑን አጥባ እትብት ቆርጣ የምትሰጠው ደግሞ ከ"ጋሳማን" የሆነች ሴት ናት። ከወለደች በኋላ ምግብ ራሷ አንስታ የማትበላበት ጊዜም ድሮ ነበር። አብሮአት ያለችው ልጅ ታጎርሳታለች። በአጋጣሚ ልጅቱ በሌለችበት ሰዓት መብላት ብትፈልግ እንኳ በአፏ

14 የ92 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ በበሪ አምልኮ ውስጥ ሴቶች ስላላቸው ቦታና ሚና ሰፊ እውቀት ያላቸው፣ የስድስት ልጆች እናትና የቆሬትር ንውስ ቀበሌ ነዋሪ አዛውንት ናቸው። የአቶ ግንጀሎ ሐቾዳኪ ባለቤት ናቸው።

እንጂ በእጇ አንስታ አትበላም፡፡ አሁን አሁን ግን ይህ የማጉረሱና በአፍ አንስቶ የመብላቱ ባህል ቀርቷል (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2004)፡፡

ወላዷ እናት ምግብ በእጇ አንስታ የማትበላበት ምክንያት በብሔረሰቡ እምነት አንዲት እናት ከወለደችበት ጊዜ ጀምሮ ልጇ ጥርስ እስኪያበቅል ጊዜ ድረስ "ሪክሳለች" ተብላ ስለምትፈረጅ ነው፡፡ እርኩሰቷ በወሊድ ጊዜ እና በኋላ በሚኖራት ፈሳሽ ምክንያት ነው፡፡ ቤት ውስጥ የማትወልድበትና ከባሏ ጋርም እንዳትገናኝ የሚደረገው ከዚህ ፈሳሽ ለመንጻት ሲባል ነው፡፡ ከባሏም አትገናኝም (ግብረ ስጋ ግንኙነት አለመፈጸም ብቻ ሳይሆን በዓይንም መተያየት አይቻልም)፡፡

የልጇ ጥርስ መብቀል እስኪጀምር ድረስ ህፃኑን አጥባ እትብት ቆርጣ የሰጠችው ሴት በየወሩ እየመጣች ፀጉሯን በትንሽ በትንሹ ትላጫታለች፡፡ በአምስተኛው /በስድስተኛው ወር ልጁ ጥርስ ሲያበቅል ሙሉ በሙሉ ትላጫታለች፡፡ ለብዙ ወራት ተለይታ ከቆየችበት ጎዳይ (ጎጆ) ወጥታ ወደ ቤቷ የምትገባበት ከባሏም ከልጆቿም የምትገናኝበት ጊዜ ስለደረሰ ሁሉም ደስ ይለዋል፡፡ ባልም በቤት ውስጥ ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ዝግጅቱ ሚስቱ ከአዲስ ልጇ ጋር የምትተኛበትን ቦታ፣ ምግብን እና ጎረቤት መጥራትን ያካትታል፡፡

የቤት ውስጥ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከጎዳዩ በር ላይ ባሏ እግሩን ከፍቶ ይቆማል፡፡ ሚስቲቱም ከነልጇ ከእግሩ ስር ሾልካ ትወጣለች፡፡ ወደ ዋናው ቤት ስትገባም በር ላይ ባሏ እግሩን ከፍቶ ከእግሩ ስር ሾልካ ትገባለች፡፡ እንደገባችም ጎዳዩ (ጎጆው) በእሳት ይቃጠላል፡፡ ቤተሰቡና ጎረቤት ተሰብስበው የደስ ደስ ቡና ተፈልቶ ይጠጣሉ፤ "በሪ እንኳን ማረችሽ!" ይሉአታል፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ደስታቸውን ከገለጹ በኋላ ለህፃኑ ስም መሰየም ይጀምራሉ፡፡ ስም አሰያየሙ ከተለያዩ አጋጣሚዎች /ምክንያቶች ጋር የተያያዘ ሆኖ ሁሉም ቤተሰብ ስም ይሰይማል፡፡ ከነዚህም ሁሉን የሚያስደስት ሆኖ የተገኘው ይጸድቃል፡፡ ራሱን የቻለ ስም የማውጣት ስርዓት ቢኖርም ይህ ጥናት ባተኮረበት አካባቢ ስለማይዘወተር በዚህ ጥናት አልተካተተም፡፡

ባሏ ከጎዳዩና ከዋናው ቤት በር ላይ እግሩን ከፍቶ ሚስትም ሾልካ በመውጣቷ ርኩሰቷ ተወግዷልና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወላዷ በማንኛውም ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ትችላለች፡፡ በጎዳይ ውስጥ በምትቆይበት ጊዜ ከባሏና ከባ እንዲሁም ከጎድሚዎች ጋር በምንም አይነት ሁኔታ እንድትታይ አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ከእነዚህ ሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት በሁለት መንገድ ሲታይ አንድም፣ ከባሏ ጋር ስትታይ (በዓይን ስትገናኝ) ባል በፍትወት ስሜት እንዳይጎዳ እና ወደ

ሌላ ሴት እንዳይሄድ ለመጠንቀቅ፤ አንድም፣ ባቢና ጎድሚዎች ቅዱስ የበሪ መንፈስ ያረፈባቸው ናቸው ተብለው ስለሚታመኑ እነሱን ባየች ጊዜ መንፈሳቸውን ታረክስባቸዋለች፤ በእነሱ መንፈስ መርከስ ደግሞ እሷም ልጇም ይቀሰፋሉ፡፡ በተለይ ልጇ ሊሞትባትም ይችላል፡፡ ስለዚህም አብሮአት ያለችው ልጅ ከጎጆዋ አጠገብ ማንም ዘው ብሎ እንዳይመጣ የመጠበቅ ኃላፊነትም አለባት፡፡ ሰዎች ሲመጡም ወላዷንም መጨዎቹንም ታስጠነቅቃቸዋለች፡፡

ወላድ ሴት ልጇ ጥርስ እስኪያበቅል ድረስ ከብዙ ነገር ትከለከላለች፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ነገሮች በተጨማሪ የከብት ወተት እንድትጠጣ አይፈቀድም፡፡ ይህም ወተቱን ከጠጣች ወተት የምትሰጠው ላም እና ጥጃዋ "በበረት አይበረክቱም" ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ወተት ብቻም ሳይሆን የምንጭ ውሃ እንድትቀዳና ማር እንድትበላ አይፈቀድም፡፡ የምንጭ ውሃን እንዳትደርስ /እንዳትቀዳ የምትከለከለው በእምነቱ ዘንድ የምንጭ ውሃ "የበሪ ውሃ" ተብሎ ስለሚታመን ይህች በወሊድ የረከሰች ሴት እንዳታረክሰው ለመጠንቀቅ ነው፡፡ ማር የማትበላበት ምክንያት እንደ ላሟ "የንብ ቀፎው አይባረክም" በሚል እምነት ነው፡፡ የልጇ ጥርስ መብቀል ሲጀምር እና ከጎዳይ ወጥታ ወደ ዋና መኖሪያ ቤቷ ከገባች በኂላ ባሏና አንድ ከአካባቢው የተከበረ ሰው አብረው በመሆን ደረቅ የእንሰት ቅጠል በእንጨት ጫፍ ላይ አስረው ከምንጩ ዳር ተክለው ከስሩም እበት ጨምረው በሪን ተለማምነው ይሄዳሉ፡፡ የሚለምኑትም "ከዚህ በኂላ አትፀየፊያት፤ ልጇ ጥርስ አብቅሏል፤ እሷም ልጇም ያንችው ናቸውና ተቀበያቸው፤....፡፡" እያሉ ነው፡፡ ይህን ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ አራሷ እናት ወተት፣ ማር እና የምንጭ ውሃን ሳትሳቀቅ እንድትጠቀም ይፈቀድላታል *(ቃለ መጠይቅ፣ ወ/ሮ ሾሺ ጉስታብ፣ 12/2004)*፡፡

## 4.5.7. ላም ስትወልድ

ይህ ከበራ ከምስጋና ማቅረቢያ ከበራ ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ አንድ ሰው (ወጣት/አዋቂ) ጊደር ከገዛ በአባቱ አስመርቆ ማርባት ይጀምራል፡፡ የማስመረቁ ተግባርም የባለ ጊደሩ (የባለ ላሙ) ባለቤት አባቱን ጠርቶ "ጊደር/ላም ገዝቻለሁና ባርክልኝ፡፡" ይለዋል፡፡ አባትም ደስ ብሎት የመባረኩን ሥራ ያከናውናል፡፡ ስለመባረኩ ስርዓት ሂደት ከስንጋመር ንዑስ ቀበሌ አቶ ካይኪ ታውሳ[15] የሰጡኝን መረጃ በዝርዝር እንመልከት፡፡

---

[15] የ 80 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ የዘጠኝ ልጆች አባት፣ በማንኛውም አምልኮ ጊዜ እንደ ጎድሚዎች ከባላባቱ ጋር የሚሳተፉ፣ ስለ እምነቱ በቂ እውቀት ያላቸው የስንጋመር ንዑስ ቀበሌ ነዋሪና የሀገር ሽማግሌ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች አንዱ ናቸው፡፡

> አንድ ሰው ጊደር /ላም ከዛ አባቱ ባርኮ ይሰጠዋል፡፡ የመባረኩ ስርዓትም ካሺ ይባላል፡፡ በካሺ ጊዜ አባትዬው የእንሰት ግንድ ከትፎ ጨው ነስንሶበት ለጊደሯ /ላሚ ይሰጣል፡፡ ከጭራዋ ቆርጦ ደግሞ በቤሪ ጫካ ውስጥ ይጥላል፡፡ ገመዷን ይዞ ምራቁን ተፍቶበት “በረት ትሙላልህ! ልጆችህን ታሳድግልህ/ትቀልብልህ!....” ብሎ መርቆ ለልጁ ይሰጠዋል፡፡ ጊደሯ/ላሚ በወለደች ጊዜ ደግሞ ሦስት ወይም አራት ትላልቅ ቅል (ጉሲ) ውስጥ ወተቷ ታልቦ በአካ ውስጥ ይሰቀላል፡፡ ከዚያም ባለቤቱ አባቱንና የከብት ጎድሚን ጠርቶ በግ አርዶ አንጀቱን ካነበበ በኋላ የበጉን ጉበት እና ወተቱን ይቀምሳሉ (ጫካው ውስጥ)፡፡ በአካው ውስጥ የተሰቀለውን ወተት እና የታረደውን በግ ከጎድሚውና ከተመረጡ የአካባቢው ሽማግሌዎች ጋር ከበሉና ከጠጡ በኋላ በቤት ውስጥ እንደገና ወተት ማጠራቀም ይጀምራል፡፡ በቅልም ሆነ በጋን አድርጎ ካጠራቀመ በኋላ የመጀመሪያ ሰዎቹ (ጎሚድ፣ አባት፣ ሽማግሌዎች ) እና ቤተሰቦቹ በሙሉ ተሰብስበው የበግ አንጀት ተነቦ በተመሳሳይ መልኩ ጎድሚው እና አባት መጀመሪያ ይቀምሳሉ፡፡ ከዚያም ባለቤቱ ቀምሶ ለሚስቱ፣ ሚስትም ቀምሳ ለመጀመሪያ ልጃቸው፣ እንዲህ እንዲህ እያሉ እስከ መጨረሻ ልጃቸው በየተራ ይቀምሳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 18/2004)፡፡

በአካ ውስጥ በ ሚከናወኑ ማን ኛውም አ ምልኳዊ ክንዋ ኔዎች ላይ ሴቶች እና ልጆ ች አይሳተፉም፡፡ በአካ ውስጥ ወተት ተቀመሰ ማለት ደግሞ ከአሁን በኋላ ማንም እንደፈለገ ወተት ይጠጣል ማለት አይደለም፡፡ ማንም እንዲጠጣ የሚያስችለው የቤት ውስጥ ቀመሳ ሲካሄድ ነው፡፡ ምክንያቱም የእድሜ ደረጃ ልዩነት ትልቅ ቦታ ስለሚሰጠው ሁሉም በእድሜው ቅደም ተከተል መቅመስ አለበት፡፡ የቤት ውስጥ ቀመሳም(ካለግር) ዋና አላማው ይህን ስርዓት ማስጠበቅ ነው፡፡ ካልሆነ ግን ማንም ከታላቅ ወንድም/እህት ቀድሞ ቢቀምስ ይቀሰፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ የቅድምና እምነት በዚህ ብቻም ሳይሆን በብዙ ነገሮች ላይ ይገለጻል፡፡ በባህሉም “ቶይድሚ” ይባላል፡፡

“ቶይድሚ/ቶይዲ” ማለት ታላቅነት/ታላቅ ማለት ሲሆን እርከኑም ከአባት ይጀምራል፡፡ በቤተሰብ ውስጥ አባት/ባል በህይወት ከሌለ ደግሞ የአባት ወንድም ወይም ከልጆች መካከል ታላቅ ወንድ ልጅ ቶይዲ ይሆናል፡፡ ቀጣይዋ ቶይዲ ምን ጊዜም ሚስት/እናት ነች፡፡ ስለሆነም በቤት ውስጥ ከእህልም ሆነ ከስጋ (የታረደ /የተገዛ) አባት/ታላቅ ወንድ ልጅ ያልቀመሰውን ሚስት/እናትም ሆነች ሌሎች ልጆች መቅመስ አይችሉም፡፡ ይህ ስርዓት በቤተሰብ መካከል ብቻ የሚተገበር ሳይሆን በማህበረሰቡ ዘንድም ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ወጣቶች ያረዱትን ሽማግሌዎች ይፀየፋሉ፡፡ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ላይም የዕድሜ ባለጠጋ ለሆኑ አዋቂዎች ልዩ ክብርና ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ ሲጠሩም “የታ/ኬታ” (እርሶ/እርሳቸው) ተብለው እንጂ በስማቸው አይጠሩም፡፡ በቤተሰብ ውስጥ ባለው ቶይድሚ በግና ፍየል ሲታረድ ቶይድው ጉበቱን አካ ውስጥ ጠብሶ ይቀምሳል፡፡ ቆርጦም ከአካው ውስጥ ይጥላል፡፡ ዋናው ስጋ ሲቀቀልም መጀመሪያ የሚጎርሰው ቶይዲው ነው፡፡ ስለሆነም በአጭሩ ቶይዲ ማለት የቤተሰብ ጎድሚ ማለት ነው፡፡

ከላይ አቶ ካይኪ ታውሳ በሰጡኝ መረጃ ውስጥ እንደተመለከትነው ቤት ውስጥ ጊደር/ላም ስትወልድ ዝም ተብሎ አይጠጣም፡፡ በአካ ውስጥ አስፈላጊው መስዋዕት (በግ) ቀርቦ የቤተሰብና የማህበረሰቡ ጎድሚዎች ቀምሰው አስፈላጊውን አምልኮ ከፈጸሙ በኋላ በጠቅላላው ቤተሰብም ከተመለከ በኋላ ይጠጣል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ነገር መመልከት ይኖርብናል፡፡ ይህም የቤተሰብ አባላቱ ወተት በሚቀምሱበት ጊዜ ወተቱን የሚይዙት በዋርካ ዛፍ ቅጠል ውስጥ ነው፡፡ በአንድ የዋርካ ቅጠል ውስጥ ወተቱ ተሞልቶ ጎድሚ ቀምሶ ለላሟ ባለቤት፣ ከባለቤቱ ሚስቱ፣ ከሚስቱ ለልጆቻቸው በየተራ እየደረሳቸው ሲቀምሱ ወላድ /አራስ ሴት ከሆነች ደግሞ በእንሰት ቅርፊት (ሾዳ) ውስጥ ትጠጣለች፡፡ በዋርካ ቅጠል ውስጥ ለምን እንደሚጠጣ አቶ ካይኪ ታውሳ "ጊደሯ/ላሟ እንደዋርካ እንድትወፍር፣ ወተት እንድትሰጥ እና በአጠቃላይ እንድትባረክ ከማሰብ የተነሳ ነው" ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ በዚህም መሠረት ላሟ ብዙ እንድትወልድ፣ ምን ጊዜም ወተት እንዲኖራት እና ጤንነቷም የተጠበቀ ሆኖ እንዲቆይላት ባረኩአት ማለት ነው፡፡ አራሷ ሴት በእንሰት ቅርፊት ውስጥ የምትጠጣበት ምክንያትም ሴቶች ከእንሰት ተክል ጋር ባላቸው የጠበቀ ቁርኝት (ተክሉን በአብዛኛው የሚያለሙት እነሱ ናቸው) እና ወላድ ሴቶች እንደ እንሰት እንዲለመልሙ (ጤነኛ እንዲሆኑ) ከመመኘት ጋር በተያያዘ እምነት ነው፡፡

ከወተት መቅመሻ ዕቃው ጋር ተያይዞ ወ/ሮ ጋበትከን ካሚን (የዝናብ ጎድሚ) ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ የሰጡኝ አስተያየት ወተት በዋርካ ቅጠል/በእንሰት ቅርፊት ውስጥ የሚቀመሰው በወተት ቀመሳ ጊዜ እነዚያ "የበታች ዘር" የተባሉት ሳይጠሩ ምናልባት ድንገት ቢመጡ በቤት ቁሳቁስ ውስጥ እንዳይጠቀሙ ለማድረግ እንደሆነ ነው፡፡ በአብዛኛው ኑሮአቸውን የሚያስተዳድሩት ከተቃራኒው ዘር (ማታ) ቤት የጉልበት ሥራ በመስራት ስለሆነ በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ላይ ይመጣሉ፡፡ መጥተው በር/ደጅ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜም በቤት ውስጥ በየተራ ሲቀመስ የነበረው ወተት መጨረሻ ላይ ለእነሱ ደጅ ላይ ይሰጣቸዋል፡፡ የዋርካ ቅጠሉም በዚያው ይጣላል፡፡ በቤት ውስጥ ዕቃ (ብርጭቆ፣ ሾርቓ፣ ቅል...) ቢቀመስ ኖሮ እነዚያም ሰዎች በነዚሁ ዕቃዎች ስለሚቀምሱ ዕቃዎቹ "ይረክሳሉ" ተብሎ ስለሚታመን ይጣላሉ፡፡ ስለዚህም የቤት ዕቃ እንዳይጣል በዋርካ ቅጠል ውስጥ ይቀመሳል፡፡

በዘር ልዩነት የሚከናወኑ እምነታዊ ጉዳዮችን በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ማንሳታችን ይታወሳል፡፡ ማናዎች ከቓንሣዎች ቤት ገብተው መብላት አይችሉም፡፡ ቓንሣዎች ከማናዎች ቤት ገብተው አይበሉም፡፡ በጋብቻም አይተሳሰሩም፡፡ ማናዎች ቤት ባይገቡም በር/ደጅ ላይ ሆነው "ርካሽ/ተራ" ተብሎ በሚታመን ዕቃ (ቁሳቁስ) ውስጥ ከቓንሣዎች መብላት የሚችሉ ሲሆን

ከማናዎች ቤት ግን ማንኛውንም አይነት ምግብ/መጠጥ በማንኛውም አይነት ዕቃ ውስጥ ቓንሣዎች አይበሉም፤ አይጠጡም ፡፡

ማናዎች የበሪን አማልክትነት አያምኑም፤ የበሪ፣ ለበሪ፤ የሚሉት ነገርም የላቸውም፡፡ በሪን ብቻ ሳይሆን በብሔረሰቡ ዘንድ የሚመለኩ አማልክቶችንና እምነቶችንም (ሳቢ፣ ጸይሲ፣ ቡንካ…) አያምኑም፡፡ በአናሳነት ስለሚፈረጁ በሀገረ-ሰባዊ እምነቶችም ሆነ በመደበኛ ሃይማኖቶች (ከፕሮቴስታንት በስተቀር) ውስጥ መቀላቀል አይችሉም፡፡ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ግን ፍላጎቱ ያላቸውን ማናዎች ይቀበላል፡፡ ይህንንም ሃይማኖት የማይከተሉ በርካታዎች ይገኛሉ፡፡ ፕሮቴስታንት የሆነ ማና ፕሮቴስታንት ከሆነው ቓንሣ ቤት ገብቶ በአንድ ማዕድ መቁረስ ይችላል፡፡ ቓንሣም ከማናው ቤት ገብቶ ይበላል፤ ይጠጣል፡፡ አብረው መተኛትና መቀመጥም ይችላሉ፡፡ ይህ ሲባል ግን ማናው ፕሮቴስታንት ሆነ ማለት በጋብቻም ከቓንሣ ጋር ይጣመራል ማለት አይደለም፡፡ ጋብቻን ብቻ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትም ይከለክላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ለአሪ ብረሔረሰብ ያለው ፋይዳ

### 5.1. ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ

የበሪ እምነት በተለያየ መልኩ በአሪ ብሔረሰብ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ብሔረሰቡ በበሪ ባለው እምነት የተነሳ ክፋውም ደጉም ከበሪ እንደሆነ አስቀድሞ ይፈርጃል፡፡ ስለሆነም በምንም ዓይነት መንገድ በሪን ላለማስቀየም ይተጋል፡፡ በትጋቱ ውጤትም ደስታንና እፎይታን ያገኛል፡፡ ለበሪ ማድረግ ያለበትን በማድረግ፤ አስፈላጊውን መስዋዕት በማቅረብ፤ በእምነቱ የተከለከሉ ድርጊቶችን ባለማድረግ ንፁህ የእምነቱ ተከታይ በመሆን ሰላማዊ ኑሮውን ይፈጥራል፡፡

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከእምነቱ ተከታይ የሚጠበቁ በርካታ ክዋኔዎች አሉ፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች ዋናው አስፈላጊነታቸው የግለሰቡን/የአማኙን ነፍስ በእርጋታ ለማኖር ነው፡፡ የአሪ ብሔረሰብ በበሪ የሚያምነውና ለእምነቱም የሚፈጽመው አምልኮ ለራሱ እና ለቤተሰቦቹ ሰላም መረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ለመጪው ትውልድ እና አሁን ላለበት ማህበረሰብ ጭምር ሰላማዊ ሕይወትን ለመፍጠር ነው፡፡

የአሪ ብሔረሰብ "ንብረቴ ይዘረፋል/ይሰረቃል" ብሎ እንዳይሰጋ ሀገረ-ሰባዊ እምነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በሪን በንብረቱ ላይ በማኖር በቀላሉ ይከላከላል፡፡ በሪን የማያኖርበት (ከብት፣ የቤት ቁሳቁስ፣ ገንዘብ.....) ቢሰረቅ እንኳ በእምነቱ ዘንድ ከባድ እርግማን ስለሚፈጸም ሌባው በቀላሉ ይያዛልና ጭንቀት አይገባውም፡፡ በዚህ እና በመሳሰሉት መንገዶች ብሔረሰቡ ከፍተኛ የመንፈስ እረፍት ያገኛል፡፡ በራስ መተማመንንም ይፈጥራል፡፡ ስጋቱን ይቀንስለታል፡፡ *(በቡድን ውይይት ጊዜ አቶ ካይኪ ታውሳ፣ 21/05/2004)*

### 5.2. ፖለቲካዊ ፋይዳ

የአሪ ብሔረሰብ በግልም ሆነ በቡድን የሚፈጽመው የበሪ እምነት ፖለቲካዊ ገጽታና ጠቀሜታም አለው፡፡ ከ ስርዓት-አምልኮው መዋቅር ተ ነስተን ስንተ ረጉም የተ ለያዩ የስልጣ ን እርከኖች አሉበት፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ባቢ በምባ አሪ ብሔረሰብ ዘንድ የፖለቲካም የእምነታዊ አሰራሮችም መሪ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ፖለቲካዊ ስልጣኑ (የመሬት ባለቤትነት፣ የአስገባሪነት ስልጣን) የቀረ ሲሆን የእምነታዊ ከበራዎችን መሪነት እንደጨበጠ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በበሪ እምነት ውስጥ ባቢ ዋናው መሪ ሆኖ ይታመናል። ከባቢ ቀጥሎም በአንዳንድ ተፈጥሯዊ ክስተቶች ላይ ስልጣን ያላቸው ጉድሚዎች አሉ። በከበራ ጊዜ ህዝቡን የሚያስተባብሩና ደንብ የሚያስፈጽሙ እንዲሁም ለባቢው መረጃ አቀባይ ሆነው የሚያገለግሉ ደግሞ "ጋናዎች" ይገኛሉ።

እያንዳንዱ ግለ-ሰብ በቀጥታም በሪን ማምለክ የሚችልበት ሁኔታ አለ። በቀጥታ በሪን ማምለክ ከቻለ ደግሞ በእምነቱ ዘንድ የክብር እርከን የተቀመጠው ምናልባትም ስርዓተ-አምልኮው ሂደታዊ እንዲሆን እና ቀድሞ ስርዓቱ ለፖለቲካ አላማም ያገለግል ስለነበር ፖለቲካዊ ስልጣኑን ጫን አድርጎ ለመጠቀም ከመፈለግ የተነሳ ሊሆን ይችላል። በዚህ ላይ የብሔረሰቡ አባላት የሚሰጡት አስተያየት ግን የለም። ይህ የስልጣን እርከን በእምነቱ መሪዎች መካከል ብቻ የሚታይም አይደለም። በቤተሰብ ደረጃም በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ አንድ የቤተሰብ መሪ ሲኖር ሌሎች እንደየዖታቸውና ዕድሜያቸው ተከታይ መሪዎች ይሆናሉ። በቤተሰብ መካከል ያለው የስልጣን እርከን ከላይ እንዳየነው የእምነቱ መሪዎች ስልጣን፣ አንዱ አንዱን አልፎ ስርዓቱን መፈፀም አይችልም። በመሪዎቹ ዘንድ ጉድሚ ብቻውን በማምለክ ዝናብ ማዝነብ የሚችል ሲሆን በቤተሰብ ዘንድ ግን አባት በሕይወት እያለ ልጅ አካ ውስጥ መስዋዕት ማቅረብም ሆነ እህል መቅመስ አይችልም።

በአጠቃላይ የበሪ ሀገረ-ሰባዊ እምነት ለብሔረሰቡ ያለው ፖለቲካዊ ፋይዳ በብሔረሰቡ መካከል መከባበር እንዲሰፍን ከማድረጉ በተጨማሪ ወንጀልን በምንም ዓይነት መንገድ መደበቅ እንዳይቻል በማድረጉም ወንጀልን በእጅጉ ይከላከላል። ወንጀለኛ ራሱን አጋልጦ ይቅርታ ካልጠየቀ "በሪ በዚህ ቀን እንዲህ ታድርገው! ይህን ትላክበት!" ተብሎ ስለሚረገም ድብቅ ወንጀልና ወንጀለኛ እንዳይኖር ያደርጋል።

ስለዚህም የበሪን እርግማን በመፍራት ሁሉም የብሔረሰቡ አባል ወንጀልን ይሸሻል። በህግ ፊት በሀሰት መመስከርም በእምነቱ በጥብቅ የተከለከለ ነው። በሀሰት የተመሰከረበት ሰው ከበሪ ፊት ወድቆ ቢያለቅስ /ቢያነባ/ ሀሰት መስካሪው "ክብቶቹ ገደል ይገባሉ" ተብሎ ስለሚታመን ማንም ለሀሰት ምስክርነት አይደፍርም። ለትክክለኛ ምስክርነት ሀገረሰባዊ እምነት ያለውን ጉልህ ፋይዳ Morton (*1973:49*) "...While belief is an important variable, the nature of social relations between accused and the accuser prior to the dispute is likely to be more relevant in terms of the response of the accused." በማለት ገልጸውታል።

በአሪ ብሔረሰብ በሐሰት መክሰስንም ሆነ በሀሰት መመስከርን የበሪ እምነት በጽኑ ይቃወማል፡፡ ይህን የሚያደርጉ ቢኖሩም በመንፈስ ይቀሰፋሉ፤ ከብቶቻቸው ገደል ይወድቃሉ፣.... ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ደግሞ በብሔረሰቡ ዘንድ ትክክለኛ የፍርድ ውሳኔ እንዲኖር ለማስቻል ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ከዚህ ጋር አያይዞም ማንኛውንም ወንጀለኛ /ከነፍሴ ገዳይ በቀር/ በሌሎች የህግ አካላት እንዲቀጣ አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ ወንጀለኛው በቤተሰቦቹ፣ በጓደኞቹ እና በሚያውቁት ሰዎች ፊት በጉልበት ስራ /ለቀበሌ/ እና በሕዝቡ ፊት ቆሞ "እኔን ያያችሁ ተቀጡ! ከእንግዲህ አይለምደኝም!" ብሎ ድምፁን አውጥቶ እንዲናዘዝ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ከአካል ቅጣት በተጨማሪ ከባድ የስነ-ልቦና ቅጣትም ስለሆነ ሁል ጊዜ ወንጀልን እንዲፈራ ያደርገዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ስውር ወንጀል ሊኖር አይችልም፤ በቀበሌ ደረጃም ህግ አስከባሪዎችና አስተዳዳሪዎች የስራ ጫና አይፈጠርባቸውም፡፡ ወንጀለኛን ለህግ ለማጋለጥም ሆነ የጠፋ ንብረትን ለማስመለስ የዕለት ተዕለት መነጋገሪያ ማድረግ ሳያስፈልግ ለበሪ አሳልፎ በመስጠት /በመናዘዝ/ ብቻ ጥቂት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ይቻላል፡፡

## 5.3. ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

የበሪ ስርዓተ አምልኮ ለአሪ ብሔረሰብ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም አለው፡፡ ብሔረሰቡ ዋና የኢኮኖሚ መሰረቱ ግብርና እንደሆነ በምዕራፍ ሦስት ተገልጿል፡፡ የግብርና ስራውን ለማከናወን ከመወጠን ጀምሮ እስከ ምርት ድረስ በየወቅቱ አምልኮ ይፈጽማል፡፡ አስፈላጊው የአየር ጠባይ እንዲኖር፣ የሰብል ተባይ ወረርሽኝ እንዳይከሰት/እንዲጠፋ፣ ድርቅና ረሃብ እንዳይከሰት እምነቱ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ከዚህም ባሻገር ንብረት በከንቱ እንዳይባክንና እንዳይዘረፍ በሪን በማኖር ይከላከላል፡፡ ማንም የማንንም ንብረት ያለፈቃድ ወስዶ መጠቀም አይችልም፡፡ ይህ ደግሞ ሁሉም ሰው የራሱን ንብረት ብቻ እንዲጠቀም ከማድረጉም በላይ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን እንዲያጎለብት ያስችለዋል፡፡ የኢኮኖሚውም የህይወቱም ምንጭ በሪ እንደሆነች በማመኑ ሲሞላለት "በሪ ሰጠችኝ" ሲጎድልበት "በሪን ምን አስቀየምኳት?" እያለ ያመልካል፡፡

በብሔረሰቡ ዘንድ ሴቶች እንግዳ ሆነው ቤተ-ዘመድ ቤት ከሄዱ እህል ወይም ስራስር ይዘው እንዲመለሱ ባህሉ ያስገድዳል፡፡ አንዲት ሴት ከወንድሟ ወይም ከአባቷ ቤት በእንግድነት ሄዳ ባዶ እጇን አትመለስም፡፡ የሴቷ ቤተ-ዘመዶችም ሳይጠየቁ በፈቃዳቸው ከእህል ወይም ከስራስር ሰጥተዋት ይሸኟታል፡፡ ይህን የእንግዳ ማስተናገጃ ሀብት ለማግኘትና ለመጠበቅ የበሪ እምነት

ጉልህ ሚና ይጫወታል። ምክንያቱም በብሔረሰቡ እምነት ያለ በሪ ምንም ነገር ውጤት አይሰጥም። ዝናብና ፀሐይ፣ ድርቅና ረሃብ፣ ደስታና ጥጋብ፣ ማግኘትና ማጣት፣ ሕይወትና ሞት ከበሪ ናቸው ተብሎ ይታመናልና። *(ቃለ መጠይቅ፣ አደመ አሰፋ*[16]*፣ 30/08/2004)*

## 5.4. ስነ-ምግባራዊ ፋይዳ

የበሪ እምነት በቤተሰብ መካከልም ሆነ በማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የስነ ምግባር ትምህርት ይሰጣል። እምነቱ የሚፈቅዳቸውና የማይፈቅዳቸው በርካታ የስነ ምግባር ደንቦች አሉት። አንደኛው ታላቅን ማክበር ነው። እንደማንኛውም ለታላቅ የሚሰጠው ክብር አይነት (አንገት ዝቅ አድርጐ ሰላምታ መስጠት፣ ከመቀመጫ መነሳት፣ አንቱ ማለት...) ሳይሆን ከነ ስሙ ልዩ ቦታ የሚሰጠው የአክብሮት ስርዓት ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው "ቶይዲ/ቶይድሚ" ተብሎ በቤተሰብ መካከል ልዩ ክብር የሚቀዳጀው አባት ወይም ታላቅ ልጅ (ወንድ) ነው። አባት ያልቀመሰውን ማንኛውንም ነገር ልጆች አይበሉም። ከቤተሰብ ውጭም ቢሆን በእርድ ጊዜ በእድሜ ከፍ ያሉ አዛውንቶች እርድ መፈፀም አለባቸው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አነስተኛ ዕድሜ ያለው ጐረምሳ እርዱን ቢፈጽም አዋቂዎች ይሳቀቃሉ።

ከዚህ በተጨማሪም አጉል የሆኑ ድርጊቶችን በመቃወም ማህበራዊ ኑሮን ያጠናክራል። እምነቱ የሚከለክለውን ማንኛውንም ድርጊት ፈጽሞ የሞተ ሰው "የደርቲ ደእስ" (ተይዞ ሞተ) እየተባለ ለቅሶ ስለማይለቀስለት፣ አልቻ ስለማይበላለት፣ ወንጀል ቀርቶ ታላቅን ሳያማክሩ "ራበኝ" ብሎ መብላት በራሱ እስከሞት ያደርሳል ትብሎ ስለሚታመን ከፍተኛ የስነ ምግባር ጥንቃቄን ይጠይቃል።

[16] የ 70 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ የባላባት ድክሳ አስፍን ታናሽ ወንድምና በበሪ አምልኮ ስርዓት ውስጥ ያደጉ፣ የአምስት ልጆች አባት፣ በእርሻና በንግድ የሚተዳደሩ የውብሐመር ቀበሌ ነዋሪ ናቸው።

# ምዕራፍ ስድስት

## ማጠቃለያ

በደቡብ አሪ ወረዳ የአሪ ብሔረሰብ ከመደበኛ ሃይማኖቶች (ክርስትናና እስልምና) በፊት ጀምሮ በፈጠረው ሀገረ-ሰባዊ እምነት ለበሪ የተለያዩ አምልኳዊ ክዋኔዎችን ይፈጽማል፡፡ ሰፊ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ስነምግባራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለውን ይህን እምነት ከትውልድ ወደ ትውልድ በክዋኔና በአስተምህሮት ሲያስተላልፍ ኖሮ እያስተላለፈ ይገኛል፡፡

በበሪ እምነት አካ፣ አድባር እና ማል ዋና ዋና የከበራ/የአምልኮ ቦታዎች ሲሆኑ እንደየቅደም ተከተላቸው መስዋዕትና ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ እነዚህ ቦታዎች የሚገኙት ከእያንዳንዱ አማኝ ደጅ ላይ ሆነው በጫካ የተከበቡና ከአምልኮ ጊዜ ውጭ ማንም ከአጠገባቸው እንዲደርስ እንደማይፈቀድ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ሀገረ-ሰባዊ እምነቱ በዋናነት በባቢ(ባላባት) የሚመራ ቢሆንም ጎድሚዎች፣ ጋናዎች እና የቤተሰብ ቶይዲዎች በጋራ ወይም በተናጠል የሚመሩት ክዋኔዎችም አሉት፡፡ ከእነዚህም የእህል ቀመሳ፣ የከብት መመረቅ፣ የልደት ስርዓት፣ የበግ አንጀት ማንበብ፣ ንብረት ላይ በሪ ማኖር እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ በባላባት መሪነት ደግሞ በአየር ለውጥ ጊዜ፣ በተባይ ወረርሽኝ ጊዜ፣ እና በበሪ መምጫ (መገለጫ) ጊዜ የሚፈጸሙት ክዋኔዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የዎባ አሪ በሪን በማመን ለኢኮኖሚው መሰረት የሆነው የግብርና ስራ በአየር ንብረት መዛባት እንዳይስተጓጎልበት ያደርጋል፡፡ ለዚህም ገንዘብ አዋጥቶ ከጎድሚዎችና ከባላባት ጋር የበግ አንጀት በማንበብ እና ገልፊ (ሾጣጣ ድንጋይ) በእርጥብ ወይም በደረቅ ቦታ ላይ በማኖር ያመልካል፡፡ የተባይ ወረርሽኝ ሲከሰትም በባላባቱ አማካይነት አንጀት አንብቦ ተባዩንም በምጣድ ቆልቶ በአንዱም ቂጥ እንጨት ሰክቶና ረግሞ ያሳድደዋል፡፡ በዚህም ከብቶቹን፣ ሰብሉን እና ቤተሰቦቹን ከወረርሽን እንደሚከላከል ይታመናል፡፡ በየዓመቱ ግንቦት ወር ላይ የእምነቱ አማልክት የሆነችው በሪ (በረን) ከሩቅ አካባቢ መጥታ በባቢው አካ ውስጥ በንፋስ ትገለጣለች ተብሎ እንደሚታመን ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

ይህ የበሪ እምነት በአሪ ብሔረሰብ መከባበር/መቻቻል እንዲኖር፣ ወንጀል እንዳይበረክት፣ ሰብሎች በወረርሽኝ እንዳይጠቁ እንዲሁም ድርቅ/ረሃብ እንዳይከሰት ለማድረግ የብሔረሰቡ ዋነኛ አማራጭ እንደሆነ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡

በሪን በመስዋዕትና በጸሎት መገናኘት የሚችሉት ባቢ፣ ጎድሚ እና ጋና የተባሉ በብሔረሰቡ ዘንድ ክብር የሚሰጣቸው ግለ-ሰቦች ይገኛሉ። ባቢ የእምነቱና የስርዓተ-አምልኮ ዋና መሪ ተብሎ ሲታመን መሪነቱንም የሚያገኘው ንጹህ ከሚባሉት ማታዎች ውስጥ በሚሰጥ ሹመት ነው። ባቢ አንዴ ከተሾመ በሞት ካልሆነ በስተቀር ስልጣኑን የሚወስድበት አካል የለም። ሲሞት ብቻ ከወንድ ልጆቹ ታላቅየውን ወይም ወንድ ልጅ ከሌለው ከቤተዘመዶቹ ህዝቡ የሚያምንበትን መርጦ በቦታው ይሾማል። ጎድሚዎች ግን በሹመት ሳይሆን በተፈጥሮ ከተፈጥሮ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የሚታመኑ ሆነው ሲሞቱ ወንድ ልጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ሴት ልጆቻቸውም ስልጣናቸውን ይጋራሉ።

የበሪ እምነት ስርዓተ-አምልኮ ማስፈጸሚያ ዋና መሳሪያ የበግ አንጀት ነው። ለክፉም ለደጉም አጋጣሚ ልምዱ ባላቸው ግለ-ሰቦች አማካይነት የበግ አንጀት እየተነበበ የማንጻት (ጭልሺ) ስርዓት ይፈጸማል። በዚሁ ስርዓት አማካይነትም በሪ ለአማኞቿ ያላትን አላማ እና ኃይል ትገልጣለች ተብሎ ይታመናል። በባቢው መሪነት ለሚፈጸሙ ከበራዎች በግ የሚገዛው ከህዝቡ በተዋጣ ገንዘብ ሲሆን በየግለ-ሰቦች ቤት ለሚከናወን ግን ግለ-ሰቦች በግላቸው ገዝተው ወይም ከበረታቸው አውጥተው በማረድ ስርዓቱን ይፈጽማሉ።

በአጠቃላይ የአሪ ብሔረሰብ ሕይወቱን በሰመረ ኑሮ ለመምራት፣ ግጭቶችን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ለመፍታት፣ ንብረትን ከሌባና ከወረርሽኝ ለመከላከል፣ ቤተሰቡንና አከባቢውን ከተፈጥሮ አደጋዎች ለመጠበቅ ሲል ለበሪ አምልኮ ያደርጋል። ይሁን እንጂ በፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስፋፋትና በብሄረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ፣ በብሔረሰቡ የህዝብ ቁጥር በከፍተኛው እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ለእርሻና ለመኖሪያ ቦታ ሲባል የአምልኮ ቦታዎች በመመንጠራቸው እና በዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት አዲሱ ትውልድ የቀደመውን የአባቶቻቸውን ባህልና ወግ ለመከተል እየሰነፈ በመምጣቱ ይህ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ሀገረ-ሰባዊ እምነት በአሁኑ ጊዜ እየተዳከመ እንደሚገኝ ጥናቱ አረጋግጧል። ለዚህም የእምነቱ ተከታዮች እንደማስረጃ የሚያቀርቡት የእምነቱ አባላት ቁጥር መቀነስን፣ ያሉት አባላትም ለተለያዩ ምክንያቶች የማምለኪያ ስፍራዎቻቸውን መመንጠራቸውን እና ለስርዓቱ ያላቸውን የቀድሞ ክብር እየተዉ መምጣታቸውን እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል።

ከዚህም በመነሳት ይህ ጥናት የሚሰጠው አስተያየት የአሪ ብሔረሰብ የሚፈጽመው የበሪ እምነት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ምግባራዊ ፋይዳው የላቀ በመሆኑ ብሔረሰቡ አጥብቆ እንዲከተለው እና አዲሱ ትውልድም ጥሩ ሰብዕና እንደሚያገኝበት በማመን በአክብሮት

እንዲመለከተው፤ በርካታ የፎክሎር ዘሮችን በአንድ ላይ ለማጥናት የሚያስችለውን ይህን እምነት ጥቃቅን ክዋኔዎቹም ሳይቀሩ እንዲጠናና በቅርስነት እንዲመዘገብ አቅምና ኃላፊነቱ ያላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር ይህን ጥናት መነሻ በማድረግ ሰፊ ጥናት (በዘጠኙም የባላባት ግዛቶች ላይ) ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኚዎች ብሔረሰቡ ለጥናት አመቺ አቀራረብ እና ብዙ የሚጠኑ የፎክሎር ሀብቶች ያሉት በመሆኑ በተገኙ አጋጣሚዎች ሁሉ ብሔረሰቡን ለማጥናት እንዲመርጡ ይጠቀማል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት


መልስ በርሄ፡፡ “የቦዥ አምላክ እምነት በጉራጌ ብሄረሰብ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ የቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ መሟያነት የቀረበ፣ 1980፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፣3ኛ እትም፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡ከ1847 እስከ 1983*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2003፡፡

ናምሲ አልቃ፡፡ “አሪኛ ከአማርኛ የተዋሳቸው ቃላት”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ መሟያነት የቀረበ፣ 1980፡፡

አህመድ መሃመድ፡፡ “በአሪ ብሄረሰብ የቢዮ ባላባታዊ ቤተሰብና የለቅሶ ስርዓቱ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፣ 1989፡፡

አያለው ምትኩ፡፡ “የአሪ ህብረተሰብ የስም አወጣጥ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ መሟያነት የቀረበ፣ 1976፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነቃል መምሪያ*፡ አዲስ አበባ፡ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991፡፡

Alice L. Morton, “Mysticl Advocates: Explanation and Spirit- Sanctioned adjudication in the Shoa Galla Ayana cult.” *Proceedings first United State Conference on Ethiopian studies;* African Stuides center, Michigan University, 1973.

Bender, Lionel, M. *Comparative Morphology of the Omotic Languages*. Lincom Euro Freibadstr; Muenchen, 2000.

Catherine Bell. *Ritual:* perspectives and dimensions. New York: Oxford University press, 1997.

Gebre Yintiso. “The Ari of South Western Ethiopia: An exploratory study of production practices.” Social Anthropology፡ Addis Ababa University; MA Thesis, 1995.

Girma Yadeta. “Traditional Belief Systems and Religious Practice of the North-Eastern Wallega: The Case of Jidda Oromo”. (BA thesis) Addis Ababa University, 1996.

Glodstein, K.S. *A Guide for Field Work in Folklore*. Pennsylvania; Hatbora,Folklore Associates Inc, 1964.

Hamer, John and Irene Hamer. "Spiritpossession and Its Socio-pschological Implications among the Sidama of South West Ethiopia." *Ethnolgoy*, 5, 1966, p. 392-408.

Hamer, John H. "Dispute Settelement and Sanctity: an Ethiopian Example;" (Reprinted from *Anthroplogical quarterly*). Washihgton, Vol. 45, No.4, 1972, 232-47.

James George Frazer. *The Golden Bough:* A Study of Magic and Religion. The Floating press, 2009.

Levine, D.N. *Greater Ethiopia*. Chicago; the University of Chicago Press, 1974.


Martha C. Sims. *Living Folk lore:* Introduction of the Study of People and their Traditions. Utah State University Press, 2005.

Pascal B. and Pierre L. *Behavioural and Brain Science*. Printed in the United Sates of America, 2006.

Smith, E.W., ed. *African Ideas of God*. A Symposium. London, 1950.

Tesfaye Hailu. "Child Birth and Seclusion Among the Omotic Ari" Harold G. Marcus (ed),Papers of the 12th *International Conference of Ethiopian Studies,* Red Sea Press, vol. 2, 1994, p.1017-1032.


# የፎቶ አባሪ



አቶ ድክሳ አስፍን
“ማል” ላይ ተቀምጠው



አቶ ድክሳ አስፍን እና ጎድሚዎች
ለአድባር መስዋዕት ሲያቀርቡ







ባቢው ከጎድሚዎች ጋር የመስዋዕት በግ አርደው አንጀት ሲያነቡ




ሴቶች ቡና ሲያፈሉና
ባቢው ከአድባር ዙሪያ ቀጠማ ሲበትኑ




ባቢው ከአድባር ስር ቡናና ቦርዴ ሲረጩ







የምባ አሪ ህዝብ በወይሳና ያለ ወይሳ ሲጨፍር



አቶ ግንጀሎ ሀቕዳኪ እና ባለቤታቸው
ወ/ሮ ሾሺ ጉስታብ በመኖሪያ ቤታቸው



አቶ ለጋስ ሀቕዳኪ ቃለ መጠይቅ ሲደረጉ



ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ከቡድን ውይይት በኋላ
ጠጅ ሲጋበዙ



ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ከቡድን ውይይት
በኋላ (በሻማመር ቀበሌ ጽ/ቤት ግቢ)



አቶ ድክሳ አስፍን በሪን ሲጸልዩና ጎድሚዎች “አሜን” ሲሉ



አቶ ቡጭሚ (የእህል ጎድሚ) ጉበት ጠብሰው ከባቢው ጋር ለመቅመስ ሲያዘጋጁ

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የራሴ መሆኑንና ትክክለኛ መረጃዎችን የያዘ መሆኑን በግል ፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

| ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| ኮማንደር መሐመድ ብሩሀቃል | ---------------------------- |